
Proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



WWW.BINYAMHK.WORDPRESS.COM

679

# ማርክሲዝም መግቢያ

# N INTRODUCTION TO MARXISM

ትርጉም

በሰለሺ አንዳርጌ

Proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



WWW.BINYAMHK.WORDPRESS.COM


# የማርክሲዝም መግቢያ ።

ጸሐፊ — በኢሚል በርንስ

ትርጉም — በስለሺ አንዳርጌ

Proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



WWW.BINYAMHK.WORDPRESS.COM

## ማ ው ጫ ፤

| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩. | ስለ ዓለም ሳይንሳዊ አመለካከት | 5 |
| ፪. | የሕብረተሰብ ዕድገት ሕጎች | 7 |
| ፫. | የካፒታሊስት ሕብረተሰብ | 21 |
| ፬. | ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ከፍተኛ ደረጃ | 37 |
| ፭. | የመደብ ትግሎችና መንግሥት | 53 |
| ፮. | ሶሻሊስት ሕብረተሰብ | 63 |
| ፯. | ስለተፈጥሮ ማርክሳዊ አመለካከት | 92 |
| ፰. | የተግባር መመሪያ | 106 |

## ማስታወሻ ከተርጓሚው ፤

1. ዓመተ ምህረቶች ሁሉ እንደግሪጐሪያውያን (አውሮፓውያን) አቆጣጠር ነው የተወሰዱት ።

2. (— —) በእነዚህ ምልክቶች ውስጥ ያሉት ሐረጐች ወይም ፀ. ነገሮች ትርጉም ሰጭዎች ናቸው ።

3. መስመር የተሠመረባቸው በ. ነገሮች ሁለት ዓይነት ናቸው ። አንደኛው አፅንዖት ለመስጠት ሌላኛው ደግሞ በ. ነገሩ ላል ገባው ሰው የተሠመረበትን ብቻ በማገጣጠም ትክክለኛ አባባሉን ሊሰጥ የሚችል ነው (በመካከሉ ያሉ ሐረጐችን በመተው ማለት ነው) ።

4. አንዳንድ አዳዲስ ቃላትን ተጠቅሜአለሁ ። ለዚሁም ለማገናዘብ እንዲመች እንግሊዝኛውን ያስገባሁ ስለሆነ ሀሳቡን መረዳት ይቻላል ።



# ስለዓለም ሳይንሳዊ አመለካከት

ማርክሲዝም የምንኖርባት ዓለምና ከዓለም አካል አንዱ ስለሆኑት ሰዎች አጠቃላይ የሆነ ንድፈ — ሀሳብ የሚሰጠን ነው ። ስሙን የወሰደው ባለፈው ምዕተ ዓመት አጋማሽና በኋላ ንድፈ — ሀሳቡን ከቀመረው ከካርል ማርክስ (1818 — 1883) እንበልም ከፍሬድሪክ ኤንግልስ (1820 — 1895) ጋር ይሠራ ከነበረው ነው ።

እነኚህ ሰዎች ሰብአዊ — ሕብረተሰብ እንዴት እንደ መጣ ፤ እንዴት እንደ ሚለወጥ ፤ ወደፊትም የሚአደርጋቸው መጠቅ ያሉ ለውጦች እንደሚኖሩ መመራመር ያዙ ። ጥናታቸው እነኚህ ለውጦች እንደውጫዊው ተፈጥሮ

(External nature) ሁሉ ድንገታዊ ሳይሆን የተወሰነ ሕግ ይዞ ይጓዛል ወደሚል መደምደሚያ ላይ አድርሷቸዋል ። ይህ እውነት ስለሕብረተሰብ ሽፍን አስተሳሰብ ከአቀረቡት) አሁንም ከሚአቀርቡት) ማለትም ከሃይማኖት እምነቶች ፤ ከዘርና ከጀግና ተዋጊነት፤ከግለሰብ ዝንባሌ ወይም ተምኔታዊ ሕልሞች አመለካከት ተጻራሪ በመሆን በሰዎች ዕለታዊ ገጠመኝ ላይ (Experience) በመመሥረት ስለሕብረተሰብ ሳይንሳዊ ንድፈ — ሀሳብ ለማቅረብ ያስችላል ።

ማርክስ ይህንን አጠቃላይ ሀሳብ በኖረበት ሕብረተሰብ
ተጠቅሞበታል ፤ በተለይም በካፒታሊስቷ ብሪቴይን ፤ እና
ም ይበልጥ የታወቀበትን የካፒታሊዝም ምጣኔ — ሀብታዊ
ንድፈ ሀሳቡን ሥራ ከውኗል ። ነገር ግን ሁልጊዜም ያሳስብ
የነበረው የእርሱ ምጣኔ — ሀብታዊ ንድፈ ሀሳቦች ከታሪ
ካዊውና ከሶሻል ንድፈ ሀሳቦች ሊገነጣጠሉ እንደማይችሉ
ነው ። ትርፍና ምንዳዕ ሊጠኑ የሚችሉት እስከ ተወሰነ
ነጥብ ድረስ እንደ ንጹህ ምጣኔ ሀብታዊ ፕሮብሌሞች ሆነው
ነው ። ግን ሥውርን ሳይሆን እውነተኛ ሕይወትን የሚአጠ
ና ሰው ትርፍና ምንዳዕ ሙሉ በሙሉ ሊጤኑ የሚችሉት
ቀጣሪዎችና ሠራተኞች በመድረክ ላይ ሲመጡና ፤ እነኝህ
ም በተራቸው ስለሚኖሩበት ታሪካዊ ደረጃ ወደሚመራ
ጥናት ሲአስመለክቱ መሆኑን ወዲያውኑ ያረጋግጣል ።

ስለ ሕብረተሰብ ዕድገት የሚመለከተው ሳይንሳዊ
አቀራረብ የተመሠረተው እንደሌሎች ሳይንሶች ሁሉ በገ
ጠመኝ፣ በታሪክ እውነቶችና በአካባቢአችን ዓለም ነው ።
ስለዚህ ማርክሲዝም የተጠናቀቀና የአበቃ ንድፈ ሀሳብ
አይደለም ። ታሪክ እንደማይታጠፍ ሁሉ ፤ ሰዎች ብዙ
ገጠመኝ እንደሚሰበስቡ ሁሉ፤ማርክሲዝምም በማያቋርጥ
ሁኔታ እየዳበረና በአዲስ እውነቶች ላይ በተግባር እየዋለ
ይሄዳል ። ከነኝህ ዕድገቶቹ ብዙውና ዓይነተኛው ማርክስና
ኤንግልስ ከሞቱ ጀምሮ የዳበረው በሌኒን (1870 — 1924)
ነው ።

ሕብረተሰብን ለማጥናት የተካሄደው የሣይንሣዊ አቀ
ራረብ ውጤቱ ሕብረተሰብን ለመለወጥ የሚአገለግል ዕው
ቀት ማስገኘቱ ነው ። ማለትም ሁሉም ሳይንሳዊ ዕውቀት
ውጫዊውን ዓለም ለመለወጥ እንደሚአገለግል ሁሉ ። በተ
ጨማሪም ይህ ዕውቀት የሕብረተሰብን እንቅስቃሴ የሚ
ገዛው አጠቃላይ ሕግ ከውጫዊው ዓለም ሕግ ጋር አንድ
ዓይነት ሂደት እንዳለው ግልጽ ያደርጋል ። እነኝህ ሕጎች
በአጠቃላይ ጥሩ ነገሮችን የሚይዙት ማለት ነው (ለሰዎ
ችም ሆነ ለነገሮች) ማርክሲስት ፍልስፍናን ወይም ርዕዮተ
ዓለም የሚባለውን ያስገኛሉ ።

የሚቀጥሉት ምዕራፎች በጣም አጣዳፊ ፍላጎትን በ
ሚመለከተው የማርክሲስት ንድፈ ሀሳብ ላይ ያተኩራሉ ።
አስፈላጊ ናቸው ፤ ምክንያቱም ማርክሲዝም የሚመነጨው
ከዕውነቶች ሣይንሳዊ ጥናት ስለሆነ ፤ ምክንያቱም ንድፈ
ሀሳቡ ከዕውነቶች ስለሚስማማ ፤ ባጭሩ ምክንያቱም እርግ
ጠኛ ስለሆነ ፤ ለአንባቢ ማጤኑና መገንዘቡ ያሻል ። እናም
እርግጠኛ ስለሆነ በዓለም ላይ ብዙ ሰዎችን ከሚአሰቃዩ
ችግርና ሥቃይ ነጻ ለማውጣት የሚአስችል እና መጠቀም
ም ያለብን ፤ ሰዎችም ከፍተኛውን ሕብረተሰብ ለመመሥ
ረት የሚአስችላቸው መሆኑን የምንቀበለው ነው ።

ም ዕ ራ ፍ ፪

# የሕብረተሰብ ዕድገት ሕጎች

ከዚህ በፊት የሰው ልጅ ታሪክ ሁሉ የቀረበውና የተመ
ዘገበው በብሔሮች መካከል በሚደረግ ጦርነትና በግለሰብ
ዘውዶች ፤ ጀኔራሎች ወይም በመሣፍንት ብዝበዛ ላይ
በመመሥረት ነው ። አንዳንድ ጊዜ የነኝህ ግለሰቦች ግፊት
የሚገለጸው በግለሰብ መንገድ ነው ፤ እንበል — ምኞታ
ቸው ግዛትን አሸንፎ ወደማምጣት መራቸው ወይም ሞራ
ላዊ ወይም ከሞራል ውጪ የሆነ አመለካከታቸው የተወሰኑ

ምክንያት ሆነ ። አንዳንድ ጊዜ
ፖሊሲዎችን እንዲአቀርቡ ምክንያት ሆነ ስለሀገር ክብርና መቆርቆር በሚ
ፍላጐቶቻቸው የሚገለጹት ስለሀገር ክብርና መቆርቆር በሚ
ደረግ ወይም ከሃይማኖታዊ ግፊት የተነሣ እንደ ሆነ ነው ።

ማርክሲዝም በዚህ ዓይነት የታሪክ አቀራረብ አል

ረካም ።

በመጀመሪያ ደረጃ ትክክለኛው የታሪክ ሣይንስ መሆ
ንና መገኘት ያለበት ከሕዝብ ነው ። ለምሣሌም የ1640
ዓ.ም. የእንግሊዝን አብዮት የመራውንና የመልከኛውን
እሽክላ እንደሰበረው ዓይነተኛ ሰው እናም የብራቱንን ካፒ
ታሊዝም ለመገንባት ስሬ በር እንደከፈተ ሆኖ የተወሰደውን
ክሮምዌልን እንውሰድ ። መጤን ያለበት የእርሱ ጦርነትና
ሃይማኖታዊ አመለካከቱ ወይም ያንን ለማካሄድ የሠራው
ተንኰል አይደለም ፤ በብሪቴሽ የምርት ዕድገትና ማከፋፈል
ላይ ለክሮምዌል የሚሰጠው ቦታ መጠናት ያለበት በብሪ
ቴን ውስጥና በዚያን ጊዜ የፊውዳሉን ዘውዳኛ በመጻረር
ትግሉ እንዴት ዳበረ ? በሚለው ጥያቄ ላይ ነው ። በዚያን
ጊዜ ለውጡን ያስመጣው ሁኔታ ያለው ጥናት ነው ዋናው
ነገር ።እነኝህ አስፈላጊ ናቸው ፤ለታሪክ ሳይንስ መሠረቶች
ናቸውና።ከዚህ ዓይነት ጥናት ላይ የመጣውን ዕውቀት በመ
ጠቀም (በተጨማሪም በሌላ ጊዜና በሌሌላ ሕዝቦችም የሆነ
ውን በማገናዘብ ) ፤ አጠቃላይ ንድፈ ሀሳቦችን ለመሰንዘር
ይቻላል ። እንበል ስለሕብረተሰብ ዕድገት ሕጎች — ማ
ለትም እንደኬምስትሪ ወይም እንደሌላ ሳይንሶች ሕጎች
ዕውነት የሆነውን ። እናም አንዴ እነኝህን ሕጎች ካወቅን
ልዩ ሕጐችን እንደምንጠቀምባቸው ሁሉ በእነዚህም
መጠቀም እንችላለን ። ወደፊት የሚሆነውን እንተነብያለን
ሳይሆን ሲሆን እንዴት እንደሚችል የሚአረጋግጠውን
ድርጊት እናሳያለን ።



ስለዚህም ማርክሲዝም በሰዎች ታሪክ ውስጥ እየተ ጓዘ የቆየውን ሁኔታ ለማወቅና ተፈጥሮአዊ ሕጐችን ለመ ገንዘብ በዚህ ዓይነት ታሪክን ይቀርባል ። ስለዚህ የሚአተ ኩረው በግለሰብ ሳይሆን በሕዝቡ ላይ ነው ። እናም ሕዝ ቡን ሲመለከት (ከጥንታዊው ሕብረተሰብ በኋላ) የተለያዩ የሕዝብ ክፍሎች እንዳሉ ፤ አንዱ ሌላ ሌላኛውም ሌላ መን ገድ ሲከተሉ በግለሰብ ሳይሆን እንደመደቦች ሆነው ያገኛ ቸዋል ።

እነኝህ መደቦች ምንድን ናቸው ? በቀላል አገላለጽ የሕዝብ ክፍሎች ሆነው ኑሮአቸውን በአንድ ዓይነት መን ገድ የሚአካሂዱ ናቸው ። በመልከኛው ሥርዓት ዘውዳኛ ውና መልከኞች ኑሮአቸውን የሚገፉት ከገባሮቻቸው ከሚ ወስዱት ክፍያ (የግል ግልጋሎትም ይሁን ወይም የዓይነት ክፍያ) በተለይ ከመሬት ከሚገኘው ምርት ነው ። መልከ ኞች (ፊውዳሎች) በጥቅም የተሳሰረ መደብ ያላቸው — ከገ ባሮቻቸው ጉልበት የሚገኘውን ነገር በተቻለ መጠን በብ ዛት ለመውሰድ የሚፈልጉ ፤ መሬታቸውን ለማስፋፋትና የሚሠሩላቸውን ገባሮች ለማብዛት የማይቋረጥ ጉጉት ያደረባቸው ናቸው ። በተግባርም ያሳያሉ ። በዚሁ ተጻራሪ ገባሮች ከመደብ ፍላጐታቸው ጋር የራሳቸው የሆነ መደብ አላቸው ፤ ያመረቱትን ለጌቶቻቸው ከማቀበል ይልቅ በብ ዛት ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ለማስቀመጥ ይሻሉ ፤ ለራሳቸው ለመሥራት ነጻነት ይፈልጋሉ ፤ የጌቶቻቸውን የድንብ አውጭነት ፤ ዳኝነት ፤ ጭቆናዊ ውርጅብኝና ገፋፊ ነት ለመወርወር ይጥራሉ ።

ስለዚህም በመልከኞች አገር ውስጥ ሁሉ በመልከኛ ውና በገባሩ መካከል የሚካሄድ የማያቋርጥ ትግል አለ ። ይህም አንዳንዴ በግለሰብ ደረጃ ብቻ ፤ ወይም ሰፋ ባለ

ሁኔታ ማለትም ብዙ ገባሮች የሚሳተፉበት ነው ። ይህ የሚ
ሆነው የኑሮ አቸውን ሁኔታ ለማሻሻል ነው ። በእንግሊዝ
በ1381 ዓ.ም. በጀንቦልና ዋት ቲለር መሪነት የተካሄደው
ብጥብጥ የዚሀ ምሣሌ ነው ። ተመሳሳይ የሆኑ የገበሬ ዎች
ወይም የገባሮች መነሳሳት (Risings) በጀርመን ፤ በሩ
ሲያና በሌሎች ብዙ አገሮችም ታይተዋል ፡ ይሁንና ትግሉ
በአነስተኛ ደረጃ ነበር ሳያቋርጥ የተከታተለው ።

በተጨማሪም በጌቶቻቸው መሬት ላይ እንዲሰሩ ከመገ
ደዳቸው ሌላ ፤ በዓይነት የሚከፈልም ክፍያ ነበር ። ካላቸው
ይዞታ ላይ ከሚመረተው ምርት ብቻ ሣይሆን በገባሮችና
በገባሮች ቤተሰቦች ከሚሰሩት የጅ ሥራ ውጤቶችም ነው ።
በሙያው የሰለጠኑ አምራች ገባሮች ነበሩ፤ለምሣሌ ፡ —
የጦር መሣሪያዎችና የተለያዩ ዕቃዎችን የሚሰሩ ። ከሌሎች
አካባቢዎች ወይም አገሮች ጋር ካሉት ውጤቶች ለመለ
ዋወጥ ከመጠን በላይ የሆነ ምርት የሚገዙ ነጋዴዎችም
ነበሩ ። ከንግድ ማደግ የተነሣ እነኝህ ነጋዴዎች በገባሮች
ከሚመረተው ትርፍ ምርትና መልከኛው ከሚፈልገው
በላይ የበለጠ ምርት ፈለጉ ፤ ስለዚህ ምርትን ለማዳበር እና
ለገበያ ለማቅረብ በተቀናጀ መልክ ገባሮችን ወይም ገበሬ
ዎችን በማደራጀትና ጥሬ ሀብቱን በማቅረብ ፤ ውጤቱንም
በመግዛት አዲስ መልክ አስያዙት ። አንዳንድ ነጻ የወጡት
ገባሮች በከተማ ራሳቸውን በራሳቸው ነጻ ባለሙያዎች በማ
ድረግ፤ልብስ በመሥራት ፤ ብረታ ብረትን በማዘጋጀትና
ሌሎችንም ዕቃዎች በማምረት ተቋቋሙ ።

ስለሆነም ብዙ ምዕተ — ዓመታት በመውሰድ በዝግታ
በመልከኛው ምርት ውስጥ ለአካባቢው ብሎት እና ለገበያ
ሲባል ምርት በነጻ ባለሙያዎችና በጉልበት ምንዳዕ ቀጣሪ
ዎች አማካኝነት እያደገ ሄደ ። ነጻ ባለሙያዎችም ቀስ በቀስ



ወደ ጉልበት ቀጣሪነት ተሻገሩ — ማለትም የሰለጠኑ የቀን
ተቀጣሪዎችን በምንዳዕ ያዙ ። ስለዚህም ከ16ኛው ምዕተ—
ዓመት ጀምሮ አዲስ መደብ መጣ — የኢንዱስትሪ ከበርቴ
መደብ የሚባለው ። ከዚህም ጥላ ሥር የኢንዱስትሪው ሠራ
ተኛ መደብ ። በገጠርም ውስጥ አሮጌው የመልከኛ ማስገ
ደጃ ደንብ ነኳኩተ፤ግላዊ ግልጋሎት በገንዘብ ኪራይ ተለ
ወጠ ። በብዙ ሁኔታዎች ገባሮች ወደ ነጻ ገበሬነት ተሻገሩ
— የየራሳቸው ይዞታ ኖራቸው ። መልከኛው በመሬቱ ላይ
ለማሠራት ለሚፈልገው ሥራ የጉልበት — ኃይል ምንዳዕ
መክፈል ጀመረ ። በዚህም መንገድ የካፒታሊስቱ ገበሬ
ሕልውና ምንዳዕ እየተከፈለው ከሚሠራው የእርሻ ሠራ
ተኛ ጋር ተከሰተ ።

የካፒታሊስቱ መደብ ዕድገት ወዲያውኑ የቀድሞ ፊው
ዳላዊ የገዥ መደብን ዕድሜ አላሳጠረውም ። በተቃራኒው ፤
ዘውደኝነት ፤ የድሮ የባለመሬት መሣፍንትነትና ቤተክርስ
ቲያን አዲሱን ካፒታሊዝምን ለራሳቸው ጥቅም መጠበቂያ
ለማድረግ የተቻላቸውን ጥረት አድርገዋል ። ነጻ የወጡት
ወይም እያመለጡ ወደ ከተማ የገቡት ገባሮች ለጌቶቻቸው
ከሚከፍሉት ነገር ሁሉ (ከግላዊ አገልግሎት ፤ ከዓይነት
ወይም ከገንዘብ ክፍያ) አምልጠዋል ። ግን በዚሁ አንጻር
የነኝህ ገባሮች ዝርያዎች ሀብታምነት ሲአድግ በእውነት
ነጻ እንዳልወጡ ተገነዘቡ ። ንጉሡና የፊውዳል መኳንንት
በተለያዩ ዓይነት ግብር እንዲከፍሉ ፤ በንግዳቸው ላይ ገደብ
እንዲኖበርት እና የመሣሪያዎችን (ዕቃዎችን) የማምረት
ሥራ ነጻ ዕድገትን ከለከሉ ።

ንጉሡና መኳንንቱ ይህንን ደንብ ሊሰሩ የቻሉበት
ምክንያት የመንግሥቱን መሽከርከሪት ስለሚቆጣጠሩ —
ነው ። የጦር ኃይሉን ፤ ዳኞችንና (ፍ/ ቤቶችን) እስር ቤቶ

ችን፣ሁሉ ። በዚያውም ላይ ሕጐችን ያወጣሉ ። ስለዚህ የከበርቴው መደብ ማደግ ማለት አዲስ መልክ ያለው የመደብ ትግል መዳበር ነው ። ከበርቴው ከዘውዶችና ከመልከኞች አንጻር በመቆም ራሱን ለትግል መሰለፍ አለበት ። ለረጅም ምዕተ—ዓመታት የቀጠለ ትግል ። በአንጻሩም ወደ ኋላ በቀሩ አንዳንድ ሀገሮች አሁንም ይህ ትግል ይካሄዳል ። ግን ለምሣሌ በብሪቴንና ፈረንሣይ በፊት የአከተመ ነው ።

## ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?

በብሪቴን ፣ ከሌሎች አገሮች ይልቅ ይህ ደረጃ በጣም ራቅና ቀደም ብሎ በደረሰበት በአዳጊው የካፒታሊስቱ መደብ ታክስንና ገደብን በመጻረር የሚካሄደው ትግል በ17ኛው ምዕተ ዓመት ከፍተኛውን ደረጃ ደረሰ ። እነኝህ ገደቦች የካፒታሊስቱን የምርት ዕድገትና መስፋፋት ወደኋላ ጐትተው ያዙት ። ከበርቴዎች በሰላማዊ መንገድ ገደቦች የሚወገዱበትን ዘዴ ፈለጉ ፦— ውሣኔ ለንጉሡ በማሳለፍ፣ ግብሩን ባለመክፈል ፣ እና በሌላም ። ግን የትኛውም ከመንግሥቱ መሸከርከሪት አንጻር በመቆም ሊአሸንፍና እዳር ሊአደርስ አልቻለም። ስለሆነም ፣ ከበርቴዎች ኃይልንበኃይል መቋቋም መሆኑን አጤኑ። በንጉሡ፣ በገፋፊው ግብር እና የንግድ ገደቦች፣ በንጉሡና በዳኞች በሚወሰኑት እሥራቶችና መቀጫዎች ላይ ሕዝቡን ማስነሳትና የፊውዳሉን አሸክላ እንዲሰበር ማድረግ ግዴታ ሆነ ። በሌላ አነጋገር ከበርቴዎች ትጥቃዊ አብዮት ማቀናጀት እና ሕዝቡን በንጉሡና በአሮጌው የጭቆና መልክ ላይ መሣሪያ ይዞ እንዲነሣ ለመምራት ቆረጡ ። የቀድሞዎቹን ገዥዎች በወታደራዊ ስልት ድል ለማድረግ መሆኑ ነው ። ይህ ከተፈጸመ በኋላ ብቻ ነው የከበርቴው መደብ የገዥ መደብ እንዲሆን ያበቃው ።



አሸክላዎችን ሁሉ ለመሰባበርና ለካፒታሊዝም ዕድገት የሚአስፈልገውን ሕጐች ለማርቀቅም ያስቻለው ።

በእንግሊዝ የተካሄደው የከበርቴ አብዮት የቀረበው ቻርልስ 1ኛን በመዋጋት እንደነበር ትክክልና እርግጥ ነው ። (ምክንያቱም ርሕራሄ የሌለው ጨቋኝ ፣ በሮማዊ ካቶሊክ አዘንባይነት የተላበሰ ንጉሢ ነበር ።) ክሮምዌል ግን ክቡርና ጸረ—ካቶሊክ፣ ስለብሪቴን ነጻ መሆን ትልቅ ሀሳብ ያለው ነው ። ትግሉ ባጭሩ እንደሞራልና ሃይማኖታዊ ጦርነት ሆኖ ነው የቀረበው ። ማርክሲዝም ከግለሰቦች አልፎ ጠልቆ ይሄዳል ፣ ጦርነቱ ከተካሄደበት ማቀንቀኛም በማለፍ ይመራመራል ። ማርክሲዝም በዚያን ወቅት የተካሄደውን የትግል ባሕርይ የአረጀውን የፊውዳል የገዥ መደብ ሥልጣን ለመንጠቅ የመጣ የከበርቴ መደብ ትግል አድርጐ ነው የሚመለከተው ። እናም ግልጽ የሆነ የመታጠፊያ ነጥብ ነበር ። ከዚያ አብዮት በኋላና በዚሁ የሁለተኛው ደረጃ በ1688 ዓ.ም. የከበርቴው መደብ መንግሥቱን የመቆጣጠር ድርሻ በማግኘት አሸንፏል ።

በእንግሊዝ የካፒታሊስት ደረጃ ቀደም ብሎ በመምጣቱ ምክንያት የከበርቴዎች ድል አድራጊነት ወሳኝና ያለቀለት አልነበረም ። ስለዚህም አሮጌው የመልከኛ ግንኙነት በብዙው ቢደመሰስም ፣ የመሬት ከበርቴዎች (የከተማ ከበርቴዎችን ጨምሮ) ለተከታታይ ሁለት ምዕተዓመታት በተጨማሪ በገንዘብ ወለድ ላይ እና በመንግሥቱ ቁጥጥር ላይ ከፍተኛ ድርሻ በመጨበጥ ለብዙ ጊዜ ቆይተዋል ።

ነገር ግን በፈረንሣይ ሁሉም ዓይነት ሂደት ዘግይቶ በመጣበት ፣ እስከ 1789 ዓ.ም. የካፒታሊስት አብዮት ባልተካሄደበት ፣ ለውጡ በአጣዳፊ ነው የተከናወነው ። ይሁንና

ለማርክሲስቶች ይህ ሊሆን የቻለው ሩሶና ሌሎች ደራሲዎች የሰውን ልጅ መብት ስለማስከበር ስለተናገሩ ወይም የአብዮቱ ማቀንቀኛ «ነጻነት ፣ እኩልነትና ወንድማማችነት» ስለሆነ አይደለም ። የክሮም ዌል አብዮት ባሕርይ የመደብ ትግል እንጂ የሃይማኖት ማቀንቀኛ አልነበረም ። ስለዚህም የፈረንሣይ አብዮትም ባሕርይ የሚገኘው በመደቦች ግንኙነትና ዝምድና እንጂ በሰንደቃቸው ላይ ይዘውት በሚዞሩት ውስብስብና ሽፍን በሆነው «የፍትሕ» መርሆ አይደለም ።

ስለዚያ ወቅት ማርክስ ሲናገር «አንድን ግለሰብ ባለው አስተያየት መሠረት እንደማንገምተው ሁሉ አብዮትንም ባለው የራሱ ንቃት ይህ ነው የሚል ግምት ልንሰጠው አንችልም» ብሏል ። በፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ግምገማ መግቢያ ለአብዮታዊ ወቅት ዋናው ዓይነተኛ ነገር ለሥልጣን የሚታገሉትን መደቦች ማየት ፤ ከአሮጌው መደብ ሥልጣን የሚረከበውን ማጤን ነው ። በንቃትም ይሁን ያለንቃት የአዲሱ መደብ መሪዎች ትግላቸውን በጊዜው ከተንጸባረቀው ሥውር ሐሳብ ወይም ጥያቄ ላይ ፤ ከመደብ ጥያቄ ፍላጐትና ከመደብ ሥልጣን በቀጥታ ካልተያዘው ጋር እንዲሆን ያደርጋሉ ።

ማርክሳዊ የታሪክ አቀራረብ ግን ትግልን የሚአየው በተዋጊ መደቦች መካከል የሰውን ዕድገት ለማዳበር የሚአስችለው ኃይል ዋናው የትኛው መሆኑን በመለየት ነው ። ግን የሕብረተሰብ በመደብ መከፋፈልና የአዲስ መደቦች መምጣት የሚመረኰዘው ሰዎች ለሕይወታቸው የሚአስፈልጓቸውን ነገሮች ለማምረት በሚአስችሉአቸው በምርት ኃይሎች ዕድገት ነው ። በእንፋሎት የሚንቀሳቀሱ ማሺኖች መገኘት ለምርት ከፍተኛ ምጥቀት ነው ። ይህም ብቻ



አይደለም ። ከራሱም ጋር በራሱ መሣሪያ የሚአመርተውን አምራች ማለትም በዚህን ወቅት ከተገኘው መሣሪያ ጋር ተወዳድሮ ሊቋቋም በማይችልበትና ወደመጥፋቱ አደረሰው ። ስለሆነም ግለሰብ አምራች — የራሱ መሣሪያ ባለቤትና ተጠቃሚው — ለሁለት የሕዝብ ቡድኖች ቦታ ለቀቀ ። አዲስ ለተሠራው መሣሪያ ባለቤት ለሆነው — ራሱ ለማይሠራው የከበርቴ መደብና ለኢንዱስትሪው ሠራተኛ መደብ ፤ ምንም የምርት መገልገያ ባለቤት ላልሆነውና ለባለንብረቱ እየሠራ የጉልበት ኃይሉን ምንዳዕ ለሚቀበለው ።

ይህ ለውጥ የመጣው በንቃት አይደለም ፤ ቀድሞ በተዘጋጀም ዕቅድ አይደለም ፤ በጥቂት ሰዎች በተገኘው አዲስ ዕውቀት ውጤት ነው ። ይህንንም ዕውቀት ለራሳቸው ሲሉ በምርት ላይ በተጠቀሙበት ። ግን የሚአስከትለውን የሕብረሰብ ውጤት (የወደፊቱን) በመገንዘብ ሳይሆን ለጊዜው ያለውን የገንዘብ ፍላጐት ማሙያ በሚደረግ የዘፈቀደ ድርጊት ነው ። ማርክስ ከዚህ በፊት ለተደረገው የሕብረተሰብ ለውጥ ሁሉ ይህ ዕውነት ነበር ፤ ሆኗልም ፤ ብሏል ። ሰው ዕውቀቱን በየጊዜው እየጨመረ ይህንንም በምርት ተግባር ላይ እያዋለ ሄደና ፤ በዚህም መሠረታዊ የሆነ ለሕብረተሰብ ለውጥ ምክንያት ሆኗል ። እነኝህ የሕብረተሰብ ለውጦች ወደመደብ ግጭቶች ከዚያም አስተሳሰቦች ወይም ተቋሞች ማለትም ወደ ሃይማኖት ፤ ሸንጎዎች ፤ ፍትሕና ሌሎችም ተላልፈዋል ። ምክንያቱም ሃሳቦችና ተቋሞች ያለፉት የተመሠረቱት ባለፈው ሥልተምርትና የመደብ ግንኙነት ነውና ።

እነኝህን ሀሳቦችና ተቋሞች ወደ ሕልውና ምን አመጣቸው ? እንዲአከትሙ ያደረጋቸውስ ምንድነው ? ማርክስ ሲጠቱም ሁልጊዜ ምና የትም ቦታ ሃሳቦች ፤ ተቋሞች ሊአ

ድጉ ሊአቆጠቆጡ የሚችሉት ካለው የሰዎች ዕለታዊ ተግ
ባር ነው ። የመጀመሪያው ነገር ለመኖር ምክንያት የሆነው
ምርት — ምግብ ፤ ልብስና መጠለያ ዋናው ነው ። በማንኛ
ውም ታሪካዊ የሕብረተሰብ ክፍል ፡ — ጥንታዊው ጋርዮሽ
የባሪያ ሕብረተሰብ ፤ የመልከኛው ሕብረተሰብ ፤ የከበርቴው
ሕብረተሰብ ሁሉ በቡድኑ ውስጥ በሚገኙት አባሎች ያለው
ግንኙነት የሚወሰነው በምርት መልኩ ነው ።

ስለዚህ ፤ ከዚህም በማከታተል — የምርቱ ሁኔታ ሲለ
ወጥ — ለምሳሌ ከመልከኛው ወደ ከበርቴው — ሀሳቦችና
ተቋሞችም ይለወጣሉ ። በአንድ የሕብረተሰብ ደረጃ ላይ
ሞራላዊ የነበረው ነገር በሌላ ጊዜ ከሞራል ውጭ እየሆነና
እየተለወጠ ይሄዳል ። ቁሳዊ ለውጥ በሚፈጠር ጊዜ ማለ
ትም የምርት ለውጥ ሲኖር ያሉትን ተቋሞች ለመቋቋም
ሲባል የሀሳቦች ግጭት ሁልጊዜ ይመጣሉ ።

ካለው የካፒታሊስት ምርት ዕድገትና ከፊውዳሊዝም
ቅራኔ ጋር አብሮ የሀሳቦች ቅራኔም መጣ ፡— መለኮታዊ
ኃይል አይደለም ፤ ግን «ለማይወክለን ግብር የለም» ፤
በነጻ የመነገድ መብት ፤ እና የበላጠ የግለሰብ መብትን
የሚገልጹ አዲስ ሃይማኖታዊ ጽንሰ ሀሳቦች ፤ ላላ ያለ ማዕ
ከላዊ ቁጥጥር የሚሉት ናቸው ። የቀረቡትም በሰዎች ነው ።
ነገር ግን ለሥውር መብቶችና ሃይማኖታዊ ምክንያቶች
እስከዎት ድረስ ሰዎችን የአዋጋቸው ባቆጠቆጠው ካፒታ
ሊዝምና በሚሞተው ፊውዳሊዝም መካከል የማያረገው
ትግል ነው ። የሀሳቦች ግጭት ግን ሁለተኛ ደረጃ ነው ።

ማርክሲስቶች ሥውር «መርሆዎችን» ሕብረተሰብን
ለማያራጅት ሲሉ አያቀርቡም ። ማርክሲዝም እንደነኝህ
ዓይነት መርሆዎችን የሚቆጥራቸው ፤ በሰዎች ሀሳብ ውስጥ



እንደ ሖረቡ ሁሉ በቀላሉ የሚአንጸባርቁት በተወሰነ ወቅ
ትና ቦታ ሕብረተሰቡ የተደራጀበትን እንጂ ሁልጊዜምና
የትም ጥሩ የሆነ ነገር ይዘው አያውቁም ሊይዙም አይች
ሉም ነው የሚለው ። ከዚህም በላይ ሁለንቲዊ (Universal)
መስለው የሚታዩ ሀሳቦች «እንደሰብዓዊ እኩልነት» ያሉ
ት ፤ በተለያዩ የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ዎች ሁሉ የሚ
ሉት አንድ ዓይነት አይደለም ። በግሪክ (ዕርዕ) የከተማ መን
ግሥታት የሰዎች «የዕኩልነት መብት» አሳቦች ባሮችን
አይመለከቱም ፤ «ነጻነት ፤ እኩልነትና ወንድማማችነት»
የሚለው የትልቁ የፈረንሳይ አብዮት ማቀንቀኛ መፈክር
የሚናገረው ለአዲሱ የካፒታሊስት መደብ በነጻ ለመነገድ ፤
የዚሁኑ መደብ ከፊውዳሉ መደብ ጋር የዕኩልነት ነጻነትን
እና ለዚሁ መደብ ወንድማማችነት ነው የሚጠይቀው ፡—
እንበልም ከፊውዳሉ ጭቆናና ገደብ አንጻር ለመቆም የእ
ርስ በርስ መረዳዳት ። ከነዚህ አሳቦች አንዳቸውም እንኳ
በፈረንሳይ ቅኝ ውስጥ ላሉት ባሮች ወይም በፈረንሳይ
ውስጥ ለሚኖሩት ድሆች አልዋሉም ።

ስለሆነ ፤ ከሕብረተሰብ አደረጃጀት ጋር የተያያዙ ሀሳ
ቦች እንደሕጉ ከሆነ መደባዊ ናቸው ። የገዥው መደብ ሀሳ
ቦች ማለት ነው ። እነኝህም በፕሮፓጋንዳ ማሠራጫ ባለ
ቤትነት ፤ ትምህርትን በመቆጣጠር እና ተጻራሪ ሀሳቦች
አቀራቢዎችን በሕጋዊ ፍ/ቤቶች በመቅጣት ፤ ከአገር በማ
ባረርና በተመሳሳይ ርምጃዎች አማካይነት ወደ ሠፊው
ሕዝብ ይሠራጫሉ ። ሕዝቡም የራሱ አድርጎ እንዲቀበላ
ቸውና እንዲአንጸባርቅ ይገደዳል ። ይህን ገዥው ለራሱ
ይለዋል ፤ ይናገረዋል ማለት አይደለም ። ለምሳሌ —«አንድ
እውነት ያልሆነ ነገር ይኸውና ግን ሌሎች ሰዎች እንዲአ
ምኑት እናስገድዳለን ወይም ቢአንስ በሕዝብ ፊት እንዳይ
ካድ እንሻለን»—ብሎ አይናገርም ።እንዲያውም እንደሕጉ

ከሆን ገዥው መደብሀሳቦችን ሊፈጥር አይችልም ። ሐሳቦ ች የሚገኙት ከዕለታዊ ሕይወት ነው ። ለምሳሌም የነበ ረው የመሬት ከበርቴ ሥልጣን ወይም ሀብታሙ ኢንዱስ ትሪያሊስት «ዱክ» የተሰኘው ፤ከሰው ሁሉ በላይ ናቸው ለተባሉት «መኳንንት» ቁሳዊ መሠረቶች ናቸው ። ግን እንዴ ሀሳቡ ከወጣና መሠረት ከያዘ ሁሉም ሰው እንዲቀ በለው ለማድረግና ለማረጋገጥ ለገዥው መደብ ዋና ሆኖ ይቀርባል ። ሕዝቡ ባይቀበለው ማለትም ከዚያ ጋር በማይ ሰምር ሁኔታ ሥራን ባይሠራ ለምሣሌም የንጉሡን መለኮ ታዊ መብት መቋቋም (እናም ምናልባትም ከዚያም አልፎ ራሱን እስከ መቁረጥ) ይደርሳል ። ይህን በፈረንሳይ ያየነው ነው ። ስለዚህም በማንኛውም ወቅትና አገር ገዥው መደብ የሚችለውን ያህል «አደገኛ ሀሳቦችን» እንዳይሠራጩ ለማ ገድ ይጥራል ።

ግን ፡ — ሀሳቦች ሁለተኛ ደረጃ ከሆኑ ፤ የመጀመሪያ ውና ተቀዳሚው ዕውነት የምርት ቁሳዊ መለወጥ ሲሆን ፤ እንዴት «አደገኛ ሀሳቦች »ሊመጡ ይችላሉ ? በአጭሩ ፤ ሕዝቦች ስለአዲስ ዓይነት ምርት ከመምጣቱ ከመታየቱ በፊት እንዴት ሊአስቡ ይችላሉ ? ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል ።

መልሱ ሕልውናው ከመታየቱ በፊት ሊታሰብ አይች ልም ። ግን ሕልውናው ሲከሰት ይታሰባል ። በተለይም በአሮጌው ሁኔታና በአዲሱ የምርት ኃይሎች መካከል በሚ ካሄደው ግጭት ። ለምሣሌም ፡ — ከአለው የምንዳዕ ጉል በት የምርት ዕድገት እና ትርፍን ለማወቅ ምርትን የመሸጥ ፍላጐት ጥንታዊ ከበርቴዎች በንግድ ላይ ባለው ገደብ ከፊውዳሉ ጋር ተጋጩ ። ስለሆነም ከገደቦች ነጻ የመው ጣት ሀሳብ እንበልም ግብርን የመወሰን እና ሌላም ምክን ያቶች መጡ ። ይህን ያደረገው ካፒታሊስት ሕብረተሰብ



አይደለም ። ግን የካፒታሊስት ሕብረተሰብ መነሳሳት ሁኔ ታዎችና ከዚህም ካፒታላዊ አስተያየቶች ስለመጡ ነው ።

ሀሳቦች ምንም ከቁሳዊ ሁኔታዎች የሚመነጩ ቢሆ ኑም ከመነጩ በኋላ በሰዎች ተግባር ላይና በነገሮች ሂደት ላይ ተጽዕኖ ያሣድራሉ ። በአሮጌው የምርት ሥልት ላይ የተመሠረቱ ሀሳቦች ወግ አጥባቂ ናቸው ። የሰዎችን ተግ ባር ይገቶታሉ ። እናም ለዚህ ነው በየጊዜው የሚገኝ ገዥ መደብ እነኝህን ሀሳቦች ለማስተማር የሚችለውን ሁሉ የሚአደረግ ። ግን በአዲሱ የምርት ሥልት ላይ የተመሠረቱ ሀሳቦች ተራማጅ ናቸው ። ወደአዲሱ ሥርዓት ለማምራት የሚአስችሉ ተግባሮችን ያጠናክራሉና ። እናም ለዚህ ነው የገዥው መደብ አደገኛ ብሎ የሚወስዳቸው ፤ የሚአወግ ዛቸው ። ስለዚህ የዋጋን ተመን ለመጠበቅ ሲባል ምግብን የማጥፋትና የማበላሸት ሥርዓት አመለካከት (ግማሹ ረሀብ ኞች በብዛት እያሉ ፣) የገማ እና አደገኛ አስተያየት ነው ። ይህም ስለሆነ ተጻራሪ ሀሳብ ምርት ለትርፍ ሳይሆን ለጥቅ ም ፤ ለብሎት እንዲአመራ ወደሶሻሊስትና ኮሚኒስት ፓርቲ ዎች መደራጀት (አዲሱን ሥርዓት ለማምጣት ሥራ ላይ ወዳሉት) እንዲሄድ ያደርጋል ።

የማርክሲስቶች የሕብረተሰብ ዕድገት ጽንሰ — ሀሳብ (ታሪካዊ ቁስአካልነት የሚባለው) የቁስ አካላውያን «ወሳ ኝነት» አይደለም ፤ ማለትም የሰው ተግባሮች ንድፈ ሀሳብ በፍጹም ሊወሰኑ የሚችሉት በአካባቢአቸው ባለው ቁሳዊ ዓለም ነው ። እንዲያውም የሰው ተግባሮችና እነኝህ ተግባ ሮች የሚአስገኟቸው ቁሳዊ ለውጦች በከፊል ከሰውዬው ውጭ የሆነው ቁሳዊ ዓለምና በከፊል ደግሞ ቁሳዊ ዓለምን እንዴት እንደሚቆጣጠር ያለው ዕውቀቱ ውጤት ነው ። ግን ይህንን እውቀት በመጀመሪያ ሊአገኝ የሚችለው ቀዳ

ሚ በሆነው በቁሳዊ ዓለም ገጠመኝ ነው ። ሰው የቁሳዊውን
ዓለም ገጠመኝ የሚአገኘው በስውር መንገድ ወይም በወን
በር እንደ ተቀምጠ ሳይሆን ለሕይወቱ የሚአስፈልጉትን
ነገሮች በማምረት ነው ። እናም ዕውቀቱ በጨመረ ቁጥር
ልዩ የምርት ዘዴዎችን በአገኘና በተጠቀመባቸው ቁጥር ፤
የአሮጌው ሕብረተሰብ አደረጃጀት መልኮች አዲሶችን
ሙሉ በሙሉ እንዳይጠቀምባቸው እንቅፋት ይሆናሉ ።
ካለው ዕለታዊ ተግባር በመረዳት የተመዘበረው ሕዝብ
ይህ ግልጽ ይሆንለታል ። ትግሉም በመጀመሪያ ልዩ ከሆኑ
መጥፎ ድርጊቶች ፤ ልዩ ከሆኑ የአሮጌው ሕብረተሰብ አደራ
ጃጀት ከአመጣቸው ዕንቅፋቶች ጋር ይሆናል ። ግን በማይ
ቀር ሁኔታ አሮጌውን ሥርዓት ለመለወጥ ወደ አጠቃላይ
ጦርነት ይለወጣል ።

እስከተወሰነ ደረጃም ቀድሞ ባልተወሰነና ይሆናል
ተብሎ ባልታወቀ ሂደት አዲሶች የምርት ኃይሎች ከአሮ
ጌው ይገኛሉ ፤ እንዲህም ከሆነ ትግሉም አሮጌውን ሥር
ዓት ለማቆየት ከሚታገለው የሕብረተሰብ አደረጃጀት ጋር
ይሆናል ። ይህም እንዲሆን አሮጌዎቹ የመደብ ግንኙነቶች
አዲሶቹን የምርት ኃይሎች ሙሉ በሙሉ በተግባር ላይ
እንዳይውሉ ሲከላከሉና ሲአግዱ የሚታዩበት ጊዜ ይመ
ጣል።በዚህ ጊዜ ነው የወደፊቱን ኑሮ በጁ ጨብጦ ያለው
አዲሱ መደብ የንቃት ድርጊቱን ሚና መድረክ ላይ የሚ
አወጣው ።

ስለዚህም እያደገ የሚሄደው የምርት ኃይል ሂደት
ከዚህ በኋላ ያለንቃት እና ያለዕቅድ አይሄድም ። ወደሚቀ
ጥለው ደረጃ በንቃትና በዕቅድ ለመሸጋገር እና ምርትም
በንቃትና በዕቅድ የሚመረትበት ሕብረተሰብ ለማቋቋም



ሰው በቂ ገጠመኝ ፤ ስለሕብረተሰብ ዕድገት ሕግ በቂ ዕው
ቀት አጠራቅሟል ። ኤንግልስ ስለዚህ ደረጃ እንዲህ ይላል፦

«ከዚህ በፊት ታሪክን ገዝተውት የነበሩት ነባራዊና
ውጫዊ ኃይሎች ከእንግዲህ የሚተላለፉት በሰዎች ተቆጣ
ጣሪነት ነው ። ሰዎች ከዚህ ነጥብ ላይ ብቻ ነው በሙሉ
ንቃት የራሳቸውን ታሪክ የሚቀርጹት ፤ የሚአሟሉት» ።

ምዕራፍ ፫

# የካፒታሊስት ሕብረተሰብ

የማርክስ ብዙው ሕይወቱ የአለቀው ካፒታሊዝምን
ለማጥናት በአደረገው መስዋዕትነት ነው ። በብሪቴን ፊው
ዳሊዝምን ስለተካው በመላው ዓለም ባለፈው ምዕተ ዓመ
ት ራሱን ስላስፋፋው ሥልተ ምርት ማለት ነው ። የጥናቱ
ዋና ዓላማ የካፒታሊስት ሕብረተሰብን የእንቅስቃሴ ሕግ
ለማግኘት ነበር ። ካፒታሊዝም ሁልጊዜም አልኖረም ፤
ግን ቀስበቀስ አድጓል ። በ18ኛው ምዕተ ዓመት በብሪቴን
እንደነበረው የኢንዱስትሪያል አብዮት ጊዜና በማርክስ
ዘመን የነበረው አንድ አልነበረም ። ችግሩ ለማርክስ በእ
ርሱ ጊዜ ስለነበረው የካፒታሊስት የአመራረት ስልት መግ
ለጹ ሳይሆን ፤ ነገር ግን ለምንና በምን አቅጣጫ እንደሚለ
ወጥ መተንተኑ ነበር ። ለጥያቄው ይህ አቀራረብ አዲስ
ነው ። ሌሎች ጸሐፊዎች በኢኮኖሚ ጥያቄ ላይ ካፒታሊዝ
ምን እንዳለ በመውሰዳቸው ቋሚ ዘላለማዊ ሥርዓት አድ
ርገው ገልጸውታል ። ለማርክስ ግን ፤ ይህ የምርት ዘዴ በታ

ሪክ እንደታዩት ሌሎች ሥርዓቶች ሁሉ ተለዋጭ ነበር ።
የዚህ ውጤትም የገለጸም ጉዳይ ብቻ አልነበረም፤የማይንሳዊ
ትንተና ነጸብራቅም ነው።ምክንያቱም ካፒታሊዝም የሚዳ
ብር የሚአድግበትንም መንገድ ጭምር ለማየት ስለቻለ ።

የፊውዳል ምርት አመራረት ለካፒታሊዝም ዓይነ
ተኛ መልክ ለሆነው ለትርፍ ምርት ቀስበቀስ መንገድ ከፈ
ተ ፤ ምርት ለትርፍ ሁለት ነገሮች ያስፈልጉታል ። —

1. የምርት መገልገያዎችን ለመግዛት በቂ የገቢ
ምንጭ ያለው (ሞተሮች ፣ ማጠንጠኛዎችና ሌላ ሌላም)
፪. ለራሳቸው የምርት መገልገያ የሌላቸውና ራሳቸውን
ለመናር የሚአስችላቸው የጉልበት ኃይል ያላቸው። በሌላ
አነጋገር የምርት መገልገያዎች ባለቤቶች የሆኑ ከበርቴ
ዎችና ለመናር ሲሉ ብቻ በከበርቴው ባለቤትነት ሥር
ባሉት ማሽኖች የመሥራት ዕድል ያላቸው ሠራተኞች ።

ሠራተኞች ያመርታሉ ፤ ግን ለራሳቸው በቀጥታ ለሚ
ጠቀሙበት ወይም ለአዲሱ ጌታቸው (ካፒታሊስት) ለዕለ
ታዊ ፍላጐቱ የሚገለገልበት ሳይሆን ፤ ካፒታሊስቱ ለገን
ዘብ እንዲሸጠው ነው ። ዕቃዎች ለዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲሠሩ
ሸቀጥ ይባላሉ ። ማለትም ዕቃዎች ለገበያ ሽያጭ ሲመረቱ።
ሠራተኛው «ምንዳዕ» ይቀበላል ። ቀጣሪውም ትርፍ ።
ይህም «ደምበኛ» ለሸቀጦች ከፍሎ የሚቀረውና ከበርቴው
ለምንዳዕ ፤ ለጥሬ ዕቃዎችና ሌላም ለምርት አስፈላጊ ወጭ
ዎች ወጥተው ቀሪው ነው ።

የዚህ ትርፍ ምንጩ ምንድነው ? ማርክስ ሲጠቁም ፤
ካለው ዋጋ (እሴት) በላይ ተሸጦ ከካፒታሊስቱ ሊገኝ የሚ
ችል አይደለም ። ነው ካልንም ከበርቴዎች ሁልጊዜም



እርስ በእርሳቸው ሲተላለሉ ኖረዋል ፤ እናም አንዱ ትርፍ
ሲአገኝ ሌላው ከስሯል ፤ ከዚያም ትርፍና ኪሣራዎች አንዱ
አንዱን እርስ በእርሳቸው እየተጠፉፉ አጠቃላይ የሆነ
ትርፍ ሳያስገኙ ቀርተዋል ማለት ነው። ይህንም አስመል ከቶ
የአንድ ዕቃ ዋጋ (ዕሴት) በገበያ ላይ ትርፉንም በውስጡ መያ
ዝ አለበት የሚል ማጠቃለያ ይመጣል ። ግን አይደለም ፤
ትርፍ የሚገኘው ዕቃው ሲመረትና በሚመረትበት ወቅት
እንጂ ምርቱ በሚሸጥበት ጊዜ አይሆንም ፥ ሆኖም አያውቅ።

ስለዚህ ጥያቄው የሚአመራው ስለምርት ሂደት መመ
ራመር እንበልም በምርት ውስጥ ዋጋን (እሴትን) ከራሱ በላይ
ተመን ሊጨምር የሚአስችል ፀባይ እንዳለ ማየት ላይ ነው ።

መጀመሪያ ዋጋ (እሴት) ምን እንደሆነ መጠየቅ አስ
ፈላጊ ነው ። በተለምዶ አነጋገር ዋጋ (እሴት) ሁለት የተለ
ያዩ ትርጉሞች አሉት ። ዋጋ ስንል ለአንድ ሰው መጠቀ
ሚያ ነው—የተጠማ ሰው «ዋጋ» የሚሰጠው መጠጥን
ሲሆን ፥ አንድ ነገር ለአንድ ሰው « ስሜታዊ ዋጋ » ይኖ
ረው ይሆናል ። ነገር ግን በተለምዶ አጠቃቀም ሌላም ትር
ጉም አለው የአንድ ዕቃ (ነገር) በገበያ ላይ በአንድ ሻጭና
በሌላ ገዥ በሚካሄደው ያለው ዋጋ ነው ። እንበልም « የል
ውውጥ ዋጋ » የሚባለው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት እንኳ የተለዩ ዕቃዎች ለተወ
ሰኑ ገዥዎች ሊመረቱ እንደሚችሉና የተለዬ ተመንም
እንደ ሚዘጋጅ እርግጥ ነው ። ነገር ግን ማርክስ ብዙውን
የተመለከተው የካፒተሊስትን ምርት ነው ፡— የተለያዩ
በሚሊዮን የሚቆጠሩ ምርቶች በአጠቃላይ ለገበያ ለማንኛ
ውም ገዥ የሚመረቱበትን ሥርዓት ነው ። የምርቶችን
ጤነኛ የልውውጥ ዋጋቸውን በገበያ ላይ የሚአስገኘው መን

ድነው ? ለምን ነው ለምሳሌ አንድ ያርድ ልብስ ከወረቀት
መርፌ ይልቅ ይበልጥ የልውውጥ ዋጋ የሚኖረው ?

የልውውጥ ዋጋ የሚለካው በገንዘብ ነው ፤ — ይህም አንድ ዕቃ ይህን ያህል ገንዘብ ያወጣል ስለሚባል ። በቀጥታ ልውውጥም ይሁን ወይም በገንዘብ ነገሮችን እርስበእርሳቸው በዋጋ እንዲመጣጠኑ የሚያስችለው ምንድነው ? ማርክስ ሲናገር በዚህ ዓይነት ነገሮች ሊመጣጠኑ የሚችሉት ለሁሉም አንድና የጋራ የሆነ ነገር ሲኖር ብቻ ነው ። ማለትም በአንዳንዶቹ የበለጠ በሌሎች ያነሰ ነገር ሲኖር ማነጻጸር ይቻላል ። ይህ የጋራ ጠባይ እንደዕውነቱ ከሆነ ክብደት ወይም ቀለም ወይም ሌላ ግዝፈታዊ ጸባይ ወይም ደግሞ ለሰዎች ያለው « የጠቀሜታ ዋጋ » (Use value)—ምክንያቱም አስፈላጊ ምግቦች ከመኪኖች ይልቅ አነስተኛ ልውውጥ ዋጋ አላቸውና (ወይም ሌላ ምስጢር (ሰውር) (Abstruct) ጸባይ አይደለም ።ለሁሉም ምርቶች የጋራ የሆነ ጸባይ አለ፤ ይኸውም በሰው ጉልበት መመረታቸው ነው ይላል ። አንድ ዕቃ ብዙ የሰው ጉልበት ከፈሰሰበት ላቅ ያለ የልውውጥ ዋጋ ይኖረዋል። የልውውጥ ዋጋ የሚወሰነው ዕቃውን ለማምረት በጠፋው የሥራ ጊዜ (Labour time) ነው ።

እንደዕውነቱ ከሆነ የአንድ ግለሰብ የሥራ ጊዜ አይደለም ። በአንድ አጠቃላይ ገበያ ላይ ዕቃዎች ሲሸጡና ሲገዙ የልውውጥ ዋጋቸው እንደነጠላ ምርት ( እንደግለሰብ ምርት) ( Individual production )አማካይ ዋጋ ይወጣለታል ። እናም አንድ የተወሰነ ክብደትና ዓይነት ያለው ልብስ (በያርድ) የልውውጥ ዋጋው የሚወሰነውምርቱን ለማምረት በሚጠይቀው « የሕብረተሰቡ አማካይ የሥራ ሰዓት » ነው ። ( Average Socially necessary Labour time)



በካፒታሊዝም ውስጥ ስለሚመረቱት ምርቶች አጠቃላይ መሠረታዊ የልውውጥ ዋጋ እንዲህ ከሆነ ዕቃዎችን ለሚአመርተው ሠራተኛ የሚከፈለውን ምንዳዕ የሚወስነው ምን ነው ? ማርክስ ጥያቄውን በአጭሩ እንደበራቱ ነው ያስቀመጠው ፤ — በገበያ ላይ የልውውጥ ዋጋ ያላቸው የጉልበት ኃይልና በሚመርተው ምርት መካከል (በካፒታሊዝም) የጋራ የሆነው መለኪያ ጸባይ ምንድነው ? ይላል ። ከዚህ በፊት ካየነው ሌላ ጸባይ የለም ፤ እንበልና የልውውጥን ዋጋ ከሚወስነው ፤ እርሱን ለመሥራት ከሚፈጀው የሥራ — ጊዜ በቀር ። የጉልበትን ኃይል ለማምረት የሚጠፋው የሥራ — ጊዜ ማለት ምንድነው ? ምግብን ፤ መጠለያን ፤ ልብስንና ሌላም ሠራተኛውን ከዕለት ወደዕለት እየተዳከመ ከመሄድ የሚጠብቁትን ነገሮች ለማምረት የሚጠፋው ጊዜ አማካይ ሕብረተሰባዊ አስፈላጊ ጊዜ ነው። (Average Socially Necessary time) በማንኛውም የካፒታሊስት ሕብረተሰብ የሠራተኛውን ቤተሰብ ለመጠገን የሚአስችሉ አስፈላጊ ነገሮች በደንብ መጤን አለባቸው ። እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማምረት የሚአስፈልገው የሥራ ጊዜ ለከበርቴው የሚሸጠውን የሠራተኛውን የሥራ —ኃይል የልውውጥ ዋጋ ይወስነዋል ።

ግን በአንድ ዘመናዊ የከበርቴ ሕብረተሰብ ውስጥ የሠራተኛውን የሥራ — ኃይል ለመጠገን የሚጠፋው ጊዜ አራት ሰዓት ይሆን ይሆናል ፤ ይሁንና ሠራተኛው ለሥራ የሚአጠፋው በቀን ስምንት ወይም አሥር ሰዓትና ከዚያም የበለጠ ነው ። ስለዚህ በየቀኑ ለመጀመሪያዎቹ አራት ሰዓት ለእርሱ በምንዳዕ መልክ የሚከፈለውን ያህል እኩል የሚሆን ያመርታል ፤ በቀሪው የሥራ ሰዓቱ ግን ቀጣሪው የሚበዘብዘውን ትርፍ «ዕሴት» ነው የሚአመርተው ። የካፒታሊስቱ ትርፍ ምንጩ ይኸነው — ሠራተኛው እርሱን ለመ

ጠገኛ ከሚውለው ዋጋ (ዕሴት) በላይ የሚአመርተው ዋጋ
(ዕሴት) — እንበልም የሚቀበለው ምንዳዕ ።

ይህ በማርክስ ስለ ዋጋ (ዕሴት) እና ስለ ትርፍ ዋጋ
(ዕሴት) የተሰጠው አጭር የማብራሪያ ትንታኔ በብዙ መን
ገድ ትክክል መሆኑ እንዲረጋገጥ ያስፈልጋል ። ቢሆንም
ሁሉንም መልኮች ለመግለጽ ቦታ አይበቃም ። ይሁንና
ከአጠቃላዩ ነጥቦቹ ጥቂቶቹ ይጠቆማሉ ።

«የልውውጥ ዋጋ» የሚለውን ሐረግ የተጠቀምነው
ምክንያቱም የትንታኔአችን መሠረት ስለሆነ ነው ። በዕው
ነት ከሆነና በየጊዜው እንዳየነው ዕቃዎች ልክ በልውውጥ
ዋጋ ቻው አይሸጡም ። ቁሳዊ ምርቶችም ይሁን የሰው የጉ
ልበት — ኃይል የሚሸጡና የሚገዙት በገበያ ላይ ከትክክ
ለኛው የልውውጥ ዋጋ በላይ ወይም በታች በሆነ ተመን
( Price ) ነው ። አንድ የተለየ ምርት በገበያ ላይ
በብዛት ሊቀርብ ይችል ይሆናል ፤ እናም በዚያን ቀን ተመኑ
ከትክክለኛው የልውውጥ ዋጋ በታች ወይም እጥረት ካለ
ተመኑ ከዋጋው በላይ መሆን ይችላል ። ይህ የተመን መዋ
ለል ተጽዕኖው የሚመጣው ሸቀጡን «በማቅረብና በመጠ
የቅ» (Supply and Demand) ላይ ያለ ሁኔታ ነው ። ይህም
ብዙ ካፒታሊስት ኢኮኖሚስቶችን የተመንን ሁኔታ የማቅ
ረብና የመጠየቅ ነገር ነው የሚወስነው እንዲሉ ረድቷቸ
ዋል ። እርግጥ እስከተወረሰነ ደረጃ ድረስ የማቅረብና የመ
ጠየቅ ሁኔታ ለመዋለል ምክንያት ይሆናሉ ። ደረጃው
አንድ ሳንቲም ትሁን ወይም መቶ ብር በግልጽ በሚቀርበ
ውና በሚጠየቀው አይደለም የሚወሰነው፤ዕቃውን ለማ
ምረት በጠፋው የሥራ ጊዜ እንጂ ።



ትክክለኛው የጉልበት ኃይል ተመንም በሚከፈ
ለው ምንዳዕ ፤ በሚጠየቀውና በሚቀርበው ሸቀጥ ተጽዕኖ
ይደርስበታል ። ተጽዕኖው በሌሎች ጸባዮችም ሊሆን
ይችላል ። ለምሳሌ — በተለይም በሙያ ማህበሮች
ጥንካሬ ፤ ይሁንና በማንኛውም የካፒታሊስት ሕብረ
ተሰብ ውስጥ የጉልበት ኃይል ተመን በተወሰነ ደረጃ
ሲዋልል ይታያል — ይህም ቀደም ብለው ትግል በማካሄድ
የመነሻ ክፍያውን በመሥራታቸው ምክንያት የተለያዩ
ደረጃና ቡድን በፈጠሩት የሙያ ማህበሮች ሊመጣጠን የሚ
ገባው የሠራተኛው ሕልውና መጠበቂያ ፤ የተለያዩ ቡድኖ
ችና ደረጃዎች ፍላጎት የተለያዩ ሁኔታ ስለሚኖር ተመኑም
በዚሁ በተለያዩ ደረጃ ለመመጣጠን ላይና ታች ማለቱ
ነው ።

በተለያዩ ደረጃ ባሉት ሠራተኞች ላይ ያለው የጉልበት
— ኃይል እንደዕውነቱ ከሆነ ከዋጋ (ዕሴት) ተመሳሳይ
አይደለም ። ብዙ ልምድ ያለው አንድ ኢንጂኔር የአንድ
ሰዓት ሥራ ከአንድ ልምድ ከሌለው ሠራተኛ የአንድ ሰዓት
ሥራ ይልቅ ብዙ ዋጋ ሊያመርት ይችላል ። ማርክስ እንዳ
ሳየው — ልምድ ያለውና ልምድ የሌለው ሠራተኛ የአ
ንድ ሰዓት ምርት ውጤት ያላቸው የተወሰነ ግንኙነታቸው
ተመዝግቦ በገበያ ላይ ሸቀጣቸው ሲቀርብና ሲሸጥ በመካ
ከላቸው ያለው ልዩነት ይከሠታል ።

ይህ ልዩነት እንዴት ነው በዋጋ (ዕሴት) ላይሊወጣ
የሚችለው ? ማርክስ እንዲህ ይላል ፡— በአንድ በተወሰነ
«መርህ» ወይም ሥውር አስተሳሰብ አይደለም ልምድ ያለ
ው ሠራተኛ ልምድ ካጣው ሠራተኛ የሚበልጠው ። እው
ነቱ ነገር ፤ ልምድ ያለው ሠራተኛ የጉልበት ኃይል ልምድ
ከሌለው ሠራተኛ የጉልበት ኃይል የበለጠ የልውውጥ ዋጋ

(ዕሴት) ስለሚፈጥረው ነው ። የእንፋሎት መርከብ በመቅ
ፊያ ከሚቀንቀሳቀስ ጀልባ ይበልጥ ጥቅም እንዳለው ሁሉ ።
ምክንያቱም የእንፋሎት መርከብ ለመሥራት ብዙ የሰው
ጉልበት ስለሚፈስበት ። ልምድ ያለው ሠራተኛ ለማ
ልጠን ካለው ሂደት ሌላ በተጨማሪም ለልምዱ እስፈላጊ
የሆነውን ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ለማስገኘት ብዙ ጉልበት
እንዲጠፋበት ያሻል (Intensified Labour) ። ሌላ ማስታወስ
ያለብን ነጥብ ፡— በፊት ከሚአስፈልገው እማካይ በላይ
በተወሰነ ጊዜ የሰው ጉልበት ቢታፈግና ቢጨመር ፤ ከረዥም
የሥራ ሰዓት ጋር ዕኩል ይሆናል ። በስምንት ሰዓት ውስጥ
የታፈገ ጉልበት የሚመረት ምርት በፊት በመጠነኛ ጉል
በት የሚሠራውን የአሥርና የአሥራሁለት ሰዓት ምርት
ዕኩል ይሆናል ።

የትርፍን ምንጭ ለማሳየት በማርክስ የተደረገው ትን
ተና ዋናነት ምንድነው ? በካፒታሊስቱ ጊዜ ያለውን የመ
ደብ ትግል ይገልጻል ፤ ያብራራል ። በየአንዳንዱ ፋብሪካ
ወይም ድርጅት ውስጥ ለሠራተኞች የሚከፈለው ምንዳዕ ፤
ሠራተኞች ከሚአመርቱት ምርት ዋጋ (ዕሴት) ጋር ተመ
ጣጣኝ አይደለም ። ነገር ግን ካለው ዋጋ (ዕሴት) ግማሽ
ወይም በታች ቢሆን እንጂ ። ሠራተኛው በሚሠራበት ቀን
የአመረተው ቀሪ ምርት ግን (ማለትም እራሱን ለመደገፍ
ከሚአመርተው ውጭ ያለው) በቀጥታ በቀጣሪው ይወሰ
ዳል ። ስለዚህ ቀጣሪው በየቀኑ ከሠራተኛው ላይ የሚወሰ
ደውን በማያቋርጥ ሁኔታ ለመጨመር ይሞክራል ። ይህ
ንም በተለያየ መልክ ያሳያል ፡— ለምሳሌ የሠራተኛውን

ምንዳዕ በመቀነስ ። ይህም ማለት ሠራተኛው ለራሱ
የሚሆነውን ምርት የሚአመርተው ካለው የሥራ ቀን በጣም
በአነስተኛው ጊዜ እንዲሆንና ብዙውን ለቀጣሪው እንዲ



አመርት ሲደረግ መሆኑን ነው ። ይህንን ሁኔታ ለማስገኘት
«ሥራ በማፋጠን» ወይም ጉልበትን በማፈግ እንበልም
ሠራተኛው በጥቂት ጊዜ ውስጥ ለራሱ መጠገኛ እንዲአመ
ርትና ለረጅም ሰዓቶች ለቀጣሪው እንዲሠራ ይሆናል ።
ይህንኑ ውጤት ለማስገኘት የሥራ ቀኑን ማራዘም ነው ።
ይህ ደግሞ ለቀጣሪው የሚሠራውን የሥራ ቀን በጣም ከፍ
ያደርገዋል ፤ የዚያኑም ያህል ምርቱን ። በሌላ መንገድ ፡—
ሠራተኛው ያለውን ደረጃ ለማሻሻል ለከፍተኛ ምንዳዕ ፤
ለአጭር የሥራ ሰዓት ይታገላል ። እንደገናም« ሥራን ማፋ
ጠን» የሚለውን መርህ በመቃቃም ይቃወማል ።

እናም በዚህ ምክንያት የካፒታሊስት ሥልተ —
ምርት ካልጠፋ በቀር ሊጠፋ የማይችል የማይቋረጥ ትግል
በከበርቴውና በሠራተኞች መካከል ይካሄዳል ። ይህ ትግል፤
በአንድ ግለሰብ ሠራተኛ ወይም በሠራተኛ ቡድኖችና በግ
ለሰብ ቀጣሪ መካከል በመነሣት ቀስ በቀስ ይስፋፋል ።
በሌላ በኩል የሙያ ማኅበሮች በእነሱ አንጻር የቀጣሪዎች
ድርጅቶች ከየራሳቸው መደብ የሕዝብ ክፍሎችን በማም
ጣት ይቆራቆሳሉ ። በመጨረሻም ፤ የሠራተኞች የፖለቲካ
ድርጅቶች ይመሠረታሉ ። ሲስፋፋም የኢንዱስትሪ ሠራ
ተኞችንና የሕዝቡንም የተለያዩ ክፍሎች በመቀስቀስ በከ
በርቴው መደብ አንጻር አቁመው ያፋልማሉ ። የመጨረሻ
ነቁጡን ሲደርስ ይህ ትግል አብዮት ይሆናል — የከበር
ቴው መደብ መወርወርና በምትኩ ሠራተኞች የሚሠሩብ
ትን የሥራ ቀን ከፊሉን ወይም ይበልጡን ለሌላ መደብ
ጥቅም ሳይሆን ለራሣቸው ላባቸውን የሚአፈሱበት አዲስ
የአመራረት ሥልት መቋቋም መሆኑ ነው ። ይህ ነጥብ በይ
በልጥ በሚቀጥሉት ምዕራፎች ተብራርቷል — ማስታወስ
ያለብን ዋናው ነገር በካፒታሊዝም ውስጥ ያለው የመደብ
ትግል የሚነሣው በራሱ በካፒታሊስቱ የምርት ሥልት

ባሉት ጠባዮች ነው — በሁለቱ መደቦች መካከል በምርት
ሂደት ጊዜ በሚፈጠረው የማያቋርጥ ግጭት ምክንያት
ተጻራሪ በሆነው ፍላጐታቸው ነው ።

ምንዳዕንና ትርፍን ከተነተንን ዘንድ ካፒታልን በማጥ
ናት እናልፋለን ። በመጀመሪያ ሠራተኛው በሚአመርትበት
ጊዜ በሠራተኛው የሚፈጠረው «ትርፍ ዕሴት» በቀጣሪው
በሙሉ እንደማይያዝ ነው መገንዘብ የለብን ። እንናገር ፤
የተለያዩ የከበርቴ ቡድኖች በተለያዩ አቅጣጫ የሚወስዱት
ክፍያ (ድርሻ) ነው ። አባባሉ — መሬት ከበርቴው የመሬት
ኪራይ ፤ ባለባንኩ ወለድ ፤ የመካከለኛው ሰው (The Middle
Man) — ዕቃዎችን ወሣጅ መሆኑ ነው — የነጋዴነት
ትርፉን ፤ እና ዋና ባለኢንዱስትሪ ቀጣሪ ከዚህ ሁሉ የቀረ
ውን በትርፍነት ይወስዳል» ነው ። ይህ በፊት ያደረግነውን
ትንተና በምንም ዓይነት አያናቅፍም ። እነኝህ የተለያዩ
ካፒታሊስቶች ሁሉ ከላይ እንደጠቀስነው የሚጠፉውን
ነገር በመሃከላቸው ለመከፋፈል የሚአደረጉት የመረዳዳት
ትግል ነው ከማለት በቀር ። ግን ከሠራተኛው መደብ ላይ
የሚፈልጉትን ለማግኘት የተቻላቸውን ያህል ሁሉም ይተ
ባበራሉ ።

## ካፒታል ምንድን ነው ?

ብዙ አካላዊ መልኮች አሉት ፡— ማሺኖች ፤ ሕንጻ
ዎች ፤ ጥሬ ዕቃዎች ፤ ነዳጅ እና ለምርት የሚአስፈልጉ
ሌሎች ነገሮችም ፤ በተጨማሪም ምርትን ለማስመረት ለሚ
ከፈል ምንዳዕ የሚውል ገንዘብ ።

ይሁንና ማሺኖች ፤ ሕንጻዎችና ሌሎችም ወይም የገ
ንዘብ ድምሮች ሁሉ ካፒታል አይደሉም ። ለምሣሌ—አንድ
እነስተኛ ገበሬ ለመኖሪያ የሆነ ቤት ከቦታ ጋር ፤ ከብቶ



ችና የተለያዩ መሣሪያዎች ፤ አነስተኛ ገንዘብም ሊኖረው
ይችላል ። ግን እራሱ ባለቤት ከሆነና ሌላ ባለቤት ከሌለ
አንዱም ንብረቱ ካፒታል አይደለም ።

ንብረት (ምንም ዓይነት አካላዊ መልክ ቢኖረው) ካፒ
ታል ሊሆን የሚችለው ፤ በኤኮኖሚአዊ አስተሳሰብ «ትርፍ
ዕሴት» ለማምረት ስንጠቀምበት ነው ። አባባላችን ምር
ትን በሚአመርቱበት ጊዜ በተጨማሪም ትርፍ ዕሴት የሚ
አመርተውን ሠራተኛ ለመቅጠር ሲውል ነው ።

ይህ ዓይነት ካፒታል ምንጩ ፤ አመጣጡ እንዴት
ነው ?

ታሪክን ወደኋላ ቀለስ መለስ ብለን ብናይ ፤ የካፒታል
ጥንታዊ ክምችት ግልጽ የሆነ ዝርፊያ ነበር ። በወርቅ መል
ክ ብዙ መጠን ያለው ካፒታልና ውድ የሆኑ ነገሮች በአጉል
ጀብደኞች ከአሜሪካ ፤ ከሕንድና ከአፍሪቃ ተዘረፉ ። ካፒ
ታል ወደ ሕልውና የመጣበት በዚህ ዓይነት የዝርፊያ
መንገድ ብቻ አልነበረም ። በእንግሊዝ ተከታታይ« የከ
በባ ተግባር» ( Enclosure act ) ሂደት የተራውን ሕዝብ
መሬት ለካፒታሊስቶች ጥቅም ሲባል ወሰዱ (ነገሩን ከብ
ዶት ለመስጠት «ሰረቁት»)።ይህንንም በማድረግ ገበሬውን
የመኖሪያ መንገዱን ዘጉበት ፤ ስለዚህም ወደ ወዝአደር
ነት ለውጡት — ማለትም በተወሰደባቸው መሬት ላይ
ለአዲሱ የመሬት ባለቤት ተቀጥረው ከመሥራት በቀር ሌላ
የመኖር መንገድ የሌላቸው ሠራተኞች መሆን ፤ ወይም ሌላ
ቀጣሪ ከበርቴ መፈለግ ። ማርክስ ይህንን ነው ትክክለኛው
የካፒታል ምንጭ (ጥንታዊ ክምችት የሚባለው) ያለው ።
ከበርቴዎች በመሠረቱ ከድህነት ኑሮ የወጡ ርሕራሄ ያላ
ቸው ሰዎች ናቸው የሚለውን ተረታማ ታሪክ ማርክስ ነው

የሚፈዝበት ታሪክ መሆኑን ያሳየው ። ተረቱ የሚቀጥለው ነው ።

«ይህ ጥንታዊ ክምችት በፖለቲካ ኢኮኖሚ ላይም በቴዎሎጅ (በመንፈሳዊ) ትምህርት ላይ የሚጫወተውን ሃጢአት ይደግማል ይልና ማርክስ ተረቱን ይጠቅሳል—ከረጅም ጊዜ በፊት ሁለት ዓይነት ሕዝቦች ነበሩ ፤ አንደኛው ትጉህ ሠራተኞች፤ብሩህ አሳቢዎች ከዚያም በላይ ጠንቃቃ ፤ ቆጣቢ ፤ ሊቅ የሆኑ ፤ ያሉበት ፤ ሌላኛው — ሰነፎችና በልጣጮች ፤ ዕቃዎቻቸውን አውዳሚዎች እና በተጨማሪም ሕግ ጣሺና በጥባጭ ነዋሪዎች የሚገኙበት . . . . ስለዚህ የመጀመሪያዎች ሀብት አከማቹ ፤ የኋለኞቹ ግንየሚሸጡት ምንም ነገር አጡ ከቆዳቸው በቀር ። እናም ከዚህ መሠረታዊ ሃጢአት የብዙሐኑ ድህነት ቀን ተጀመረ— እስከአሁንም ድረስ ከጉልበቱ በቀር የሚሸጠው የለውም እራሱን እንጂ፤በየጊዜው እየጨመረ ሀብታቸው በማያቋርጥ ሁኔታ የሚሄደው ጥቂቶቹ ግን ይኸውና መሥራት ካቆሙ ብዙ ጊዜ አቸው ነው ። »ተረቱ ከዚህ በላይ ያለው ነው ። ግን ምን ያህል እውነት ነው ?

ይሁንና ካፒታል በጥንት ክምችት ደረጃ የሚቀር አይደለም ፤ በሚአስደንቅ ሁኔታ ደረጃው እየጨመረ ነው ። ምንም እንኳን የመጀመሪያው ካፒታል የቀጥታ ዝርፊያ ውጤት ቢሆንም ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እየተከመረ የመጣው ተጨማሪ ካፒታል ምንጩ ምንድነው ?

ሥውር ዝርፊያ (ዘወርዋራ — ኢ.ርቱዕ) ነው ይላል ማርክስ ። ለሕይወቱ ከሚአስፈልገው በላይ ሠራተኛውን ትርፍ ሰዓት እንዲሠራ በማድረግና በዚህ ተጨማሪ ሰዓት የሚሠራውን ምርት ዋጋ (ዕሴት) በመበዝበዝ የሚመጣ ነው ፡— «ትርፍ ዕሴት» የሚባለውን ። ከበርቱው የዚህን



ትርፍ ዕሴት ክፊሉን ለራሱ ያውለዋል ። ቀሪው እንደ አዲስ ካፒታል ይሆናል — ምን ለማለት እንደተፈለገ ግልጽ ይሁንና ፡— ከበፊቱ ካፒታል ጋር ያዳምረውና ብዙ ሠራተኞች ለመቅጠር ሲአስችለው ፤ በሚቀጥለው ምርት ላይ ይበልጥ ትርፍ ዕሴት (በተራው ተጨማሪ ካፒታል — በማያቋርጥ መከታተል ማለት ነው) እንዲአገኝ ያደርገዋል ። ማንን ? ካፒታሊስቱን ።

በማያቋርጥ ሁኔታ ይሄዳል ፤ ነገር ግን ሌሎችም ሕብረ—ሰብዕና ኢኮኖሚካዊ ሕጐች አብረው ይመጣሉ እንጂ ። ፍጹም ዋናው እንቅፋትና ከጊዜ ወደጊዜ አጠቃላዩን ሂደት የሚገትተውና በመጨረሻም የካፒታሊስትን ሥልተ ምርት አደንዝዞ የሚአቆመው የመደብ ትግል ነው ። ካለው ሥርዓት የሚመነጩና የካፒታሊስትን ጤናማ ዕድገት የሚአናቅፉ ሌላም ብዙ እንቅፋቶች አሉ ።

ባለፈው ጊዜ የተከማቸውን ካፒታል በከፊል ወደሚአፈራርስ ሁኔታ የሚመራ ኢኮኖሚ አዊ ቀውስ ይፈጠራል። ይህም የካፒታልን መጨማተር ያረጋግጣል ። «በእንኘህ ቀውሶች» ይላል ማርክስ(Communist Manifesto)« ባለፉት ዘመናት ሁሉ ፈገ ይመስል የነበረው ወረርሽኝ አጥሩን ሰብሮ ወጣ — ከሚፈለገው በላይ ትርፍርፍ የምርት ወረርሽኝ ፡፡» በመልከኛው ሥርዓት ፡— ብዙ ትርፍርፍ የስንዴ ምርት ሲባል ፤ ለሁሉም ተጨማሪ ምግብ ማለት ነበር ። በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ግን ለሠራተኞች ርሀብና ፤ ከተቀጠሩበት መባረር ነው ። ምክንያቱም ስንዴው ለሽያጭ ነውና የሚቀርበው ሳይሸጥ ቢቀር ለሚቀጥለው ዓመት አንስተኛ ስንዴ ነው የሚዘራው ።

በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል የካፒታሊስት የቀውስ ገጾች የተለመዱ ሆነው ነበር ፡ ከሚፈለገው በላይ

አዲሱ ምርት አሽቆለቆለ ፤
ምርት ነበርና ፣ ስለሆነም — አዲሱ ምርት አሽቆለቆለ ፤
ምርት ነበርና ፣ ስለሆነም — አጥ መሆን
ሠራተኞች ሥራ አጥሆኑ ፤ የሠራተኞች ሥራ — አጥ መሆን
ማለት በገበያ ላይ የምርት ተጠያቂነት ማሽቆልቆል ነው ።
ስለዚህ ብዙ ፋብሪኮች ምርትን ይጐትታሉ ፤ አዳዲሶች
አይቋቋሙም ፤ እንዳንድቹም ይበለሻሻሉ ። ስንዴና ሌሎች
ምርቶች ተበላሹ ፤ ስለሆነም ሥራ—አጦችና ቤተሰቦቻ
ቸው በበሽታና በርሃብ ተገረፉ ። የእብድ ሰው ዓለም መሆኑ
ነው ። በመጨረሻ ላይ ከምቾት (የምርት) በጥቅም ላይ
ዋለ ወይም ጠፋ (ተበላሸ) ፤ ምርት መጨመር ያዘ ፤ ንግድ
እደገ ፤ ብዙ የሰዎች ቀጠራ ተካሄደ ፦— ለሁለትና ለአንድ
ዓመት ያህል ያልተቋረጠ ማገገም ተገኘ ። ይህም ግልጽ
ወደሆነ ድንበር የለሽ የምርት መስፋፋት አመራ—እንደገና
በድንገት ከሚፈለገው በላይ የምርት ቀውስ እስከሚመጣና
ያለፈው ድርጊት እስከሚደገም መሆኑ ነው ።

የነዚህ ቀውሶች ምክንያት ምንድነው ? ማርክስ እን
ዲህ ይላል ፡ እያንዳንዱ የካፒታሊስት ክበብ ለመስፋፋት
በሚአደርገው ትግል የሚመጣ የካፒታሊስት ምርት ሕግ
ነው ፡ — ብዙ ትርፍ ለማግኘት ። እናም ስለዚህ ብዙ ለማ
ምረትና ብዙ ለመሸጥ ፡ የበለጠ ካፒታል በተገኘ ቁጥር
ብዙ ምርት ይመረታል ፡ ከዚሁ ጋር ብዙ ካፒታል ቢኖ
ርም አነስተኛ የጉልበት — ኃይል ይቀጠራል — የሰዎችን
ቦታ ማሺኖች ይተኩታል (የኢንዱስትሪዎች እንደገና የሰ
ውን ጉልበት በመቀነስ መሻሻል መሆኑ ነው) ። በሌላ አነጋ
ገር ፤ ካፒታል ሲበዛ ብዙ ምርት ይኖርና አነስተኛ ምንዳዕ
ይከፈላል—ስለዚህም አነስተኛ የምርት ተጠያቂነት ይኖ
ራል ፡ እዚህ ላይ መጤን ያለበት የምንዳዕ ፍጹም ጠቅላላ
መውደቅ እንዳልሆነ ነው ፦— ብዙውን ጊዜ ቀውስ የሚመ
ጣው ከአንጻራዊ ውድቀት ነው — ማለትም ጠቅላላ ምን
ዳዕ ድንገተኛ ጭማሪ ሊአሳይ ይችላል ፤ ይሁንና ከአጠቃ



ላዩ ምርት ሲነጻጸር አነስተኛ ነው ፤ ስለዚህም ተጠያቂነት
(የሸቀጥ) ከውጤቱ የወረደ ይሆናል ።

ይህ በካፒታል መስፋፋትና በአንጻሩ የሠራተኞች
ጥያቄ መታፈን መካከል ያለው አለመመጣጠን ዋናው የቀ
ውስ ምክንያት ነው ። ነገር ግን ወዲያውኑ የቀውሱ ግልጽ
መሆንና የሚዳብርበት መንገድ መታወቅ የተለዩ ምክንያ
ቶች ላይ ሊንተራስ ይችላል ። ምሳሌ ለመውሰድ — ከ 1950
ዓ.ም. ጀምሮ ዩናይትድ ስቴትስ ባካሄደችው የትልልቅ ጦር
መሣሪያዎች ምርት የቀውሱ ሁኔታ እስከሚዳብር ድረስ
በከፊል ሊደበቅ ችሎ ነበር ። ይሁን እንጂ ሌሎች ሁኔታ
ዎች ለምሳሌ የእርሻ ምርት ውጤቶችን መንግሥት በብዛት
ሲገዛ ወይም ለመፍጀት (ለብሎት) የሚውሉ ዕቃዎችን
በዱቤ የመውሰድ ማስፋፋትና የቀስ በቀስ ክፍያዎች ይከ
ሠታሉ ። ግን ከነዚህ ሁኔታዎች ወይም ጠባዮች አንዳ
ቸውም እንኳን ቀውሱን ከማስተላለፍ በቀር በምርትና
በብሎት መካከል ያለውን የልዩነት ጸባይ አይለውጡትም ።

ከዚህም ሌላ በካፒታሊዝም ዕድገት ውስጥ የሚከሠት
በጣም ዋና መለያ ጠባይ አለ ፦— ውድድር የሚባለው ።
በካፒታሊስት ምርት እንደሚታዩት ሌሎች ጠባዮች ሁሉ
ሁለት ተቃራኒ ውጤቶች አሉት ። በአንድ በኩል በውድ
ድር ምክንያት ከፍተኛ ሽያጭ ለማሸነፍ ሲባል እያንዳንዱ
የካፒታሊስት ድርጅት እያከታተለ የምርት ተመኖችን
ሊቀንስ ይሻል — በተለይም ደመወዝን በመቀነስ ፦— በቀ
ጥታ ምንዳዕን በመቀነስ ወይም ሥራን በማፋጠን የሚው
ጣውን የጉልበት — ኃይል በማሳነስ ። ይህን ለማድረግ
አዲሱ መልክ ማሺኖችን አውቶማቲክ ማድረግ ነው ።
በሌላ መንገድ ደግሞ አነስተኛ ድርጅቶች — በቂ ካፒታል

ለማግኘትና ቴክኒካቸውን ለማሻሻልና በአነስተኛ ጉልበት
ብዙ ለማምረት የሚፈልጉት ተቀንሶ በሚከፈለው ጠቅላላ
ምንዳዕ ምክንያት ለጥያቄ (Demand) ትንሳ አስተዋጽኦ
አቅማቸውን ያበረክታሉ ።

ይሁንና ፤ ቴክኒኩን የሚአሻሻለው ድርጅት ለጊዜው
ከፍተኛ ትርፍ ያጋብሣል — ተወዳዳሪዎቹ ተመሳሳይ ሁ
ታ እስከሚፈጠሩና በአነስተኛ ጉልበት እስከሚጠቀሙ
ድረስ መሆኑ ነው ። ግን ሁሉም ተወዳዳሪዎች አይሳካ
ቸውም ። የመወዳደሩ አማካይ ዕድገት እየጨመረ እየወ
መረ በሄደ ቁጥር ፋብሪካውን ለማሻሻል ከፍተኛ ካፒታ
እያስፈለገና ይህንኑ የሚአሟሉት ደግሞ በጣም እያነ
ይሄዳሉ ። ሌሎች ተወዳዳሪዎች ከግርግዳ ይጋጫሉ ፡
ይከሥሩና ወይ በትላላቅ ተወዳዳሪዎቻቸው ይወሰዳሉ
አሊያም ይዘጋሉ ። «አንድ ካፒታሊስት ብዙዎቹን
ይገላል» ። ስለዚህ በእያንዳንዱ የእንዱስትሪ ቅርንጫፍ
ያሉ የተለያዩ ተወዳዳሪዎች በተከታታይ ይቀንሳሉ — ይ
ዛም ይነስ የተወሰነን የኢንዱስትሪ መስክ የሚሸፍኑ ት
ልቅ የሕብረት ድርጅቶች (Trusts) ደግሞ ይመጣሉ
ስለሆነም ከካፒታሊስት ውድድር የርሱ ተቃራኒ የሆ
ካፒታሊስት ሞኖፖል ይገኛል ። በሚቀጥለው ምዕራፍ
የሚገለጸውን አዲስ ገጽና መልክ ያሳያናል ።

ምዕራፍ ፬

# የካፒታሊዝም የኢምፔርያሊስት ደረጃ

በታወቀ ትርጉም ፤ ኢምፔሪያሊዝም የመስፋፋት ማለትም ወደኋላ የቀሩ አገሮችን እያሸነፉ ወደግዛት የመቀላቀል ፖሊሲ ነው ። እስከ አሁን ድረስ ፖሊሲው እንደታየው ካለው ሥውር ምኞቱ ሌላ በተለያዩ ግዛቶች የሃገሩ ባንዲራ በተቻለ መጠን እንዲውለበለብ መፈለጉ ፤ የመስፋፋቱ ዓላማ ዋናው ኢኮኖሚያዊ ምክንያት እንደሆነ ያረጋግጣል ። እንዳንዴም እንዲህ ሊባል ይቻላል ፡ — ለምሣሌ — ምክንያቱ ፤ የገበያ ፍለጋ ነው ወይም ጥሬ ሀብትና ምግብ ወይም የራሳቸው ሕዝብ ተጨናንቆ ከሚኖርበት ቦታ ሌላውን በመዝረፍ መውጫና መተንፈሻ ለማግኘት ነው ።

ውጭ ሀገር በጣም ጥሩ የሆነ ገበያ ይኖረዋል ። ጥሬ ሀብቶችና ምግቦች ሁልጊዜም ከውጭ ሊቀርቡ ይችላሉ ። ግን ለመሬትና ለሠፈራ ሕዝብን ከገዛ ሀገሩ እንዲፈልስና በሌሎች ሰዎች ሀገሮች የመኖር ፍላጐት እንዲኖር የሚአነሳሳው ካፒታሊዝም የሚፈጥረው ሁኔታ ነው ፤ ታዲያ ምንድነው የኢምፔሪያሊዝም መስፋፋት ምክንያት ?

የመጀመሪያው ስለዘመናዊ ኢምፔሪያሊዝም ማርክሳዊ ትንተና የተካሄደው በሌኒን ነው ። ሌኒን ሲጠቁም ፡— አንድ ልዩ ጠባዩ የካፒታል የአገር ድንበር ጥሶ መውጣት ነው — ይህ ነው ከሌላው የሸቀጥ ምርት ወደውጭ መውጣት የሚለየው ። በካፒታሊዝም ውስጥ የተደረጉት የአንዳንድ ለውጦች ሁኔታ ውጤት ይህ ነው ። ስለዚህም ኢም

ፔሪያሊዝምን ሲገልጸው የካፒታሊዝምልዩ ደረጃ ነው ብሉ
ታል ። በከፍተኛ ደረጃ ሞኖፖሊዎች በዋና የካፒታ
ሊስት ሃገሮች የአደጉበት ፤ የሠለጠኑበት ማለት ነው ።

በቀድሞው የኢንዱስትሪ ካፒታሊዝም ጊዜ ፋብሪካ
ዎች ፤ ማዕድኖችና ሌሎችም ድርጅቶች በጣም ጥቂት
ነበሩ ። እንደደንብ ሆኖም በቤተሰብ ደረጃ ወይም በጓደኛ
ሞች — ማለትም አንድን ፋብሪካ ለማቋቋም ወይም ለመ
ጀመር የሚአስችል የመዋጮ ድርሻ ሊሰጡ በሚችሉ ነበር
የተያዙት ። ይሁንና እየንዳንዱ አዲስ ቴክኒካዊ ዕድገት
ብዙ ካፒታል አስፈለገው ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኢንዱ
ስትሪ ውጤቶች ገበያ በማያቋርጥ ሂደት እየተስፋፋ ሄደ ።
አነስተኛ የእጅ ሥራዎችን እየጨፈለቀ በመጀመሪያ በእ
ንግሊዝ ከዚያም በሌሎች አገሮች አደገ ። ስለዚህም የኢ
ንዱስትሪያዊው ድርጅት መጠን በአፋጣኝ ተመነደገ ።

ከሃዲድ መንገዶችና ባቡሮች ፤ ከእንፋሎት መርከቦች
መገኘት ጋር ተያይዞ ፤ የብረትና በኋላም የአረብ ብረት
ኢንዱስትሪ ማደግ የብዙ የኢንዱስትሪ ድርጅቶችን ዕድገት
ጠሩ ። ኢንዱስትሪው ምንም ዓይነት ይሁን ምርትን ለማ
ፋጠን ትላላቅ ኢንዱስትሪዎች ለቁጠባ (ለባለቤቱ) ይመ
ረጣሉ ። ስለሆነም ብዙ ትርፍና የመስፋፋት መንገድን
ዝንባሌ አሳዩ ። አነስተኛ ድርጅቶች ለመወዳደር ባለመቻ
ላቸው ተዘጉ ወይም በተወዳዳሪዎቻቸው ተዋጡ ።

ስለዚህ ሁለት ዓይነት ሂደቶች በማከታተል ሥራ ላይ
ዋሉ ። በትላላቅ ድርጅቶች ምርት እጅግ በጣም እየደለበና
በጣም ሀብታም በሆኑ ሰዎች ቁጥጥር ሥር የሚውለው የም
ርት መጠን በማከታተል እየጨመረ ሄደ ።



ማርክስ እርሱ በኖረበት ዘመን ይህንን በመረዳቱ ለ
ጨመረ ስለሚሄደው ቴክኒካዊ ክምችት መጤን እንዳለበት
አስገንዝቦ ነበር ። ይህም ፩ / በከፍተኛ ክፍሎች የምርት
መድለብ ፤ ሁለተኛ — በባለቤቱ ሥር የካፒታል መድለብ
ወይም በጣም ቁጥራቸው አነስተኛ በሆኑ ሰዎች መከማቸት
መቀጠሉን ነው ። የማይቀረው ውጤትና ነጻ ውድድር በሞ
ኖፖሊዎች መተካቱን አይቶ ነበር ። እናም ይህ በካፒታሊ
ዝም ውስጥ የሚገኙትን ችግሮች ሁሉ በጣም አስከፊ ወደ
ሚሆን ደረጃ እንደሚአደርስ ግልጽ ነው ።

በዚህ ምዕተ—ዓመት መጀመሪያ ላይ ኢኮኖሚያዊ
ጸሐፊዎች (በተለይም ጄ.ኤ. ሆብሰን በእንግሊዝ ውስጥ)
በብዙ ኢንዱስትሪዎች ላይ የደረሰውን ከፍተኛ የሞኖፓሊ
ደረጃ መዝግበዋል ። በ፲፱፻፲፮ ፤ በአንደኛው የዓለም ጦርነት
ጊዜ ፤ ሌኒን (ኢምፔሪያሊዝም :— የካፒታሊዝም ከፍተ
ኛው ደረጃ በሚለው መጽሐፉ) ስለሞኖፖሊዎች ዕድገት
የታወቁ የተለያዩ ዕውነቶችን በአንድነት አቅርቦ ፤ ይህንኑ
ዝንባሌውን ወደ ፖለቲካዊና ሶሻላዊ ሁኔታዎች ከማዞሩም
ሌላ የሞኖፖሊን ኢኮኖሚያዊ ገጾች በንጹህ አሳይቷል ።
ማርክስ ከሞተ ጀምሮ ያለውን የዕድገት መሠረት — ማለ
ትም ማርክስ ከደረሰበት መደምደሚያ ላይ ተነስቶ ሌኒን
ማስፋፋትና ማሳደግ ችሏል ። ሌኒን :— የካፒታሊዝም
የኢምፔሪያሊስት ደረጃ —(የዳበረው ወደ 1900 ዓ. ም. ላይ
ነው ፤ )አምስት ኢኮኖሚያዊ ገጾች እንዳሉት ይናገራል ።

፩/ የምርትና የካፒታል መድለብ በኢኮኖሚያዊ ሕይ
ዎት ላይ ዋና ሚና ይዞ የሚጫወተውን ሞኖፖሊን በከፍ
ተኛ ደረጃ አሳድጎ አስፋፍቷል ።

ይህ በበለጸጉ ሐገሮች ሁሉ የተፈጸመነው ፤ በተለይም
በጀርመንና ዩናይትድስቴትስ ። እንደዕውነቱ ከሆነ ሂደቱ

በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ነው፤በእንግሊዝ ይህ ሁኔታ በኢ.
ምፔሪያል ኬሚካል ኢንዱርስትሪዎች ከመጠባበቂያ ሌላ
በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. በ፩፻፶፰ ሚሊዮን ፓውንድ እና በዩኒሊበር
በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም. ከመጠባበቂያ ሌላ በ፩፻፲፩ ሚሊዮን ፓውንድ
መጨመራቸው ቀዋሚ ምሳሌዎች ናቸው ። በኢያንዳንዱ
ኢንዱስትሪ ከአጠቃላዩ ንግድ በጣም ከፍተኛው ድርሻ
የሚካሄደው በጥቂት ድርጅቶች ነው ። ብዙውን ጊዜ
ዋጋን ለመወሰን ፤ ኮታን (ድርሻን) ለመመጠንና በሌላም
ምክንያት ስምምነት ፈጥረው በመጨረሻም የተዋሀደ
ሞኖፖሊ ባስገኙት ድርጅቶች ነው የሚካሄደው ።

፪. የባንክ ካፒታል ከኢንዱስትሪ ካፒታል ጋር «የፋ
ይናንስ ካፒታል» ማሕበር ፈጥሮ ኢያንዳንዱን ሀገር ይገ
ዛል ።

ይህ ነጥብ አንዳንድ መግለጫዎች ይፈልጋል ። በመ
ጀመሪያ የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶችና ባንኮች ጥቂት
ወይም ከኢንዱስትሪያዊ ድርጅቶች ቀጥተኛ ወለድ ስለሌ
ላቸው የተለያዩ ነበሩ ። ቢሆንም ቅሉ ገንዘብ ለድርጅቶቹ
እያበደሩ ካለው ትርፍ በወለድ መልክ ድርሻ ይወስዳሉ ።
ነገር ግን ከኢንዱስትሪ ዕድገትና የሕብረት ኩባንያዎች
በሠፊው መቋቋም ጋር ተያይዞ የባንክ ባለቤቶችም በኢንዱ
ስትሪያዊ ኩባንያዎች ውስጥ አክሲዮን (ድርሻ) መግባት
ሲጀምሩ በጣም ሀብታም ኢንዱስትሪ ያሊስቶች በባንክ
ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው ሆነ ። ስለዚህ እጅግ በጣም
ከበርቴዎች ከባንክም ይጀምሩ ከኢንዱስትሪ ባንከኛ — ኢ
ንዱስትሪ ያሊስቶች ሆኑ ። በዚህ የካፒታሊስቶች የውህደት
አሠራር በአንድና በዚሁ ቡድን ውስጥ በሚአስደንቅ ሁኔታ
ኃይላቸው ጨመረ ። (በተለይም በእንግሊዝ ትላልቅ የመ
ራት ከበርቴዎችም ከዚህ ቡድን ጋር ወጥተዋል) ባንክ ፤



ከኢንዱስትሪያል ድርጅቶች በመያያዝ ገንዘብ እያበደረ
ይረዳል ። ባንኩ በሚፈልገው ዓይነት ከድርጅቱ ጋር ግዴ
ታዎችን በመዋዋልና በሌላም ለኩባንያዎች ብድር ያዘጋ
ጃላቸዋል ። ስለዚህ የፋይናንስ ካፒታሉ ቡድን ሀብቱንና
በሞኖፖሊ ላይ ያለውን ቁጥጥር ከአንድ የኢንዱስትሪ
ክፍል ወደ ሌላው ለመጨመርና በአፋጣኝ ለማደግ አስች
ሎታል ። እናም ፤ ለማለት ባያስፈልግም ፤ ሁኔታው የመን
ግሥትን ዝንባሌ ስቦት ነበር ።

የባንክንና የኢንዱስትሪን ውህደት በደንብ የሚአሳ
የው በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ በባንክ ድሬክተሮች አማካ
ይነት የአስተዳዳሪዎች (ድሬክተሮች) ቁጥር እየጨመረ
መሄድ ነው ። ይህም ሌሎች ድርጅቶችን ባንኩ ያዝባቸ
ዋል ማለት ሳይሆን ፤ ዋናው ነጥብ በባንክ ዓለም ውስጥ
ኃይል ያላቸው በኢንዱስትሪና በንግድም ኃይል እንዳላ
ቸው ለመግለጽ ነው ። በብሪቲሽ ካፒታሊዝም ውስጥ ካፒ
ታላቸው የሚራራጠውን በጣም የሀብታም ሰዎች ቡድና
ችን ይመሠርታል ለማለት ነው ። በ፲፰፻፸ የባንኮቹ
ድሬክተሮች በኋላ (The''Big Five») «ትልቆቹ አምስ
ቶች» የተባሉትና የኢንግሊዝ ባንክ ፩፻፺፯ ሌሎች አስተ
ዳዳሪዎች አስቀምጠዋል ፤ በ፲፱፻፲፫ ደግሞ ፫፻፷፱ ፤
በ1939 እንደገና 1150 ተሹመዋል ። የዚህ ቁጥር ሙሉ ኃይል
የሚአይለው የ፲፱፻፴፱ ቁጥር ዩኒሊቨርና (I-C-I) ኢምፔ
ሪያል ኬሚካል ኢንዱስትሪ — ሲጨመር ነው ። እነኝህ
ሁለት ድርጅቶች ብዙ ትናንሽ ድርጅቶችን የዋጡ ናቸው ።

፫. የካፒታል ወደ ውጭ መውጣት ከሸቀጦች ወደ
ውጭ መውጣት ጋር ሲመዛዘን ዋናነቱ እያደገ ሄደ ።

በካፒታሊዝም የመጀመሪያ ደረጃ እንግሊዝ የልብስ
ሸቀጦችንና ሌሎችንም የፋብሪካ ውጤቶችን ወደውጭ

( Local Prodcts ) ተራ ምርቶች
በመለክ በምትኩ ( Local Prodcts ) ተራ ምርቶች
በመለክ በምትኩ የኢንዱስትሪ ውጤቶቿን በጥሬ
ትገዛ ነበር ። ስለዚህም የኢንዱስትሪ የሚያስፈልግ ምግብ
ዕቃዎችና ለብሪቴሽ ኢንዱስትሪ የሚያስፈልግ ምግብ
ትለውጥበታለች ። እንግዲህ ባለፈው ምዕተ ዓመት
ሁለተኛ አጋማሽና በተለይም በመጨረሻው ፤ ፋይናንስ
ካፒታል ወደ ውጭ በሚወጣ ካፒታል ውስጥ ይዞታው
እጅግ እያደገ ሄደ ። በንግድ ልውውጥ ላይ ሳይሆን ፤ ግን
ከዓመት ወደ ዓመት በካፒታል ላይ የወለድ ማስገባት ሄደቱ
እየጨመረ መሄዱን ነው ። የዚህ ዓይነት የካፒታል ወደ

ውጭ መውጣት — መፈጸም የሚችለው ማለትም ለውጭ
መንግሥታት ወይም ኩባንያዎች ገንዘብ ማበደር ወይም
በሌሎች ሀገሮች ውስጥ ያሉ የባቡር መስመሮችና የባሕር
ላይ ሥራዎችን ወይም የማዕድን አውጭ ድርጅቶችን የገን
ዘብ ማጠናከር ዕርዳታ የሚከወነው — ተረጂዎቹ የማቴሪ
ያሉችና ወዘተ . . . . . መጠየቂያዎችን ባንኩ በእንግሊዝ
ውስጥ ራሱን ካስከገባባ ቸው ድርጅቶች ውለታ ካካሄዱና
ግንኙነት ከፈጠሩ ነው ። ስለዚህ የፋይናንስ ካፒታል ሁለት
ክንፎች (ኢንዱስትሪና ባንክ ) ተወዳዳሪዎቻቸውን በመ
ጣልና አንድ ላይ በመሥራት እያንዳንዳቸው በጣም ብዙና
ትልቅ ትርፍ አገኙ ።

፬. የዓለም አቀፍ ሞኖፖሊስቶች ከበርቴዎችን በማ
ዋሀድ ተመሥርተው ዓለምን በመካከላቸው ተከፋፈሏት ።

ይህ የታየው በብረት ፤ በዘይትና በሌሎችም ብዙ ድር
ጅቶች ነው ። ይህ በተለያዩ አገሮች የሚገኙ የሞኖፓል
ቡድኖች በውጭ ንግድ ላይ ምን ያህል ድርሻ እንደሚኖራ
ቸው ስምምነት ወሰደዋል ። ሌላው ይቅርና በእያንዳንዳ



ቸው የተለዩ የገበያ ቦታዎችና ቀዋሚ ተመንም ተደርጓል ።
የዚህ ስምምነት ወሰኖች በኋላ ይገለጻሉ ።

፭. በኃያላን መንግሥታት የዓለም ግዛታዊ ክፍፍል
በትድሚያ አልቋል ። (በ፲፰፻፸፮ ዓ.ም. የአፍሪቃ በአውሮ
ጳውያን ኃይሎች ይዞታ ስር የነበረው 11% እና በ፲፱፻
ዓ. ም. 90% ነበር) ።

የዚህ ዋናነቱ የብዙ ወይም የጥቂት መከላከያ የሌላቸ
ውን ሀገሮች የግዛት ነጠቃወይም ማዋሃድ ከእንግዲህ ሊቀ
ጥል አለመቻሉ ነው ። በጣም በበለጸጉ መንግሥታት ውስጥ
ያሉ የፋይናንስ — ካፒታል ቡድኖች የሚቆጣጠሯቸውን
ግዛቶች እርስ በእርሣቸው ካልተጠፋፉ በቀር ከእንግዲህ
ማስፋት አይችሉም ። ማለትም ዓለምን እንደገና ለመከፋ
ፈል ከፍተኛና ሠፋ ያለ ጦርነት አካሄደው አንዱ ከአንደ
ኛው ድል በማድረግ ወይም በማጥፋት ካልተነጣጠቁ
በቀር ።

በሌኒን ከተጠቆሙት ነጥቦች በተለይ በዚህ ግንኙነት
ላይ ከዋናዎቹ አንዱ ይህ ነው ። የእያንዳንዱ ኢምፔሪያሊ
ስት አገር ለመስፋፋት የሚአደርገው መገፋፋት ጠባይ
በአጠቃላይ የተከሰተው ዓላማውን በቅኝ ግዛቶች ላይ ሲያ
ተኩር ነው ተብሎ ተገምቶ ነበር ። ሌኒን ሲጠቁም ይህ በም
ንም ዓይነት ዋናው አልነበረም ፤ መነሳሳቱ በአጠቃላይ
ተስማሚ ሁኔታዎች ሲፈጠሩለት በትክክል በሌሎች በኢን
ዱስትሪ የዳበሩ አገሮችን በማጥቃት ላይ ነበር ብሏል ።
በናዚዎች ወቅት የጀርመን ፋይናንስ — ካፒታል መነሳሳት
በማንላይ እንደነበር ማወቅ ለዚህ ግልጽና ጥሩ ምሳሌ
ነበር ።

በዚህ አጠቃላይ ትንተና ላይ በመመርኮዝ ሌኒን የካፒታሊዝም ኢምፔሪያሊስት ደረጃ ሲመጣ ከከፍተኛ ምጣኔ — ሀብታዊ ቀውሶች ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጦር — ነቶችና በሌላ በኩል የሠራተኛው መደብ አብዮቶችና በቅኝና በግማሽ ቅኝ ግዛቶች ውስጥ ያሉ የተጨቆኑ ሕዝቦች የኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛን በመቃወም ከማመጽ ጋር ነው የሚከሠተው ብሎናል ።

በጥቂት ቡድኖች እጅ የካፒታል መድለብ ማለት የእነኚህ ጥቂት ቡድኖች በመንግሥት መሽከርከሪት ላይ እጅግና በጣም ከፍተኛ ኃይል ማግኘት ነው ። ስለዚህም የተለያዩ አገሮች ፖሊሲ የእነዚህን ጥቂት ጠባብ ክፍሎች ፖሊሲ በተቀራረበ ሁኔታ ተባብረው ማለት ነው ። ይህ ጠባይ ነው በየአገሩ ያሉት የፋይናንስ ካፒታል ቡድኖች የውጭ ተወዳዳሪዎቻቸውን ፤ በኰታና ፤ በሌላም መንግሥታዊ ርምጃዎች በመጨረሻም ደረጃ በጦርነት ለመዋጋት ያስቻላቸው ።

ለምንድነው በነዚህ ተወዳዳሪ ቡድኖች መካከል ያለው ግጭት ሊቀር የማይችል የሚሆነው ? ለምንድነው ዓለምን በመካከላቸው ለመቃረጥ የማይ ስማሙት ?

የተለያዩ አገሮች የሞኖፓሊ ቡድኖች የዓለምን ገበያ ለመከፋፈል ስምምነት አድርገው እንደነበረ አላይ ተጠቅሶ ነበር ። በሥውር መልኩ ፤ ይህ የውድድርን ፍጹም መጥፋት ወደ ሚአረጋግጥ ሁኔታ የሚወስደን ይመስላል ። እናም ነዋሪ የሆነ ዓለም አቀፋዊ የፍላጐት ጸባይ ዓይነት የተፈጠረ ያስመስላል ። ነገር ግን ሌኒን ይህ ዓለም አቀፋዊ ስምምነት እስከመጨረሻ ዘላቂ አለመሆኑንና ሊቀጥል እንደማይችል ጠቁሟል ። ለምሳሌ በ፲፱፻፰ ዓ.ም. የተደረገው



ስምምነት ከአምራች ኃይሎች ጋር ባለው ግንኙነት ማለትም በዚያን ጊዜ ባሉት የተለያዩ ቡድኖች እንበልና በእንግሊዝና በፈረንሣይ ፤ በጀርመንና በአሜሪካ መካከል የገበያዎችን መከፋፈል መሠረት በማድረግ የተፈጸመ ነው ። ይሁንና ያልተስተካከለ ዕድገት የካፒታል የዕድገት ሕግ ነውና ይህ ዓይነት ስምምነት ከተደረገ ከጥቂት ዘመናት በኋላ ፤ የጀርመን የአምራች ኃይል ቡድን ወይም የአሜሪካ ወይ የሌላው እድገቶ ጨምሮ ሊሆን ይችላል ። ስለሆነም ይህ የአደገው ቡድን ፊት ባለው የገበያ ክልል (በዓለም ውስጥ) ተወስኖ ሊኖር በፍጹም አይፈቅድም ። ስምምነቱን ያወግዛል ፤ እናም ሌላው ቡድን በአፋጣኝ ካልተቀበለው (ካላመነበት) ለገበያ ሲባል አዲስና መራራ ትግል ይጀምራል ። በእውነትም ፤ ለእነዚህ ዓይነት ስምምነቶች ሁሉ ይህ ነው ዕጣቸው ። የአልተመጣጠነ ዕድገት ሕግ የሚውለው ለተወሰኑ የኢንዱስትሪያል ቡድኖች ብቻ ሳይሆን ፤ በአጠቃላይ በተለያዩ አገሮች ካፒታልም ላይ ነው ። እንግዲህ ከተባለ ፤ ምጣኔ — ሀብታዊ ስምምነቶች በተለያዩ አገሮች ባሉ የፋይናንስ ካፒታል ቡድኖች መካከል በሚደረግ የማያቋርጥ የንግድ ጦርነት ውስጥ መጫሪያዎች ብቻ ናቸው ። ሌላም አይደሉ ።

ምጣኔ ሀብታዊ ጦርነት ብቻውን ምንም መፍትሔ አይሰጥም ። ስለሆነም ፤ የፋይናንስ ካፒታል ቡድኖች በሃገራቸው ባለው የመንግሥት መሽከርከሪት በኩል በተወዳዳሪዎቻቸው ላይ የታሪፍ ድንበር በመሥራት ፤ ወደ ውስጥ በሚገባ ሸቀጥ ላይ መጠን (ኰታ) በመወሰን ፤ ከሌሎች አገሮች ጋር የተሻለ የንግድ ስምምነት ለማዘጋጀት በመሞከር ፤ ሞኖፖሊአቸውን በሚአንቀሳቅሱበት አካባቢ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ይታገላሉ ። እናም በተወዳዳሪአቸው

ላይ ጊዜአዊ የበላይነት ሊአስጨብጥ የሚአስችል ድል ለማ
ግኘት ለጦርነት ይታጠቃሉ ።

በተለያዩ አገሮች ባሉ የፋይናንስ ካፒታል ቡድኖች እጅ ውስጥ የሀብት መድለብ ውጤት የሁለቱን የዓለም ጦርነት አምጥቷል ። ግልጽ የሆነ ንጹህ ምጣኔ ሀብታዊ ሂደት — የካፒታልና የምርት መድለብ — አደገኛ ወደሆነ የሕብረተሰብ የጥፋት ጦርነት ይመራል ።

ስለጦርነት የማርክሲስቶች አቀራረብ የፍጹም አን የው ( Pacifist ) ዘዴ አይደለም ። ለነጻነታቸው የሚዋጉ ሕዝቦችን ጦርነት ለማፈንና ለመያዝ ኢምፔሪያሊዝም የሚአካሄደውን ጦርነት ያወግዛል ። ምክንያቱም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሰዎችን ዕድገት ገቷል ፤ ወደኋላ ስቧልና ። እንዲህ ዓይነቱን ጦርነት ትክክል ያልሆነ ጦርነት ይሉታል። ነገር ግን የኢምፔሪያሊዝምን የማጥቃት ጦርነት ለመቋቋም ወይም ከኢምፔሪያሊስት የአገዛዝ ቀንበር ሥር ነጻ ለመውጣት የሚደረግን የሕዝቦች ጦርነት ትክክል ብለው ይወስዱታል ፤ ብዝበዛን ለማጥፋት የሚካሄድ ሕዝባዊ ጦርነትንም እንዲሁ ። ሕዝቦች በዝባዦችን ድል ሲአደርጉ ብቻ ነው የጦርነትን መንስኤ ምክንያቶች የሚአቆሙትና ጦርነትም ለዘላለም የሚጠፋው ።

አንድ የኢምፔሪያሊስት መንግሥት ትክክል ያልሆነ ጦርነት በሚአነሳበት ጊዜ ፤ በማንኛውም መንገድ በዚያ አገር ውስጥ የሚገኝ የሠራተኛ መደብ ጦርነቱን መቃወም አለበት ። ጠንካራ ከሆነም ጦርነቱን ለመግታት እና ወደሶሻሊዝም የሚአስኬደውን እርምጃ ለመጀመር መንግሥቱን ገልብጦ ሥልጣን መውሰድ ይኖርበታል ። ይህ ነው በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም. በሩሲያ ሠራተኞች የተወሰደው ፖሊሲ ።



በተወዳዳሪ ኢምፔሪያሊስት ቡድኖች መካከል የሚካሄደው የመወዳደር ትግል የአለም አጠቃላይ ሁኔታዎችን እየአባባሳቸው የመሄድ ጠባይ ነው ያለው ። የቴክኖሎጂ መሻሻል — (የጉልበት መተኪያ ማሺን) — ከራሱ ጋር የታፈገና የተጠናከረ ፍጥነትን በመጨመር ሥራ አጥንትን ያስከትላል ። የምንዳዕ ክፍያዎች ዝቅ እንዲሉ በማስገደድ የገበያ ይዘትን ለማስጠበቅና ለማሸነፍ ይሻሉ ። (ደመወዝን በማሺኖች ተጠቅሞ በመቀነስ የገበያውን የተመን መዋለል ያካክሱበታል ።) ትላልቅ የሞኖፖሊ ድርጅቶች ለእርሻ ምርቶች ይከፍሉት የነበረውን ተመን ይቀንሳሉ ። ለጦር መሣሪያዎችና ለሌላም የጦርነት ዝግጅቶች ገንዘብ ለማግኘት ሲባል ለሕብረተሰቡ የሚሰጡ ግልጋሎቶች ይቋረረጣሉ ። ምጣኔ — ሀብታዊ ቀውሶች የጠለቁና በጣም የተራዘሙ ይሆናሉ ። ይህ ነበር በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል የታየው ገጠመኝ ።

በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ነው የመደብ ትግልና ኢምፔሪያሊዝምን የመቃወም የቅኝ ግዛት ሕዝቦች ትግል በጣም እየሰሉና እየተቡ የሄዱት ። እንግዲህ የካፒታሊዝም ኢምፔሪያሊስት ደረጃ የጦርነቶች ወቅት ብቻ ሳይሆን የአብዮቶችም ጭምር መሆኑን ነው የምንገነዘበው ።

ሌኒን በትንተናው ላይ እንዳሳየው ሌላም የካፒታሊዝም የኢምፔሪያሊስት ደረጃ አለ ፤ በኢምፔሪያሊስት አገሮች ያሉ የሞኖፖሊስት ቡድኖች ወደኋላ የቀሩ አገሮችን በመበዝበዝ ከአማካይ በላይ (Above Average) የሆኑ ትርፎችን መውሰድ ይችላሉ ። የዚህ ምክንያቱ በከፊል የእነዚህ አገሮች ሕዝቦች የኑሮ ደረጃ ዝቅ ማለት ነው ። በከፊል ደግሞ ፡— ምክንያቱም ፍጹም ጨካኝ በሆኑ ገዥዎችና በካፒታሊስቶች በሚፈጸሙባቸው አደገኛ ሁኔ

ታዎች ነው ። እናም በከፊል ፡— ምክንያቱም የማሺን ኢን
ዱስትሪ ምርቶች ከእጅ ሥራ ምርቶች ከፍተኛ በሆነ ልዩ
ነት የአለመመጣጠን ልውውጥ ስለሚደረግ ነው ። ይህ ገን
ዘብን አይመለከትም ፤ በዕቃዎች ላይ ያለውን እንጂ ።
የማንኛውም ምርት የልውውጥ ዋጋ (ዕሴት) ሊወሰን የሚ
ችለው ምርቱን ለማምረት የወጣው ጉልበት ሕብረተሰቡ
በሚቀበለው አማካይ የሥራ ጊዜ እንደነበር መታወስ አለ
በት ። እንበልና በእንግሊዝ በመኪና አንድ ያርድ ጨርቅ
ለማምረት ሕብረተሰቡ በተቀበለው የሥራ ሰዓት የሚወሰ
ደው ጊዜ በአንድ የእጅ ማጠንጠኛ የተሠራ አንድ ያርድ
ጨርቅ የወሰደውን 1/10ኛ ወይም 1/20ኛ ሊሆን ይችላል ።
ነገር ግን መኪና የሠራው ጨርቅ ሕንድ ሲገባ የሚለወ
ጠው ሕንድ ውስጥ ካለው የሕንድ ጨርቅ ዋጋ (ዕሴት) ተቃ
ራኒ በመሆን ነው ። በሌላ አነጋገር ጨርቁ እንግሊዝ ውስጥ
ከነበረው ዋጋ (ዕሴት) በላይ በጣም ከፍ ብሎ ሕንድ ውስጥ
ተለወጠ ማለታችን ነው ። በዚሁ ጊዜ ከዚህ ከፍተኛ ዋጋ
(ዕሴት) ጋር እኩል የሆኑ የሕንድ ጥሬ ዕቃዎች ወይም ሌላ
ምርቶች ወደ እንግሊዝ ሄደው ይሸጣሉ ። አንድ ያርድ
ጨርቅ በእንግሊዝ ውስጥ ቢሸጥ ኖሮ ያስገኝ ከነበረው
ትርፍ በጣም የበለጠ ትርፍ ያስገኛሉ ። የመኪናው ዓይነት
አንድ በሚሆንበት እንኳ ፤ የተለያዩ የልምድ ደረጃ ያላ
ቸው እንደልምዳቸው መጠን ያመርታሉ ፤ እናም ውጤቱ
ተጨማሪ ትርፍ ያስገኛል ። ይህ ተጨማሪ ትርፍ በልብስ
ብቻ አይደለም ፤ በእርግጥ በእንደዚህ ዓይነት ላሉ ሸያጭና
ግዥ ሁሉ ይውላል ፤ በዚህም ምክንያት በፋይናንስ — ካፒ
ታሊስት ቡድኖች ሠፊ ሀብት ይበዛል ። ይህ ሰፊ ሀብት እንደ
ኢስርማን 40,000,000 ፓውንድና እንደ «ዘየሌ» 20,000,000
ፓውንድ ሊገኝ የቻለው ብዙው ከዚህ ተጨማሪ ትርፍ
ነው ።



ይህ ከቅኝ ግዛት ሕዝቦች ብዝበዛ የሚወጣው ተጨማሪ ትርፍ ከሠራተኛ እንቅስቃሴ ጋር አዛምደን ስናየው በጣም ልዩ የሆነ ዋናነት አለው ። ማርክስ ከዚህ በፊት እንዳመለከተው የእንግሊዝ ካፒታሊስት መደብ ማለትም በመላው ዓለም በመጀመሪያ መኪና የሠራውን ምርት ሲሸጥ የነበረው ፤ በተለይ ልምድ ያላቸውን የሠራተኛ ክፍሎች በሚመለከት ረገድ ፤ በሠራተኛው መደብ በሚደረግበት ግፊትና ተጽእኖ ለጥያቄዎች መልስ ይሰጥ ነበር ። ስለዚህ በእንግሊዝ ፤ አንዳንድ ልምድ ያላቸው ኢንጂኔሮችና የጥጥ ሠራተኛ ክፍሎች በሌላ አገር ተቀጥረው ከሚሠሩ ሠራተኞች ይበልጥ ደረጃቸውን አስጠብቀው ነበር ። ከዚህም ጋር የቅኝ ግዛቶችን በካፒታሊስቶች መበዝበዝና ከራሳቸው ፍላጎት ጋር ያለውን ልዩነት ለማወቅ አዘንብለው ነበር ። ሌኒን እንዳሳየው ፤ ይህ የሆነው እያንዳንዱ በኢንዱስትሪ የገፋ አገር የኢምፔሪያሊስቶች ደረጃ ሲደርስ ነው ። በአንጻሩም የሠራተኛው ክፍል በተለይ የጥቅም ደረጃ ላይ የተቀመጡ መሪዎች የአድር ባይነት ዝንባሌ አጠቃቸው ። ይህም ማለት የሠፊውን ሠራተኛ ሁኔታ ከምንም ሳይቆጥሩትና ሳያጤኑት በሠራተኛው ስም ከካፒታሊስቶች ጋር መስማማትና መወደጃታቸው ነው ።

የኢምፔሪያሊስት ደረጃ እያደገ ሲሄድ ይህ ዝንባሌ (ሁኔታ) እየጠነከረ ሄደ ፤ በዚህም ሳቢያ በሠራተኛው መሪ ክፍሎችና የሶሻሊስት ንቅናቄዎች በሃገራቸው ባሉት የፋይናንስ ካፒታል ኢምፔሪያሊስት ፖሊሲ ዎች መካከል ያለው ልዩነት በደንብ ተገለጸ ። በአንደኛው የዓለም ጦርነት ይህ ሁኔታ የትም ባሉት ግልጽ በሆኑ የሠራተኛ እንቅስቃሴዎች ማሕበራት (ቦልሼቢኮች ማርክሲስቶች ሆነው በመቅረታቸው ምክንያት ከሩሲያ በቀር) በጦርነት ምክንያት የተፈጠረውን አጋጣሚ ተጠቅሞ ከካፒታሊስቶች ሥል

ጣን በመንጠቅ ፍንታ ፤ ሀገራቸው ውስጥ ካሉት ኢምፔሪ
ያሊስቶች ጋር በማበር ለጦርነቱ ተሰልፈዋል ።

በተለያዩ አገሮች የሠራተኛው መደብ ፓርቲዎች አድ
ርባይነት አመለካከት (ከገዥው መደብ ጋር የራሳቸውን
ፍላጐት የማስማማት መለያቸው ነው) ከ፲፱፻፲፬—፲፰ ዓ.ም.
ጦርነት በኋላ የማርክሲዝምን ርዕዮተ — ዓለም አማኝና
የሠራተኛውን ዕንቅስቃሴ የማርክሲዝም ተከታይ እንዲ
ሆን ለማሸነፍ የሚታገሉ የኮሚኒስት ፓርቲዎችን መመ
ሥረት አስፈላጊና አጣዳፊ አደረገው ።

በኢምፔሪያሊስት ደረጃ ውስጥ የቅኝ ግዛቶች ለነጻነት
የሚያደርጉት ትግልም ወሳኝና የተስፋፋ ሆነ ፤ የካፒታሊስ
ቶች በቅኝ ግዛቶች ሠርስሮ የመግባትና የመውረሩ ዘዴ የድ
ሮውን የምርት ስልት ሰባብረው ፤ እናም በብዛት የሚቆ
ጠሩ ሕዝቦች የሚኖሩበትን መሠረት አጠፋው ። በላን ካሻ
የር ግዙፍ ፋብሪካዎች የሚካሄደው ውድድር የሕንድ
ሕዝብ የኑሮ ሕልውና የሆኑትን በእጅ አጠንጣኝ ሠራተ
ኞችን ምርት አልባ በማድረግ ወደ እርሻ እንዲመለሱና
በመሬት ላይ ያለውን የሥራ ግፊት ጨመረው ። በኢምፔ
ሪያሊስት ደረጃ የብድርን ወለድ ጥቅም ለመጠበቅ እና የኢ
ምፔሪያሊዝምን መዋቅር ለመጠገን (በሲቪልም ሆነ በወ
ታደራዊ ተቋም) ሰፊው ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ግብር በመ
ጨመር ጭነት እንዲአይልበት ተደርጓል ። በዚህ የተነሣ
በመሬት ላይ እጥፍ ግፊት እንዲጨመርና የቅኝ ግዛት ምር
ቶች በትልላቅ ሞኖፓሊስቶች ተመናቸው እንዲአሽቆለ
ቆል ሆነ ። ድህነትና ቀጥተኛ ረሃብ ላልተቋረጡ የገበሬ
ትግሎች መሠረት ጣሉ ። በከተማ የኢንዱስትሪ ምርት
የሚካሄደው በአደገኛ ሁኔታ ነው ። የሠራተኛው መደብ
ድርጅቶች ከተቻለ የጨቆናሉ ፤ ካልሆነም ይደናቀፋሉ ።



መካከለኛ መደቦች በተለይም ምሁራን የኢምፔሪያሊስቶች
አሸክላማ የማሠሪያ ሕጎች ምንነት ይሰማቸዋል ፤ ይስቃ
ያሉም ። ስለዚህ ሰፋ ያለ የነጻነት እንቅስቃሴ ያደርጋሉ ።
በተለያዩ መልክ ይሁን እንጂ በሌሎችም የቅኝ ግዛት አገ
ሮችም ይኸው ይነሳል ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት
ጀምሮ የቅኝ ግዛቶች የነጻነት እንቅስቃሴ ከመቸውም ይልቅ
በጣም ሰፍቶና ጠልቆ ታይቷል ።

ማርክሲስቶች እነዚህን ትግሎች የሚአዩዋቸው በካ
ፒታሊስት ብዝበዛ ምክንያት እንደማይቀር ውጤትና
እናም ሊአከትም የሚችለው ኢምፔሪያሊስት ቡድኖችን
አፈርድሜ በማስጋጥ እንደሆነ ነው ። ስለዚህም ሠራተኞች
በኢምፔሪያሊስት አገሮች ያሉ የፋይናንስ — ካፒታሊስቶ
ችንና በአጠቃላይ ኢምፔሪያሊዝምን ከቅኝ አገር ሕዝቦች
ጋር በመሆን የጋራ ጠላት አድርጎ መውሰድና መዋጋት
ይኖርባቸዋል ።

አንደኛው የዓለም ጦርነት—የካፒታሊዝም ጠቅላላ ቀ
ውስ የመጀመሪያው ልደቱን የአስመዘገበበት ማለት ነው—
በትላልቅ ኃይሎች መካከል የፋይናንስ ካፒታል ቡድኖች
ያካሄዱት የትግል ውጤት ነው ። በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም. በሩሲያ የሠ
ራተኛው መደብ በሌኒን ተመልካችነት በቦልሼቪክ ፓርቲ
መሪነት እየተመራ የካፒታሊስቶችና የመሬት ከበርቴዎ
ችን አገዛዝ ወርውሮ በታሪክ ላይ የመጀመሪያዋን የሶሻሊ
ስት መንግሥት መገንባት ጀመረ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ
ዓለም እየጠነከረና ተጽዕኖውን እያሰፋ በሚሄደው የሶሻ
ሊስት ክበብና የካፒታሊዝም ቅሪቶዎች ሁሉ በኢምፔሪያ
ሊስት ደረጃ ላይ የካፒታሊስትን ሕብረተሰብ ፖለቲካዊና
ኤኮኖሚያዊ መሠረቶች እየፈረካከሱና እያሚሸሹ እያጨማ
ተሩ በሚሄዱበት የታሪክ ወቅት ውስጥ ባለው የኢምፔሪያ
ሊዝም ክበብ ተከፍላለች ።

## ምዕራፍ ፭ ፤

# የመደብ ትግሎችና መንግሥት

በምዕራፍ ፪ ውስጥ የማርክስ የመደብ ትግል አጠቃላይ ንድፈ ሀሳብ ተገልጾ ነበር ። የመደብ ትግሎች ሊመጡ የሚችሉት ሕብረተሰብን በመደብ በሚከፋፍሉ የአመራረት ሥልቶች (መልኮች) ነው ። ማለትም አንደኛው መደብ የሚመረተውን የምርት ሂደት አካሄድና አምራች ሲሆን (ባሪያው ፤ ገባሩ ፤ የምንዳዕ — ሠራተኛው) ሌላኛው ደግሞ (ባሪያ አሳዳሪው ፤ መኳንንቱ ፤ ቀጣሪ ከበርቴው) ለማምረት ምንም ሳይቸግር የምርቱን ክፍል (ብዙውን) በመውሰድ የሚዘባነነው ነው ። ነገር ግን በእያንዳንዱ የሕብረተሰብ ዘመን ውስጥ ካሉት ሁለት መደቦች ሌላም ሌሎች መደቦች አሉ ። ባልበለጸጉ አገሮች (ቅኝና ግማሽ ቅኝ ግዛት) ውስጥ እስከአሁንም ድረስ — ፊውዳል መሬት ከበርቴዎችና ገበሬዎች — ከገባሮች ጥቂት ከፍ የሚሉት — ጉን ለጉን ካዳበረ የካፒታሊስት መደብና (የውጭ ከበርቴዎችን ሳይጨምር) ከአዳጊው የሠራተኛ መደብ ጋር ባንድነት ይታያሉ ።

በመደቦች መካከል ያለው ትግል ሰውን በጣም ወደ ከፍተኛ የምርት ዕድገት ወደፊት እንዲገፉ ይረዳዋል ። አንድ የተቀናበረ አብዮት ብቅ ሲል ከፍተኛው የምርት ሥልት እንዲመጣ ይሆናል ወይም በሠፊው ይስፋፋል ። በእንግሊዝ ለካፒታሊዝም ከፍተኛ ምርት መንገድ የከፈተው የክሮምዌል አብዮትና በ፲፮፻፹፰ በተካሄደው «በአንጸባራቂው አብዮት» ነው ። ይህን ዓይነት ሁኔታ ፈረንሣ



ይ የደረሰችው በ፲፯፻፹፱ኙ ትልቁ የፈረንሣይ አብዮትና ተከታትለው በተካሄዱት ንቅናቄዎች ነው ።

ይሁንና ማርክስ ዕውነቶችን ሁሉንም በጠቅላላ ለማተት አልፈለገም ነበር ። በተለይም በደንብ ያተተው በኖረበት ዘመን ያሉትን ትግሎች ነው ። ለምን ? በመደቦች መካከል ያሉ የትግል ሕጎችን ለማግኘት ሲል ።

ይህ የውጊያው (የትግሉ) ቴክኒካዊ ዝርዝር ጥያቄ አይደለም ። ማርክስ የአየው ፤ — የሕብረተሰብን ዕድገት ለመገምገም የሚያስችለው በአብዮታዊ ወቅት ዋናው ፤ በመደብ ኃይሎች ውስጥ አዲስ ዓይነት የአመራረት መልክ ሊአመጣ የሚችለውን ሚና የሚጫወተውን መለየቱ ላይ ነው ። በአውሮጳ በተለያዩ ሀገሮች በተለይ በ፲፰፻፵፰ ዓ.ም. የሆኑትን አብዮታዊ ድርጊቶች በመመርመርና በማጤን ይህ እንዴት ሊገኝ እንደሚችል ታይቷል ። ለምን ? እንበል። በሁሉም አገሮች የተወሰኑ አጠቃላይ ገጽታዎች (ጠባዮች) ታይተው በመረጋገጣቸው ።

በአብዮት ጊዜ የሚረጋገጡት እነዚህ አጠቃላይ ገጽታዎች ወይም ሕጎች ምንድናቸው ?

በመጀመሪያ ደረጃ ፤ አብዮታዊ ትግሉ ሁልጊዜ የሚመራውና የሚቀዳጀው በአዲሱ ሥልተምርት ሥልጣን ላይ በሚወጣው መደብ ነው ። ግን በራሱ ብቻ አይደለም ። ለምሳሌ — በ፲፯፻፹፱ በትልቁ የፈረንሣይ አብዮት ጊዜ ብቅ ካለው የካፒታሊስት መደብ ጋር ገበሬዎች — የፊውዳሊዝም አምራች መደቦች — ትናንሽ ነጋዴዎች ፤ ነጻ የእጅ ባለሙያዎች እና የወደፊቱ የሠራተኛ መደብ ቡቃያዎችም ነበሩበት ። በጠቅላላ እነዚህ የሕዝብ ክፍሎች

ከአሮጌው ሥርዓት የገዥ መደብ ተጻራሪ በመሆን በአብዮ
ታዊ ትግሉ ተሳትፈዋል ። ምክንያቱም በተለያዩ ፍላጎት
የተነሳ ሁሉም የአሮጌው ሥርዓት መኖር ማለት የጭቆና
መቀጠል እንደሆነ በመገንዘብ ትግላቸውን ቀየሱ ፤ ችግር
በችግርም ደቀኑበት ።

ሁሉም ተከታታይ ገጠመኞች ማርክስ ያቀረበውን
መደምደሚያ አረጋገጡ ። «ማንኛውም እውነተኛ አብ
ዮት ፤ በሥልጣን ላይ ያለን የገዥ መደብ ለመደርባት ዓላ
ማው የሆነ ፤ ሥልጣኑን የሚረከበው መደብ አብዮት ብቻ
ሳይሆን ፤ በገዥው መደብ ለተጨቆኑ እሽከላ ለተደቀነባ
ቸው ሁሉ ነው» ያለውን መሆኑ ነው ። በአንድ የታሪክ
ዕድገት የተወሰነ ደረጃ ፤ አብዮቱ የሚመራው ከፊውዳል
ዘውደኛና የመሬት ከበርቴ አንጻር በመቆም በካፒታሊስቱ
ነው ። ይሁንና የሠራተኛው መደብ ከዳበረ ግን በአብዮቱ
ውስጥ ተሳትፎ የሚኖራቸውን ሁሉ እሱ ነው ሊመራ የሚ
ችል ። በሌላ አነጋገር ፤ በማንኛውም አብዮት ፤ ታሪክ እንዳ
ሳየን ከሆነ የሠፊው ሕዝብ ክፍል በዋናው ጠላት ላይ የሕ
ብረት ግንባር ይፈጥራል ። አዲስ የሚሆነው ፤ በመሬት
ከበርቴዎችና በካፒታሊስቶች አንጻር ተቃራኒ በመሆን
የሠፊውን ሕዝብ ግምባር የሚመራው ሠራተኛው መደብ
መሆኑ ነው ።

አዲስ ዓይነት የምርት ሥልት ለማምጣት አዲሱን
መደብ በሥልጣን ላይ የሚአስቀምጠው አብዮት ፤ በም
ርት ላይ ባላቸው የመጋጨት ፍላጎት ምክንያት በመደቦች
መካከል የሚካሄድ የማያቋርጥ ትግል የመጨረሻ ነቁጥ
( Nodal Point ) ነው ።

በኢንዱስትሪያል ካፒታል የመጀመሪያ ዘመን ቅራኔ
ዎቹ ተሠራጭተው ነበር ፤ እናም ጥያቄዎቹ በጣም አብዛኛ



ቹ በምን ዳዕና በአንዳንድ ፋብሪካዎች የአሠራር ሁኔታ
ዎች ላይ ነው የአተኮሩት ። «ግን ከኢንዱስትሪ ዕድገት
ጋር ወገ አደሩ በቁጥር ብቻ አልነበረም የጨመረው ፤
በአንድ ቦታ በብዛት ታፍጎ ፤ ጥንካሬው አድጎ እናም
ጥንካሬው ይበልጥ እንደሚሆን ይሰማው ነበር ። »
( Communist Manifesto )ሠራተኞች ግጭቱን በብሔራዊ
ደረጃ ሊአካሄደው ወደሚችል ከፍተኛ ድርጅት የሚአድግ
የሙያ ማሕበር ይመሠርታሉ ። የበላተኞቻቸውን ፍላጎት
ለማሟላት የሕብረት ሥራ — ማሕበሮችን ያቋቋማሉ ።
እናም በአንጻሩ መጠቅ ባለ ደረጃ እነርሱን የሚወክልና
የመደብ ፍላጎታቸውን ጥቅም በማሟላት የሚዋጋና የሚ
መራ የራሳቸው የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ይኖራቸዋል ።

## እንዴት ነው ትግሉ (ውጊያው) የሚመራው ?

ማርክስ ፤ የሠራተኛውን መደብ ፓርቲ ዓላማ ሲመለ
ከት ፤ «የካፒታሊስቱን የገዥ መደብ ለመደርባት የሚዘጋ
ጅና የሚአደራጅ ፤ የሠራተኛውን መደብ ገዥነት የሚመ
ሠርትና አዲስ ዓይነት ሥልተ—ምርት የሚገነባ ነው ፤
በተለይም ሶሻሊዝምን ።» ይላል ።

የሠራተኛውን መደብ ድርጅቶች በተለይም የሙያ
ማሕበሮችን (የሠራተኛውን መደብ ጥንካሬ የጨመረው
ንና «ጥንካሬው ይበልጥ እንዲሠማው» ያደረገውን) ለማዘ
ጋጀት ዙሪያ ገባ የሆነ ከፍተኛ ርዳታና ዕድገት የሰጠው
ፓርቲው ነው ። ለጊዜያዊ ፍላጎታቸው በማንኛውም ትግል
ውስጥ ለገቡት ለማንኛዎችም የሠራተኛ ክፍል ራሱን አሳ
ትፏል ፤ ረድቷል ። እንበልና ፡— ለከፍተኛ ምንዳዕ ፤ የተ
ሻለ የሥራ ሁኔታና ወዘተ . . . . ። በእነኚህ ትግሎች አማ
ካኝነት ሠራተኞች ብዙ ጊዜ የተሻለ ሁኔታን አግኝተዋል ፤

የጦርነታቸው ፍሬ ያለው (እምብርቱ)
ግን «እውነተኛው የጦርነታቸው ፍሬ ያለው አይደለም ፤ እየሰፋ በሚሄደው
በጊዜያዊ ውጤቶች አይደለም ፤ እየሰፋ በሚሄደው
የሠራተኞች ሕብረት ነው ።» በማርክስ የተሰጠውን
ትንተና አንዳንድ ግምገማዎች ( Critics ) እንደሚተ
ረጕሙት ማርክሲስቶች በካፒታሊዝም ውስጥ ኑሮ እንዲ
ሻሻል አይፈልጉም፤እንዲአውም አጽንአተ — ነገሩ ለአ
ብዮት ማዘጋጀት ብቻ ነው ይላሉ ። ይህ ትክክል አይ
ደለም ። በእርግጥ ማርክስ ሠርቷል ። እና ማርክስስቶችም
ሁልጊዜም ሠርተዋል ። ይህን የተመለከቱት የሕግ
ቦችን ሕብረተሰባዊ ኑሮ እንደ የሕብረሰብ አስተማ
ማኝ ዕውነቶች መሻሻል ውጤት በማድረግ ነው ። ማርክስ
በዚህ ምንባብ ውስጥ በደንብ የአተኩር የነበረው የሚ
ቀጥለውን ነው ፤ እንኚህ በሰላም የተገኙ ውጤቶች አስ
ተማማኝ አይደሉም እናም የካፒታሊስትን ሥርዓት ሳይለ
ውጡ ትተውታል ፤ እርግጥ ለሠራተኛው መደብ ለመጨ
ረሻ ዓላማው ጥንካሬውን እንዲአዳብር ረድተውታል—
ለካፒታሊዝም ማከተም ። ስለዚህ በዚህ የትግል ወቅት
ሠራተኞች የጋራ ፍላጐት ያላቸው አንድ መደብ በተለይም
በካፒታሊስቱ አንጻር የሚቆም መደብ አባል መሆናቸውን
ተረድተዋል ። የሠራተኛው መደብ ፓርቲ ሠራተኛው ዕድ
ገቱ ወደ ፊት እንዲገፋ በመርዳት ፤ ለምን የካፒታሊስት
ሥልተ ምርት እንስካሁን እንደቀጠለ ፤ በመደቦች መካ
ከል ያለው ትግልም መስፋት እንዳለበትና ምጣኔ—ሀብታዊ
ቀውሶችና ጦርነቶች ግን በሠራተኞች ላይ አደገኛ የሆኑ
ሥቃዮች እንደሚአመጡ ፤ ግን ግጭቶችና መከራዎች እን
ደሕግ ሆኖ የካፒታሊስቱን መደብ በኃይል ፈንቅሎ የመ
ጣል ተሳትፎ መኖር እንዳለበት የሚአሳዩና የሚገፋፉ መሆ
ናቸውን ያብራራል ፤ ያስተምራል ።



ይህ አጠቃላይ መደምደሚያ ባለፈው ታሪክ ደርሷል ፤ እንደገናም የማርክስ ስለመንግሥት ያካሄደው ጥናት አጠናክሮታል ።

አንዳንድ ጊዜ መንግሥት እንደፓርላማዊ ሂደት ሆኖ ተወስዷል ። ማርክስ ግን የመንግሥት ታሪካዊ ዕድገት ከተወካይ ተቋሞች የተለየ እንደሆነ ጠቁሟል ፤ እንዲአውም ፡— መንግሥት የገዥው መደብ ፍላጐቱንና ምኞቱን ወደሰፊው ሕዝብ የሚአስተላልፍበት ፤ እንዲቀበሉ የሚአደርግበት ነው ። በጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓተ—ማህበር መንግሥት አልነበረም ፤ ግን ሰብአዊ ሕብረተሰብ በመደቦች ሲከፋፈል ፤ በተፈጠሩት መደቦች መካከል የፍላጎቶች መቃረን ተነሣ ። ተጠቃሚው ክፍል ጥቅሙን ለማስከበር በቀጥታ በራሱ በሚመራ በታጠቀ ኃይል ካልተጠበቀ በቀር የማይቻለው ሆነ ። «ይህ ኃይል በማንኛውም መንግሥት ውስጥ አለ ፤ የታጠቁ ሰዎች ብቻ የያዘም አይደለም ፤ ግን ከማቴሪያል ማጠናከሪያም ማለት ከእሥር ቤቶችና ከተለያዩ የመጨቆኛ ተቋሞችም ጋር ነው ።» (ኤንግልስ ፤ በሌኒን መንግሥትና አብዮት በሚለው መጽሐፍ የተጠቀሰ) ይህ ኃይል ሁልጊዜ ያለውን ሥርዓት የመጠበቅ ተግባር አለው ፤ (እንበልም፤ ያለውን የመደብ ክፍልና ተጠቃሚ መደብ) ሁልጊዜ ራሱን ከሕብረተሰብ በላይ ፤ ለማንኛውም መደብ« አድላዊ» ያልሆነ አድርጎ ይቀርባል ። ግን ተግባሩ« ሕግንና ሥርዓትን ማስጠበቅ» ብቻ ነው ። ይሁንና ሕግንና ሥርዓትን ሲአስጠበቅ ያለውን ሥርዓት ይጠብቃል ። ሥርዓቱን ለመለወጥ በሚደረግ ዝንባሌ ወይም ሙከራ ላይ ተጻራሪ በመሆን ገብቶ ሲአማስል ይገኛል ። በማንኛውም የባዘቦት ሥራው ፤ የመንግሥት መሽከርከሪት ቀስቃሽ ( Seditious ) ሰዎችን ይይዝና ያስራል ። ቀስቃሽ ጽሑፎችንም (የፕሮፓጋንዳ ሊትሬቸር) ያግዳል ሌላ ሌላም . . . ሰላማዊ በሆነ መን

ገድ መሆኑ ነው ። ግን እንቅስቃሴው ሰፋ ያለ ይዘት ሲኖ
ረው በግልጽ በፖሊስ ኃይል ይጠቀማል ፤ አስፈላጊም ከሆነ
በጦር ሠራዊቱ ። ይህ የኃይል መዋቅር ነው የገዥውን
መደብ ፍላጎት የሚአከናውን ፤ እናም ይህ ነው የመንግ
ሥት ዋናው ገጹ ፤ መልኩና ጠባዩ ።

ታዲያ ይህ የመንግሥት መሽከርከሪት — በፓርላማ
ቁጥጥር ሥር ነው ወይስ በሌላ ተወካይ ተቋም ሥር ? በአ
ንድ ሀገር ተወካይ ተቋሙ እስካሁን ድረስ ወክሎ የሚቆ
መው የገዥውን መደብ ከሆነ ፤ መንግሥታዊ መሽከርከ
ርከሪቱን ይቆጣጠረዋል ማለት ነው ። ግን ፓርላማው
ወይም ሌላ ተቋሞ የገዥውን መደብ በትክክል ወክሎ ባይ
ቆምና የገዥውን መደብ ለመበጥበጥ የሚአስችል የርምጃ
ሙከራ ቢአካሂድ ፤ የዚህ ጊዜ በግልጽ መንግሥታዊ መሽከ
ርከሪቱን ሊቆጣጠረው እንደማይችል በቶሎ ይታያል ።
ታሪክ ፤ የገዥውን መደብ ያልወከሉና ሌላውን ክፍል ለማ
ገልገል ያሰቡ ብዙ ተወካይ ተቋሞች ሞልተውታል ፤ ይሁ
ንና ተዘግተዋል ወይም በጦር ኃይል በአስፈላጊ ጊዜ
ተበታትነዋል ። ለምሳሌ — በእንግሊዝ በክሮምዌል ዘመን
አዲሱ መደብ በአሮጌው ሥር ዓት ውስጥ ተንሠራፍቶ
ነበር ፤ ይሁንና በፓርላማዊ ምርጫ ምንም ለመደቡ ጥቅም
አላተረፈም ፤ ይልቁንም የመንግሥቱ ተጻራሪ የሆነና የታ
ጠቀ ሠራዊት በማደራጀት ነው መብቱን ያስከበረ ።

በምርት ሥልቱ ላይ ያለው የገዥ መደብ የመንግሥ
ቱን መሽከርከሪት ቁጥጥሩን ይጠብቃል ፤ የሕዝብ ተወካይ
ተቋሞችን ምን እንደ ሚደርስባቸው የማወቁን ጉዳይ እንተ
ወው ፤ ስለዚህ እውነተኛ የለውጥ ኃይል በነበረው አሮጌ
ሥርዓት ላይ ኃይል ይጠቀማል — ጠቅላላ የኃይል አወቃ



ቀሩን በአዲስ ሥርዓት አምጭዎች ላይ ሲጠቀም የነበረ
ውን ሊመታ ይነሳል ።

ይህ የማርክስ መደምደሚያ ባለፉት ታሪኮች ላይ
ደርሶ የነበረው ባሁኑ ወቅት አዳዲስ በሆኑ ታሪካዊ ወቅ
ቶች ተደግፏል ። ለምሳሌ የፋሽዝም ጠቅላላ መሠረት
የሚገነባው የሁሉንም አይነት ተወካይ ተቋሞች በጦር
ኃይል በመሰባበር ነው ። እውነቱ የፋሺስት ድርጅት እንዲ
ሁ የአሮጌው አይነት መንግሥት ሳይሆን — (በዋናው አተና
ተን ከተመለከትነው ምንም አይደለም) — አዲስ መልክ
ነው ። በስፔይን በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. ተደርጎ የነበረው የፍራ
ንኮ ብጥብጥ በሕገ መንግሥታዊ የፓርላማ ምርጫ ተመ
ርጦ በነበረው መንግሥት ላይ ተጻራሪ በመሆን የወሰደው
እርምጃ የተወካይ ተቋሞች ከታጠቀው የጦር ኃይል ውጭ
ያላቸው ቁጥጥር ምን ያህል አነስተኛ እንደሆነ ያሳያል ።

ግን እንዴት ነው የገዥው መደብ የግል መንግሥታዊ
መሽከርከሪት ቁጥጥሩን የሚጠብቀው ፤ በተለይም የጦር
ኃይሎች ሕገ መንግሥታዊ ሆነው ፓርላማው እንዴት
ይቆጣጠራል ?

መልሱ የሚገኘው በመንግሥት የመሽከርከሪት
ጠባይ ውስጥ ነው ። በማንኛውም አገር በጦር ኃይሉ ፤ በዳ
ኝነትና በአጠቃላይ በአስተዳደሩ አገልግሎት ውስጥ ሁሉ
ያሉ ከፍተኛ ቦታዎች የተያዙት በገዥው መደብ አባሎች
ወይም በታማኝ አገልጋዮች ነው ። ይህ በሚሰጠው ሹመ
ትና በሚመረጡት ሰዎች ይረጋገጣል ። በተወካይ ተቋሞች
ውስጥ መጠቅ ያለ ዲሞክራሲ ሊኖር ይችል ይሆናል ።
ይሁንና ይህን በመጠቀም ጠንካራ ወደሆነው የመንግሥ
ታዊ መሽከርከሪት ማዕከላዊ እምብርት ዘልቆ ለመግባት

በዚህ አጠቃላይ ትንተና ላይ በመመርኰዝ ሌኒን
የካፒታሊዝም ኢምፔሪያሊስት ደረጃ ሲመጣ ከከፍተኛ
ምጣኔ — ሀብታዊ ቀውሶች ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጦር —
ነቶችና በሌላ በኩል የሠራተኛው መደብ አብዮቶችና በቅ
ኞችና በግማሽ ቅኝ ግዛቶች ውስጥ ያሉ የተጨቆኑ ሕዝቦች
የኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛን በመቃወም ከማመጽ ጋር
ነው የሚከሠተው ብሎናል ።

በጥቂት ቡድኖች እጅ የካፒታል መድለብ ማለት የእ
ነኝህ ጥቂት ቡድኖች በመንግሥት መሽከርከሪት ላይ እጅ
ግና በጣም ከፍተኛ ኃይል ማግኘት ነው ። ስለዚህም የተለ
ያዩ አገሮች ፖሊሲ የእነዚህን ጥቂት ጠባብ ክፍሎች ፖሊሲ
በተቀራረበ ሁኔታ ተባብረው ማለት ነው ። ይህ ጠባይ
ነው በየአገሩ ያሉት የፋይናንስ ካፒታል ቡድኖች የውጭ
ተወዳዳሪዎቻቸውን ፤ በኩታና ፤ በሌላም መንግሥታዊ
ፕሮግራሞች በመጨረሻም ደረጃ በጦርነት ለመዋጋት ያስቻ
ላቸው ።

ለምንድነው በነዚህ ተወዳዳሪ ቡድኖች መካከል ያለው
ግጭት ሊቀር የማይችል የሚሆነው ? ለምንድነው ዓለምን
በመካከላቸው ለመቃረጥ የማይ ስማሙት ?

የተለያዩ አገሮች የሞኖፖሊ ቡድኖች የዓለምን ገበያ
ለመከፋፈል ስምምነት አድርገው እንደነበረ አላይ ተጠ
ቅሶ ነበር ።   በሥውር መልኩ ፤ ይህ የውድድርን ፍጹም
መጥፋት ወደ ሚአረጋግጥ ሁኔታ የሚወስደን ይመስላል ።
እናም ነዋሪ የሆነ ዓለም አቀፋዊ የፍላጎት ጸባይ ዓይነት
የተፈጠረ ያስመስላል ። ነገር ግን ሌኒን ይህ ዓለም አቀፋዊ
ስምምነት እስከመጨረሻ ዘላቂ አለመሆኑንና ሊቀጥል እን
ደማይችል ጠቁሟል ። ለምሳሌ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. የተደረገው

ስምምነት ከአምራች ኃይሎች ጋር ባለው ግንኙነት ግል
ትም በዚያን ጊዜ ባሉት የተለያዩ ቡድኖች እንበልና በእን
ግሊዝና በፈረንሣይ ፤ በጀርመንና በአሜሪካ መካከል የገ
በያዎችን መከፋፈል መሠረት በማድረግ የተፈጸመ ነው ።
ይሁንና ያልተስተካከለ ዕድገት የካፒታል የዕድገት ሕግ
ነውና ይህ ዓይነት ስምምነት ከተደረገ ከጥቂት ዘመናት
በኋላ ፤ የጀርመን የአምራች ኃይል ቡድን ወይም የአሜሪካ
ወይ የሌላው አድጎ ጨምሮ ሊሆን ይችላል ። ስለሆነም
ይህ የአደገው ቡድን ፊት ባለው የገበያ ክልል (በዓለም
ውስጥ) ተወስኖ ሊኖር በፍጹም አይፈቅድም ። ስምምነቱን
ያወግዛል ፤ እናም ሌላው ቡድን በአፋጣኝ ካልተቀበለው
(ካላመነበት) ለገበያ ሲባል አዲስና መራራ ትግል ይጀም
ራል ። በእውነትም ፤ ለእነዚህ ዓይነት ስምምነቶች ሁሉ
ይህ ነው ዕጣቸው ። የአልተመጣጠነ ዕድገት ሕግ የሚው
ለው ለተወሰኑ የኢንዱስትሪያል ቡድኖች ብቻ ሳይሆን ፤
በአጠቃላይ በተለያዩ አገሮች ካፒታልም ላይ ነው ። እንና
ገር ከተባለ ፤ ምጣኔ — ሀብታዊ ስምምነቶች በተለያዩ
አገሮች ባሉ የፋይናንስ ካፒታል ቡድኖች መካከል በሚደ
ረግ የማያቋርጥ የንግድ ጦርነት ውስጥ መጫረያዎች ብቻ
ናቸው ። ሌላም አይደሉ ።

ምጣኔ ሀብታዊ ጦርነት ብቻውን ምንም መፍትሔ
አይሰጥም ። ስለሆነም ፤ የፋይናንስ ካፒታል ቡድኖች በሃ
ገራቸው ባለው የመንግሥት መሽከርከሪት በኩል በተወዳ
ዳሪዎቻቸው ላይ የታሪፍ ድንበር በመሥራት ፤ ወደ ውስጥ
በሚገባ ሸቀጥ ላይ መጠን (ኮታ) በመወሰን ፤ ከሌሎች
አገሮች ጋር የተሻለ የንግድ ስምምነት ለማዘጋጀት በመ
ሞከር ፤ ሞኖፖሊአቸውን በሚአንቀሳቅሱበት አካባቢ ግዛ
ታቸውን ለማስፋፋት ይታገላሉ ። እናም በተወዳዳሪአቸው

ከሠፊው ሕዝብ በተውጣጣው ብሔራዊ ዘብ ተተካ ። የነ ኝህና የሌሎችም የኮሚውኑ ባሕሪዎች ዋና ተግባር የእገዛገ አወቃቀሩን ፤ የመሸከርከሪቱን ኃይልና መጨቆኛውን ከሠ ራተኛው መደብ ለማቅረብና ለማምጣት ነው ። ማለትም ካለፈው የካፒታሊስት ቁጥጥር እንጻር የሠራተኛውን ቁጥ ጥር ለማረጋገጥ ። ይህ አዲስ ዓይነት መንግሥት የዲሞክራ ሲያን ጦርነት ኢየሸነፈ ነበር ። የተራው ሕዝብ የራሱን ኑሮ በዚያን ወቅት በመቆጣጠር በኩል ያለው ድርሻ ከፍ ተኛ መስፋፋትና ዕድገት ነበረው ።

ስለሆነም ኤንግልስ ስለፓሪስ ኮሚውን ሲጽፍ ፡— «የወዛደሩ አምባገነንነት ነበር» ብሎታል ። ማርክስና ኤንግልስ ስለኰሚውኑ በአቀረቧቸው ሐተታዎች ተቃራኒ ነት አለ ? ማለትም ከፓርላማዊ ዲሞክራሲ ሲነጻጸር የዲሞ ክራሲን በራስ ቁጥጥር ሥር የማስፋፋት ሂደት በኰሚውኑ መብለጡና ፤ በሌላ መንገድ «የሠራተኛው አምባገነንነት ነው» በማለቱ መካከል ? መልሱ «የለም» ነው ። በቀላሉ ሁሉም ሀሳቦች አንድን ዕውነት በተለያዩ መልክ ነው የገለጹት ። የሠፊውን ሕዝብ ፍላጎት ለማራመድ ሲባል «አዲስና ዲሞክራሲአዊ መንግሥት» ተቋቋመ ። ይህም ደግሞ ሊራመድ የሚችለው አምባገነናዊነትን በተግባር በማዋልና በመለማመድ ሆኖ በሠፊው ሕዝብ ፍላጎት ላይ ተጻራሪ በመሆን ሁሉንም ዘዴዎች ማለትም ከፋይና ንስ አሻጥር ጀምረው በመመሪያ እስከ መቋቋም ድረስ ያሉ ትን ሥልቶች በመያዝ የጥቂቶችን አምባገነንነት ለማስፈን የሚጣጣረውን መደብ ለመደምሰስ ኃይል በመጠቀም ነው።

በቅርቡ የተፈጸሙት የሠራተኛ መደብ አብዮት ገጠ መኖች ማርክስና ኤንግልስ ከ፲፰፻፸፩ ዓ.ም. ኮሚውን ገጠ መኖች ያገኟቸውን መደምደሚያዎች አረጋግጠዋል ። በሩ



ሲያ በ፲፱፻፭ አብዮት ዛሩን ለመዋጋት ከሠራተኛው መደብ ክፍሎች በተውጣጡ ተወካዮች ኮሚቴዎች ተቋቁመው ነበር ። እንደገናም በመጋቢት የ፲፱፻፲፯ ዓ.ም. አብዮት ወዲያ ውኑ አብዮታዊ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ከበፊቱ ተመሳሳይ የሆኑ ሶቪየቶች ተቋቁመዋል ። ሌኒን እንደተመለከተው ፡« ከፓ ሪሱ ኮሚውን ጀምሮ ከሠራተኛው መደብ ዕድገት ጋር በማደግ እነዚህ ተወካይ አባሎች ፤ በመጀመሪያ ደረጃ ከፋ ብሪኮች ፤ አካባቢ የተውጣጡ ት (ግን ደግሞ ትግሉ ሲስ ፋፋና ሲቀጥል ከወታደሩና ከገበሬውም ጭምር) ፤ አዲሱ የሠራተኛው መደብ መንግሥት እንዴት እንደሚሠራ የሚ አሳይ መልኮች ነበሩ ። »ብሏል ። ተወካዮች ከሠራተኛው በቀጥታ ተውጣጥተው በመራጮቻቸው በተጠሩም ጊዜ በማንኛውም ወቅት ወደ ቦታቸው የሚመለሱ ናቸው ። ይህም የካፒታሊስቱ ተጽዕኖ በምንም ውሳኔ ላይ ሊጫወ ተው የሚችል ሚና እንደሌለውና ስለዚህም ፤ የሠራተኛው መደብ እውነተኛ ፍላጎት ሊጠበቅና ሊራመድ እንደሚ ችል ያሳያል ማለት ነው ። በእንጻሩም ይህ ሊሆን የሚች ለው ማንኛውንም ዘዴ በመጠቀም አዲሱን የሶቪየት መን ግሥት ለማጥፋት በሚጣጣረው አሮጌው የገዥ መደብ ላይ አምባገነንነትን እና ኃይልን በማስፈን ነው ።

የሠራተኛውም መደብ አምባገነንነት ዕውነተኛ ዲሞ ክራሲ የተገኘውና የተጠቆመው በማርክስ በኮሚውኒስት አዋጅ ምንባብ ውስጥ ነው ፡« ከዚህ በፊት የነበሩት ታሪ ካዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የጥቂቶች እንቅስቃሴዎች ነበሩ ፤ ወይም በጥቂቶች ፍላጎት የተካሄዱ ናቸው ። የወዛደሩ እን ቅስቃሴ ግን በራሱ ንቃት የሚካሄድ ነጻ የሆነ የሠፊው ሕዝ ብ ንቅናቄ ፤ በሠፊው ሕዝብ ፍላጎት የተመሠረተ ነው።» ብሏል ።

እላይ የተነገሩት ሀሳቦች እንደሚያረጋግጡት የሠራተኛው መደብ አብዮት ድል ማድረግ በአንድ ጊዜ ሁሉንም የመደብ ትግል እንደማያቆም ማርክስ አስገንዝቧል ። እንዲያውም ፤ በመጀመሪያ ጊዜ የሠራተኛው መደብ ተቃራኒ በመሆን ፋንታ ለመጀመሪያ ጊዜ መንግሥታዊ መዋቅሩን ከጕኑ የሚያደርግበት የመታጠፊያ ነጥብ እንዳለ ያሳያል ። ሌኒን በጥር ወር ፲፱፻፲፰ ዓ.ም. የዚህን ነጥብ ሁኔታ ለሶቪየት ኮንግሬስ ተናግሮ ነበር ። ሀሳቡ የሚከተለውን ያጠቃለለ ነው ፦ ባቡር ውስጥ ነበር ፤ እናም ሊገባው ያልቻለ ንግግር በዚያው ውስጥ ይካሄዳል ። በኋላ ከሰዎቹ አንዱ ወደርሱ ዞር ብሎ «ይህች አሮጊት ሴትዮ የተናገረችውን አዲስ እንቆቅልሽ ታውቃለህ ?» እንዲህ አለች ፦— ‘ጠመንጃ የያዘን ሰው መፍራት አስፈላጊ አይደለም ። አንድ ቀን በጫካ ውስጥ እንዳለሁ አንድ ባለጠመንጃ ሰው አገኘሁና እራሴ የለቀምኩትን እንጨት በመውሰድ ፋንታ በተጨማሪ እንድለቅም እራሱም ረዳኝ አለች» አለው ። ይህም ማለት ከእንግዲህ ወዲያ ያለው የኃይል መዋቅር ለሠራተኞች ተቃራኒ ሳይሆን ፤ ግን ሠራተኛውን ይደግፋል ፤ እንዲያውም ሠራተኞችን ወደኋላ ለመጐተት የሚሞ ክሩትን ብቻ ነው የሚጻረረው ።

እላይ ከታተተው እንመልከትና ፦— ስለዚህ እንዲህ አይነት ሰዎች በእርግጥ ሠራተኛው መደብ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላም ይኖራሉ ። የድሮው የገዥ መደቦች በሌሎች አገሮች የገዥ መደብ እየተረዱ ግልጽ የሆነ ጦርነት በሠራተኛውም መደብ መንግሥት ላይ ለማስነሳት እስከ ሚቻላቸው ድረስ የጦር ኃይል ይሰብስባሉ ። የ፲፰፻፸፩ ዓ.ም. ኮሚውን ድል የሆነው በዚህ መንገድ ነው ። ጀርመኖች በብዙሺ የሚቆጠሩ የፈረንሳይ እሥረኞችን ከፓሪስ ውጭ በቨርሳይልስ የተጠራቀሙ አድኅሪዎችን ለማ



ጠናከር ሲባል ፈቱዋል ፤ ስለሆነም አድኅሪው ሠራዊት በእነሱ ተረድቶ ከኮሚውኑ ፓሪስን እንዲወስድና ኮሚውኑን የረዱትን ሰዎች ጭዳ እንዲያደረግ ብዙዎችን እንዲሰዋ ረድቶታል ። በ፲፱፻፲፰ እና በ፲፱፻፳ መካከል ፤ በሩሲያ የሶቪየት መንግሥትን የገጠሙት የዛሩ ደጋፊ ሠራዊቶች ብቻ ሳይሆኑ የውጭ ወራሪ ኃይሎች ሠራዊቶችም ጭምር ነበሩ ። የእንግሊዝ ፤ የፈረንሳይ እና የዩናይትድ ስቴትስም ተዳምሮ ። በ፪ኛው የዓለም ጦርነት ሶቪዬት ሩሲያ የናዚ ወረራ ገጥሟታል ። ስለዚህም ታሪክ በማርክስ የታተተውን መደምደሚያ ያረጋግጣል — እንበልም« ሠራተኛው መደብ ራሱን ለማዳን በሶሻሊስት አያያዝ መሠረት የምርት ሥልቱን እንደገና በሚአደራጅበት ጊዜ ያለውን የበላይነት ቁጥጥር ለማረጋገጥ ለረጅም ጊዜ የራሱን መንግሥታዊ ድርጅት ከጠላት መከላከል አለበት» ያለውን መሆኑ ነው ።

የ፲፰፻፸፩ ዓ.ም. የፓሪስ ኮሚውንና በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም. የተመሠረተው የሩሲያውያን የሶቪየት መንግሥት የመጀመሪያዎቹ የሠራተኛው መደብ መንግሥት መልኮች ናቸው ። በ፪ኛው የዓለም ጦርነት መጨረሻ ላይ የሠራተኛው መደብ ንቅናቄ ጥንካሬና የኃያሉ የሶቪየት መንግሥት መኖር ወደ ሶሻሊዝም የመሸጋገሪያ አዲስ መልኮችና አዲስ መልክ ያለው የሠራተኛው መደብ መንግሥት እንዲኖር አስችለዋል ። እነኝህን በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ በተለይ እንመለከታቸዋለን ።

ማርክስ በትክክል ሶሻሊዝምና የዚህን ከፍተኛ ደረጃ ኮሙኒዝም ሲልም ምን ማለት እንደሆን በሚቀጥለው ምዕራፍ ተገልጿል። ነገር ግን የመደብ ትግልና መንግሥት የሚለውን ርዕስ ከመተዋችን በፊት የማርክስ አመለካከት የመጨረሻ ውጤት ሂደት መታተት ይኖርበታል ። የመደብ

ትግል እናም ከእርሱ ጋር የገዥውን መደብ ፍላጐት ለመ
ጠበቅ የሚቋቋመው የመንግሥት መዋቅር የመጣው የሰብ
ዓዊ ሕብረተሰብ በምርት ላይ ፍላጐታቸው በሚጋጩ መደ
ቦች በተከፋፈለ ጊዜ ነው። በታሪክ ውስጥ ሰብአዊ ሕብረ
ተሰብ በመደቦች ተከፋፍሎ እስከቆየ ድረስ የመደብ ትግ
ልና መንግሥትም በዚያው ይቀጥላሉ። ግን፣ ሠራተኛው
መደብ ሥልጣን በሚወስድ ጊዜ በመደብ መከፋፈልን ለማ
ስቀረት ትግል ያካሂዳል — ለማለት የተፈለገው፣ አንደኛው
መደብ በሌላው መደብ ጉልበት መጠቀም የማይችልበት
አዲስ የአመራረት ሥልት ለማምጣት የሚደረገውን ትግል
ነው። በሌላ አነጋገር፣ በአጠቃላይ ሁሉም ሕብረተሰቡን
በሙሉ የሚአገለግሉበትና መደብ አልባ ሕብረተሰብን ለመ
መሥረት መሆኑ ነው። ይህ ዓይነት ሂደት ሲጠናቀቅ (በዓ
ለም አቀፍ ደረጃ) ምክንያቱም የተለያዩ ፍላጐት ያላቸው
መደቦች አይኖሩምና የመደብ ግጭቶች የሉም፣ ስለዚህ የመ
ንግሥት አስፈላጊነት ይቀራል — የኃይል አወቃቀር የአ
ንድን ክፍል ፍላጐት ለመጠበቅና የሌላውን መቃወሚያ
የሚሆነው ፋይዳ የለሺ ይሆናል። መንግሥት ይሟሽሻል፣
ይከስማል — ከአንዱ ደረጃ ወደሌላውም ተጠያቂነት አይ
ኖረውም፤ በማዕከላዊ መሽከርከሪትንትሊኖር የሚችለው
የምርት ማደራጀትና ማከፋፈል ሥራ ነው። ኤንግልስ እን
ዳስቀመጠው፦ «አገዛዝ ከሰዎች በላይ የሚለው፣ ነገሮ
ችን በማስተዳደርና የምርትን ሂደት በመምራት ይተካል»።



ምዕራፍ ፮

# የሶሻሊስት ሕብረተሰብ ፤

ካፒታሊዝምን ተከትሎ ስለሚመጣው አዲሱ የሕብረ
ሰብ ሥርዓት በሰፊው የሚአብራራ ዝርዝር መረጃ በማርክስ
ጽሑፍ ውስጥ የትም አይገኝም። ማርክስ፤ ይሁንና ከእርሱ
በፊት እንደጻፉት ሰዎች ዓይነት «ተምኔት» አልጻፈም ፤
ማለትም ጽሑፋቸውን አጠቃላይ በሆኑ የሕብረተሰቡ አሳ
ቦችና ከነዚህም ውስጥ በወጡት እነሱ በኖሩበት ዘመን
እንደተወለዱት በጣም ግልጽ በሆኑ የሕብረሰቡ መርገሞች
ላይ በመመሥረት እንደጻፉት ሰዎች አይደለም። ግን ከሕ
ብረተሰብ ዕድገት አጠቃላይ ሕጎችን በመውሰድ ማርክስ፤
የአዲሱን ሕብረተሰብ ዋና ገጾችን (ጸባዮችን) እና ይህም
ሕብረተሰብ ሊዳብር የሚችልበትን መንገድ መንደፍ ችሎ
ነበር።

በማርክስ የተጠቆመው በጣም ዐይነተኛ ነጥብ (በጣም
ግልጽ ቢሆንም) የአዲሱ ሕብረተሰብ አደረጃጀት በእውነት
ከሆነ በገላጣ ሜዳ ላይ አይጀመርም ያለው ነው። ስለዚህም
«በራሱ መሠረት ላይ የዳበረውን» የሶሻሊስት ሕብረተሰ
ብን በዚያ መልክ መመልከት ዋጋ የለሽነው። የሶሻሊስት
ሕብረተሰብን ጽንሰ — ሀሳብ ለማግኘት ከውስጣቸው ግን
ምንም ነገር ከማናተርፍላቸው፤ የጥሩ ባሕሪዎቹን (ገፆቹን)
ከፍተኛ ቁጥሮች የማሰብና የማቀያየጥ ጥያቄ እንዳልነበረ
ነው። ይህ አቀራረብ በአጠቃላይ ሣይንሳዊ እንዳልሆ
ነና ውጤቱም ከውነት ጋር ሊሰምር እንደማይችል ርግጥ
ነው።

በተቃራኒው አንድ የሶሻሊስት ሕብረተሰብ ፤ ከዚህ በፊት እንደነበሩት የሕብረተሰብ መልኮች ሁሉ ፤ ወደሕልውና ለመምጣት የሚችለው ከእርሱ በፊት ኖሮ በነበረው ሥርዓት መሠረት ነው ። ለማለት የፈለግነው ከካፒታሊስት ሕብረተሰብ የሚወጣ መሆኑን ነው ። ይሁንና በሥርዓቱ ውስጥ ያሉ ምጣኔ ሀብታዊ ፤ ሞራልና ልሂቃዊ (Intelectual) መንገዶች ሶሻሊስት ሕብረተሰብ ከማኅጸኑ የሚወጣበትን የአሮጌውን ሕብረተሰብ የልደት ቀን የሚደግፉ ናቸው ።

ስለ ዕውነት ከሆነ ፤ በየጊዜው በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ያለው ዕድገት ነው ለሶሻሊዝም ጥርጊያ መንገዱን የሚአዘጋጅለትና የለውጡን ባሕሪ የሚጠቁመው ። ምርት ሕብረተሰባዊነቱ እየጨመረ የሚሄደው እያንዳንዱን ነጠላ ነገር ለመሥራት ብዙ ሰዎች ስለሚተባበሩበት ፤ ፋብሪካዎች እጅግ እየሰፉና የምርት ሂደትም በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች ጥሬ ሀብትን ወደአለቀለት ምርት የመለወጥ ሽግግር ላይ ብዙ ሰዎች ስለሚአያይዝ ነው ። በሰዎች መካከል በጣም ትልቅ የሆነ የእርስ በእርስ ጥገኝነት ይኖራል ። አሮጌው የፊውዳል ዘልማዳዊ መተሳሰርና ግንኙነት ከብዙ ጊዜ በፊት በካፒታሊዝም ተበጣጥሶ ነበር ፤ ግን ካፒታሊዝም በዕድገቱ ጊዜ በጣም ሰፋ ያለ ጠባይ ያላቸው ግንኙነቶች መሥርቷል ፤ ይኸስም ይብዛ እያንዳንዱ ግለሰብ በሕብረተሰቡ ላይ በአጠቃላይ የሚደርሰው ነገር ጥገኛ ነው ።

ይህ የካፒታሊስት ምርት ቀዋሚ የሆነ ጠባይ ቢሆንም እውነቱ በሕብረተሰቡ የጋራ ሥራ የሚመረተው ምርት የሕብረተሰቡ ሳይሆን የአንድ ግለሰብ ወይም የቡድኖች ንብረት መሆኑ ላይ ነው ። ስለሆነም የሶሻሊስት ሕብረተሰብን ለመገንባት የሚአስችለው የመጀመሪያ ደረጃ ፤



ሕብረተሰቡ በአጠቃላይ የሚአመርተውን ምርት ለራሱ ጥቅም እንዲአውለው የምርት ማደራጀት ይሆናል ። ይህም ማለት ሕብረተሰቡ በሙሉ በካፒታሊዝም ውስጥ በግል ተይዘው የነበሩትን የምርት መገልገያዎች እንዲአዝገባቸው ፤ የራሱ እንዲአደርጋቸው ማድረግ ነው ።

ነገር ግን ይህን የምርት መገልገያ ሕብረተሰባዊ ማድረግ የሚቻለው አዲሱ ሕብረተሰብ ከአሮጌው የወረሰውን መሠረት ተታኮ ነው ፤ እናም በአንፃሩ ትላልቅ ይዞታዎች ሆነው በሕብረተሰቡ ለመወሰድ አመቺ የሆኑትን እንጂ ሌላውን አይደለም ። የካፒታሊስት ዕድገት ለዚህ አዘጋጅቷቸዋልና ። በደንብ ከአየነው በባለቤቱና በምርቱ ሂደት መካከል በእነዚህ ድርጅቶች ፍጹም መፋታት አለ ። (የግል ድርጅቱ በጣም ከማየሉ የተነሣ ከባለቤቱ ቁጥጥር ውጭ ሂዷል ።) ግንኙነታቸው የሚታየው ለሸሪክ ባለቤቶች ወለድና ምርት ሲከፈል ብቻ ነው ። ምርት የሚካሄደው በሠራተኞች አስተዳዳሪዎችና ተቆጣጣሪዎች ነው ። ስለዚህ ባለቤትነቱ ለሕብረተሰቡ በሚዛወርበት ጊዜ የሠራተኞችን ሥራ አያደናቅፈውም ። ስለሆነም እነዚህ ትላልቅ ድርጅቶች በአፋጣኝ መወሰድ ይችላሉ ።

በዝቅተኛ አስመራቾች ፤ በዝቅተኛ ነጋዴዎችና ሻጮች ፤ በዝቅተኛ ገበሬዎች ባለቤትነት ሥር ባሉ ዝቅተኛ ድርጅቶች ግን (ባለቤቱ በምርት ውስጥና የአሠራር መልክ ዋና ሚና በሚጫወትበት ማለት ነው) ሁኔታው እላይ እንዳየነው አይደለም ። በትላልቅ ኩባንያዎች ውስጥ በሚገኙት ጥቂት በመቶ በሚቆጠሩት ከበርቴ ሸሪኮች አንፃር ፤ በዳበሩ አገሮች ውስጥ እነኝህ «ዝቅተኛ» የሚባሉት በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ይሆናሉ ። በሌሎች አገሮችም በተለ

ይም የካፒታሊስት እርሻ ባልዳበረባቸው አገሮች ገበሬው የሕዝቡን ብዙ ክፍል ይይዛል ። ከተግባራዊ ሁኔታ አንፃር እንደታየው ለእነኚህ ለተበታተኑ ማምረቻዎችና ማከፋፈያዎች ማዕከላዊ አስተዳደር ለመመሥረት አይቻልም ። ሌላም እነዚህ «ዝቅተኛ» ሰዎች የማይወረሱበትና ድርጅቶቻቸው በአስቸኳይ በመንግሥት የማይወሰዱበት እላይ ከጠቀስነውም በላይ የሆኑ ዋና ሶሻላዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች አሉ ።

ከሕብረተሰብ አንፃር ስናየው የእነኚህ ሰዎችእጅግ በጣም ብዙ የሆኑ ቤተሰቦቻቸው አስፈላጊ የሆነ ሥራ ይሠራሉ ። የሕልውናቸው ሁኔታ በትላልቅ ሞኖፖሊ ድርጅቶች የተገደበ ከመሆኑ ሌላም በሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉት የእነዚህ ዝቅተኛ ሰዎች ችግሮች በሌሎች ሀብት ማየል የተነሣ (በሞኖፖሊስቶች) ተሸፍነው አይታዩም ። ይሁንና አብዛኞቹ ከበርቴአዊና ግላዊ አቋም ነው ያላቸው ፣ በተግባር እንደታየው ወደሶሻሊስት ከሚሸጋገረው ሕብረተሰብ ጥቅም ለማግኘት ነው የሚቋምጡት ። ችግሩ ይህንን የመሸጋገሪያ ጊዜ እነኚህ ዝቅተኛ ሰዎች ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ፣ ጥቅም እንዳገኙበትም እንዲአረጋግጡና በዚህም የአዲሱ ሕብረተሰብ ሥርዓት ደጋፊዎች እንዲሆኑ ማድረጉ ላይ ነው ።

በዚህ አቅጣጫ ታዲያ ምን ምን ተግባራዊ ደረጃዎች መወሰድ አለባቸው ? ኤንግልስ ዝቅተኛ የእርሻ አምራቾችን አስመልክቶ ሲጽፉ ፦ «ተግባራችን ከሁሉም በፊት ግለሰባዊ ምርታቸውንና ባለቤትነታቸውን ወደ ሕብረት ምርትና ባለቤትነት በማሸጋገር ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ነው ፣ በግድ አይደለም ፣ ግን ምሣሌዎችን በማሳየትና ሕብረተሰባዊ ዕርዳታ ለዚሁ ተግባር በመስጠት ነው» ብሏል ።



በሶቪየት ሕብረትና በሌሎችም አገሮች ሶሻሊዝምን በሚገነቡ ይህ የሕብረት ሥራዎችን የማበረታታት ዘዴ በእርሻ ሥራ ላይ ውሏል ። የመንግሥት እርሻዎች ፣ የመንግሥት መኪናዎችና (ማሺኖች) የትራክተር ጣቢያዎች የትላላቅ እርሻን ጥቅምና ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴዎችን በማሳየት ረድተዋል ። በተለያየ መልክ የሚሰጠው መንግሥታዊ ዕርዳታም ከግለሰብ ወደ ሕብረት እርሻ አምራችነት የሚደረገውን ለውጥ አቃሏል ። አንድ አምራች ክፍል የ፳ ሰዎችን ቦታ ይተካል ወይም በመቶ የሚቆጠሩ ትናንሾችን ፣ ትናንሽ አምራቾች በጋራ ማምረትን ይማራሉ ፣ ግለሰባዊ አመለካከታቸው ቀስ በቀስ ወደ ጋራዊነት ይለወጣል ። ትምህርትና የሕይወት ማሻሻያዎች የማህበራዊ ኑሮዎች በትላልቅ የጋራ እርሻዎች ውስጥ ሊሟሉ የሚችሉት ማለት ነው ሂደቱን ያፋጥናሉ ። የጋራ አመለካከት ወደ ሕብረተሰብ አመለካከት ያመራል ። በቻይና ገበሬዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድነት ለማምጣት ወደ ከፍተኛ የዕድገት መልኮች ሊአመሩ የሚችሉ በጣም ዝቅተኛ የሆኑ የሕብረት ሥራዎችን ተጠቅመዋል ።

የሕብረት ሥራ ዘዴዎች ፣ ግለሰብ ባለእጆችንና በኢንዱስትሪ ውስጥ ዝቅተኛ አምራቾችን ለመሰብሰብም በሥራ ላይ ውለዋል ። በየሀገሩ በብዛት የሚገኙትን የተበታተኑ ዝቅተኛ አምራቾችንና አከፋፋዮችን ለመሰብሰብ ግን ዘዴዎችን እንዲህ በቀላሉ በተግባር ማዋል ያዳግታል ። ታዲያ ምን ዓይነት ዘዴዎችን እንጠቀም ? በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ አጠቃላይ መርሆው ሕዝባዊ ድርጅቶችን ማሳደግ ሆኖ ዝቅተኞች ሰዎችን ደግሞ ቀስ በቀስ በከፊል ግብርን በመጨመር በከፊል ደግሞ የተሻለ መገፋፊያ ዕድል በመስጠት ወደሶሻሊስት መረብ ውስጥ ማስገባት ነው ። ይሁንና በቻይና ሁኔታዎች ስለፈቀዱ ፣

ትላልቅ ማምረቻዎችንና የንግድ ሥራዎችን በግል ባለቤቶች ሥር እንዲሆኑ በመተው ፍጹም አዲስ የሆነ የቀስ በቀስ ውርስ ነበር የተካሄደው ። በአዲሱ መንግሥት የብሔራዊ ስሜትና ፍቅር መሠረት በተካሄደው የቻይና ከፍተኛ ዕድገት ፤ ብዙዎቹ ካፒታሊስቶች ከመንግሥቱ ጋር ተስማምቶ የመሥራት ፍላጐት የሌላቸው አልሆኑም ። መንግሥትም በበኩሉ የካፒታሊስቱን ግላዊ ፍላጐቶች በማንኛውም የማሸጋገር ሂደት ጊዜ (ውርስን በሚመለከት) በጥንቃቄ እየተመለከተ ነበር ።

በዚህ የውርስ ሂደት ዋናዎቹ ደረጃዎች በቻይና ፡-
(፩) መንግሥት በግል የተያዙ ድርጅቶችን ኮንትራት በመያዝ ፤ ምርቶቻቸውን በስምምነት ተመን የመግዛት እና በአንዳንድ ሁኔታዎችም ላይ ለኢንዱስትሪ ምርት የሚውሉ ጥሬ ሀብቶችን በማቅረብ ይሳተፋል።

(፪) አንዳንድ ድርጅቶችን በካፒታሊስቱና በመንግሥት የጋራ ባለቤትነት ሥር የማስገባት ፤ ካፒታሊስቶች ከትርፉ የተወሰነላቸውን ድርሻ እንዲወስዱ የማድረግ ፤
(፫) በካፒታሊስቱና በመንግሥት የኢንዱስትሪውን ሁሉንም ክፍሎች ወይም የንግድን ይዞት ባለቤትነት በጋራ መያዝ ፤ ካፒታሊስቱ የተወሰነ ድርሻ ከተስማሙበት (ብዙውን ጊዜ ፭ ፐርሰንት) ንጥር ገቢ እንዲወስድ በማድረግ፤ (፬) ሙሉ የመንግሥት ባለቤትነት—በመጀመሪያ ደረጃ ላይ ባለቤቶቹ የድርጅቶቻቸውን ሥራ ያካሂዳሉ ፤ በሁለተኛ ደረጃ የሥራ ማስኬዱን ከመንግሥቱ ወኪሎች ጋር ይከፋፈላሉ ፤ በሶስተኛ ደረጃ ምንም በማንኛውም ጊዜ አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ የቀድሞ ባለቤቶች ሥራ አስኪያጅ ወይም በሌላ ኃላፊነት ቦታ ቢመደቡም እንኳን መንግሥት ሥራውን ለማካሄድ ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳል ።



አንዴ ኃይል በሠራተኛው መደብ እጅ ስለገባ ትላልቅ ድርጅቶችን የመንግሥት አድርገዋል ። ሌኒን ይህንን የአዛዥነት ቦታ ይለዋል ። የዝቅተኛ ካፒታሊስት ድርጅቶች ተከታታይ መወረስ ያለ «ትብብ» ግጭት ቀስ በቀስ ይካሄዳል ። ግን የዚህ የቀስ በቀስ ውርስ ያለ ትብብ ግጭት መካሄድ ሊወሰን የሚችለው በፀረ-ሶሻሊስት ኃይሎች ስፋትና ጥልቀት ነው ። ምክንያቱም ትላልቅ ድርጅቶች የተወሰዱባቸው ባለቤቶች ከውጭ የኢምፔሪያሊስት ፍላጐት ጋር በመስማማት ለሠራተኛው ተፃራሪ ኃይል እንዲፈጠር ያደርጋሉና ።

የሶቪየት ሕብረት—የመጀመሪያዋ ሶሻሊስት አገር—የተጋተረችውና የተጋፈጠችው ወደድሮው ሥርዓት ለመመለስ በሚፈልጉ የውስጥ ጠላቶች ብቻ አልነበረም ፤ ግን በመጀመሪያዎቹ ዓመቶች በ፲፬ የካፒታሊስት አገሮች የጦር ኃይሎች የቀጥታ ወረራን ፤ በኢኮኖሚያዊ አሻጥርና መዘጋትን አስከትሎና በ፲፱፻፵፩ ዓ ም የናዚ ወረራንም ጭምር ነበር ።

ስለዚህ በሌሎችም አገሮች ሶሻሊዝምን ካቋቋሙ ጀምሮ ያ ኃይል በሰፊው እንደአስፈላጊነቱ ማጥቃቱ የማይቀር ግዴታ ነበር ። ግን በኋላ ወደ ሶሻሊዝም በሚሸጋገሩ አገሮች ሰላምና ሥቃዩ የተቃለለው ምክንያቱም የሶቪየት ሕዝቦች እጅግ ስለታገሉ ፤ ሁሉንም ጠላቶች ስለደመሰሱ ፤ በሠፊው ኢንዱስትሪያዊና የሕብረተሰብ እቅድ በማካሄዳቸውና በዓለም ላይ የመጀመሪያዋን ሶሻሊስት አገር ስለመሰረቱ ነው ። በስታሊን የመጨረሻ የሕይወት ዘመናት እንደታየው በአደገኛዋ ጠላት በሶቪዬት ሕብረት ላይ ብቻ ሳይሆን በታማኝ ረዳቶቻቸው ላይ እንኳን (ኢምፔሪያሊስቶች) ኃይል ተጠቅመዋል ። ከዚያም ከዛሩ አገዛዝ በመውጣት ከሕዝ

ምጥቀት ጐን ለጐን ቢሮክ
ቦች አጠቃላይ ዲሞክራሲያዊ ምጥቀት ጐን ለጐን ቢሮክ
ቦች አጠቃላይ ዲሞክራሲያዊ አብሮ አደገ ።
ራሲና የስታሊን የሥልጣን ማጠቃለል አብሮ አደገ ።

የሠራተኛው መደብ የገዥ መደብ መሆንንና «የዲሞ
ክራሲን ጦርነት ማሸነፍ» ማርክስ ሲናገር የሕዝቦችን
አጠቃላይ ዲሞክራሲያዊ ዕድገት (ከእንግዲህ በቀድሞው
የንብረት ባለቤት መደብ አስገዳጅነት የግዛት ቀንበር
ውስጥና የኑሮ ሁኔታ የማይገባው) አስመልክቶ ነበር ። ይህ
አጠቃላይ ዕድገት በሶቪየት ሕብረት በተግባር ውሏል ።
ኋላ ቀርታ በነበረችው ሩሲያ እንኳ (የዲሞክራሲያዊ መን
ግሥት ገጠመኝ በሌላት) መሠረታዊ አገዛዝ በዲሞክራ
ሲያዊ ተቋሞችና በተመረጡ ተወካይ አካሎች ተተክቷል ።
በዲሞክራሲያዊ መልክ ተቋቁመዋል ከሚባሉ ሌሎች አገ
ሮች እንኳ ሠፊው የሶቪየት ሕብረት ሕዝብ በአንዳንድ
ሁኔታዎች ይበልጥ የተሟላ ዲሞክራሲያዊ መብቶች አግ
ኝቷል ። ለምሣሌ ከሥራ ሁኔታ ጋር ባለው ግንኙነትና
በሕብረተሰብ አገልግሎቶች አስተዳደር በኩል ።

ግን ሶቪየት ሩሲያን እንደገጠማት የውስጥና የውጭ
ጠላት ትግል ምክንያት የዲሞክራሲ ሙሉ ዕድገት የማይ
ቻል ነው ። ሶቪየት ሕብረት በረጅም ጊዜ ባካባቢው ካፒታ
ሊዝምና በውስጥ ጠላት ችግሮች ምክንያት በከፍተኛ
ትሳትፎ ተከባ ምሽግ ሆና እንደነበረችበት ወቅት የፀጥታ
ድርጅቶች አስፈላጊ ነበሩ ። ጠንካራና ማዕከላዊ አመራርም
ይፈለግ ነበር ። እናም ስለዚህ የስታሊን ግላዊ ቁጥጥርና
የሶሻሊስትን መርሆዎች በብዛት መጣስ ፤ እንዲሁም
በመንግሥቱ የፀጥታ ድርጅቶች አማካይነት የብዙኃን
መጨቆን እያደገ ሄደ ። ይህ ምክንያት ሆኖና በነኝህ
ተንኰሎች አማካይነት ተመሳሳይ ከፍትህ ውጭ የሆነ



ድርጊቶች በምሥራቅ አውሮጳ ዲሞክራሲያዊ ሕዝቦች ላይ ተፈጸሙ ።

የስታሊን «ከኒ ወዲያ» ማንም የማለት (Cutt) ውጤቶች በሶቪዬት ኑሮ አካባቢ ከፍተኛ ጉዳት አስከትለዋል ። ነገር ግን እነኝህ ሁኔታዎች የሶሽሊስትን መንግሥትና የተደረገውን የሰፊው ሕዝብ ዕድገት ወደ ኋላ አላሉትም ፤ አለወጡትም ። ከስታሊን ሞት በኋላ የሶሻሊስት ዲሞክራሲን ለመመለስና ለማጠናከር በሁሉም የሶሻሊስት አገሮች የስታሊንን መርገሞች (Evils) ያሳለፉ ሁሉ እነኝህን ከፉ ድርጊቶች ለመሰረዝ ርምጃዎችን ወሰዱ ። የዲሞክራሲንና የፍትህ መጣስን የአስነሱት ሁኔታዎች ሁለተኛ አይደገሙም ፤ አሁን የሶሻሊስት አለም በጣም ጠንካራ ነው ፤ በተጨማሪም ያለፉት ትምህርቶች በየአገሩ ከፍተኛ ንቃት ፈጥረዋል ።

ሥልጣን በሕዝብ እጅ ከሆነ ፤ የአዲሱ ሕብረተሰብ መገንባት አስፈላጊነት የሚመሠረተው በምጣኔ ሀብታዊና በሕብረተሰብ ሂደት መሠረት ላይ ነው ። ትላልቅ ድርጅቶች ፤ ባንኮች ፤ የሐዲድ መስመሮችና ሌሎችም የኢንዱስትሪና የንግድ «የማዘገሮ ኃይሎች» ተነጥቀው ለከፍተኛ ዕድገት ለሚሆን ምጣኔ ሀብታዊ መሠረት መጣያ ያገለግላሉ ። አነስተኛ ምርትና ንግድ በግል ንብረትነት ይቆያሉ ፤ እናም ይነስም ይብዛ ከመንግሥት ኢንዱስትሪና ንግድ ጋር ከመዋሃዳቸው በፊት ረጅም ጊዜ ያልፉል ። ስለዚህ ሠራተኛው መደብ ወዲያውኑ ሊአገኘው የሚችለው ሶሺሊዝም አይደለም ፤ ግን የሃገሪቱ እድገት አቅጣጫ ወደ ሶሻሊዝም እንደሚሆን ያረጋግጣል ። ሁሉም ምርትና የምርት አከፋፈል የሶሻሊስታዊ መሠረት ከመያዙ በፊት ብዙ ዓመታት ይወስዳል ፤ ጠቅላላው ሕዝብ ሶሻሊዝምን የመ

ሳይሆን ግን እውነተኛ ሶሻሊስታዊ አመ
ቀበሉ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ግን መንገድን ማዳበር ከማሳየታቸው በፊት
ለካከት እና የኑሮ መንገድን ማዳበር ከማሳየታቸው በፊት
ለካከት እና የኑሮ እንደሚወስድባቸው ሁሉ ።
ረጅም ጊዜ እንደሚወስድባቸው ሁሉ ።

በአጠቃላይ የዋናዎቹ የምርት መገልገያዎች ከግል
ንብረትንነት ወደ ሕዝብ ንብረትንነት ሽግግር ብቻ ነው
መሠረቱን የሚያዘጋጀው ። ሁለተኛው ደረጃ እያደገ የሚ
ሄደውን የሕዝብ ፍላጐት ለማሟላት የሚያስችለው በን
ቃትና በእቅድ የሚካሄደው የምርት ኃይሎች ዕድገት ነው ።

ይህ ዕድገት አስፈላጊነቱ ወደኋላ በቀሩ ኢንዱስትሪ
ያዊ አገሮች (ለምሳሌ ሩሲያ በ፲፱፻፲፯ ዓ ም እንደነበረችበት
ደረጃ) ብቻ ነው ማለት ስህተት ይሆናል ። «ወዝ አደሩ
ሥልጣን ከያዘ በኋላ የፖለቲካ የበላይነቱን የሚጠቀምበት
. . . . . . በተቻለ መጠን በአፋጣኝ ጠቅላላ የምርት
ኃይሎችን ዕድገት ለመጨመር ነው።» የሚለውን በጻ
ፈበት ጊዜ ማርክስ ያስብ የነበረው መጠቅ ስለአሉት
የኢንንዱስትሪያውያን አገሮች ነው ። እና ሆኖም እነዚህ
አምራች ምንጮች ከማርክስ ጊዜ ጀምሮ በሰፊው ቢጨ
ምሩም ፤ እውነቱ ሳይንሳዊ ዕውቀት ባሁኑ ወቅት ሊአሟላ
ከሚችለው ጋር ሲነፃፀር አሁንም ወደኋላ ቀርተዋል ።
ወደኋላ ቀርተዋል እንላለን ምክንያቱም በካፒታሊስቱ
ሥርዓት ፤ ምክንያቱም ምርት ለገበያ ስለሆነ ፤ እና ገበያም
በካፒታሊዝም የሚገደብ ስለሚሆን የምርት ኃይሎችም
ዕድገት የተገደበ ነው ። እናም በምጣኔ-ሀብት ቀውሶች
የምርት ኃይሎች ሰብአዊና ቁሳዊ ነገሮችም ይቀንሳሉ
ወይም ሊወድሙ ይችላሉ ። ወደኋላ ቀርተዋል ምክንያ
ቱም ሞኖፖሊዎች ቴክኒካዊ ፈጠራዎችን (Technical
Inventions) ስለገዙዋቸውና በሠፊው ጥቅም ላይ እንዳይውሉ
ስለሚያግዷቸው ፤ ምክንያቱም ምርት በዕቅድ ስለማይ

መራና ሥርዓት የተከተለ ዕድገት ስለሌለው ፤ ምክንያቱም
ካፒታሊዝም እርሻን የተበታተነና ወደኋላ ቀር ስላደረገው ፤
ምክንያቱም ካፒታሊዝም በተወዳዳሪ ቡድኖች ለቅኝ
ግዛት ሕዝቦች ዐር ለሆነ ጦርነት ሠራ አስተዋጽኦ ለማድ
ረግ ስለሚፈልግ ፤ ምክንያቱም ካፒታሊዝም የአእምሮን
ሥራ ከጉልበት ሥራ ስለሚለያይና ስለዚህም የፈጠራን
(Invention) ሠራ በር ስለማይከፍት ፤ ምክንያቱም የመደቡ
ትግል ሠራ የሕዝብ ኃይል ስለሚመጥ ፤ ምክንያቱም ካፒ
ታሊዝም በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦችን በሀገራቸው

የሀብት ምንጭ ዕድገት ሙሉ ተሳትፎ እንዲጫወቱ የሚአ
ስችላቸውን በትምህርትና በሙያ የመሠልጠንን በር ስለ
ሚዘጋባቸው ነው ።

ስለዚህ ፋብሪካዎችና ማዕድኖች ፤ የኃይል ምንጮ
ችና የባቡር መስመሮች ፤ እርሻና አሣ ማስገር እንደገና ተደ
ራጅተው ዘመናዊ መሆን አለባቸው ፤ እናም በአጠቃላይ
ሕዝቡ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ምርት ላይ እንዲደርስ የከፍ
ተኛ የትምህርት ደረጃና በሙያ መሠልጠን ሊገጥመው
ይገባል እንላለን ። የዚህ ዓላማው ምንድን ነው ? የሕዝቡን
የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ።

በፀረ-ሶሻሊስቶች ብዙውን ጊዜ ከሚነሱት ውዝግ
ቦች አንዱ «ማንኛውም የሚመረተው ሁሉ እኩል ከተከ
ፋፈለ ፤ በሠራተኞች ውስጥ በጣም ትንሽ የሆነ የኑሮ
ልዩነት ነው የሚፈጠረው» የሚለው ነው ። ይህ እንኳ
ዕውነት ቢሆን ኖሮ እውነት አይደለም እንጂ - ከማርክስ
የሶሻሊዝም ፅንሰ - ሀሳብ ምንም ግንኙነት የለውም ።
ማርክስ ሶሻሊዝምን የአየው የምርትን የዕድገት ደረጃ
ከዚህ በፊት መታየት ቀርቶ ያልታለመ ደረጃ በላይ ከፍ

እንደሚአደርግ ነው ። ምክንያቱም እንዲሁ ብቻ የዛሩ
ሩሲያ ወደኋላ የቀረች በመሆኗ አይደለም በ፲፱፻፺፩ ዓ ም
በሶቪየት ሕብረት የኢንዱስትሪያዊ ምርት ሃያ አምስት
ጊዜ የ፲፱፻፲፫ቱን የሆነው ፤ በጣም በዳበሩ ኢንዱስትሪያዊ
አገሮች እንኳን ከፍተኛ የሆነ ጭማሪ ኖሯል ፤ ሊመጣም
ይችላል ። ስለዚህ ይህ የምርት እና የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ
ዕድገት የሕዝቡን የዕውቀትና የባሕላዊ ደረጃ ከፍ የሚአ
ደርግ ቁሳዊ መሠረት ነው ።

ግን ጠቅላላ ዕድገቱ ዕቅዳዊ አመራረትን ይጠይቃል ።

በካፒታሊስቱ ሕብረተሰብ ውስጥ ፤ በዕድገቱ ምክንያት
ከፍተኛ ትርፍ ከተገኘ አዲስ ፋብሪካዎች ይቋቋሙና የእያ
ንዳንዱም ዕቃ ምርት እንዲጨምር ይደረጋል ። ቢሆንም ፤
በምንም ዓይነት መንገድ ቢሆን ከፍተኛ ትርፍ ማለት
በጥያቄ ላይ ያለው ዕቃ በሕዝቡ የተፈለገ ነው ማለት አይ
ደለም ። ጥያቄው ጥቂት ከሆኑ በጣም ከበርቴ ሕዝቦች
ሊነሣ ይችላል ፤ ወይም ልዩ ሁኔታዎች የዕቃውን የዋጋ
ተመን ሊአንሩት ይችላሉ ። ትርፍ ዋናው አነሳሺ ኃይል
በሚሆንበት ጊዜ የምርት ሥርዓተ - አልባነት ብቻ ነው
የሚኖረው ፤ ስለሆነም ውጤቱ ባንድ በኩል የማያቋርጥ
ትርፍርፍ ምርት በሌላ በኩል ዝቅተኛ ምርት ነው ።

በሶሻሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ፤ ምርት ለትርፍ
ሳይሆን ለጠቀሜታ በሚሆንበት ምርትን ዕቅዳዊ ማድረግ
ይቻላል ። ኢንዱስትሪዎች በሙሉ ሕብረተሰባዊ ከመሆና
ቸው በፊት እንኳን ይህ ይሆናል ። ወዲያውኑ ዋና ድር
ጅቶች እንደተወረሱና ሌሎችም ይነስም ይብዛ ሥርዓት
እንዲኖራቸው ከተደረገ በኋላ የምርት ዕቅድ ሊሠራ ይች
ላል ፡- በየዓመቱ በጣም ትክለኛነቱ እያደገ የሚሄድ ዕቅድ ።



ስለዚህ ማርክስ ሶሻሊዝምን የምርት መገልገያዎች
ባለቤትነት የጠቅላላው ሕብረተሰብ በሚሆነው ምጣኔ
ሀብታዊ መስክ ፤ በምርት ኃይሎች ውስጥ ፈጣን ዕድገትና
ዕቅዳዊ ምርት ላይ የሚውል አድርጎ እንደተመለከተው
እናያለን ። በሶሻሊዝም ውስጥ ሁልጊዜም የምርት መገል
ገያዎች እያደጉ በሚሄዱበት ትርፍርፍ ምርት ሊኖር
የማይችልበት ምስጢሩ ይህ የምርት ፀባይ ዕቅድ ነው ።

የብሔራዊ የምርት ዕቅድ—ሁለት ክፍሎች ይኖሩታል፤
አዲስ የምርት መገልገያዎች ዕቅድ ሕንፃዎች ፤ መኪና
ዎች ፤ ጥሬ ዕቃዎች ፤ ወዘተ . . . . . . . እና
ለብሎት ወይም ለፍጆታ (Consumption) ዕቅድ ፤ ምግብና
ልብስ ብቻ ሳይሆን ግን ትምህርት የጤና አገልግሎት ፤
መዝናኛ ፤ ስፖርት እና ሌላም ፤ አስተዳደርንም ጨምሮ
ነው ። የመከላከያ ኃይሎች እንደሚአስፈልጉ ሁሉ እነኝ
ህም በፕላኑ በደምብ መያዝ ይኖርባቸዋል ።

ትርፍርፍ ምርት ሊኖር አይችልም ፤ ምክንያቱም
ለብሎት የሚወጡት ጠቅላላ ዕቃዎች ለሕዝቡ ስለሚከ
ፋፈሉ ማለትም ጠቅላላ ምንዳዕና ሁሉም ዓይነት አበሎች
የሚወሰኑት ከጠቅላላ የብሎት ዕቃዎች ተመን ጋር ተመ
ጣጥኖ ስለሚሆን ነው ።

እርግጥ መጥፎ ዕቅድ ሊኖር ይችላል—ከሕዝቡ ፍላ
ጎት ውጭ ብዙ ቢስክሌቶችና በጣም ጥቂት ቡቶች ለማስ
ገኘት የአንድ ዓመት ዝግጅት ይደረግ ይሆናል ። ግን እንደ
ዚህ ዓይነት ስህተቶች በሚቀጥለው ዕቅድ መስተካከሎች
ተደርጎላቸው በቀላሉ ቢፈወሱ ሚዛኑ ተቃና ማለት ነው ።
ሁልጊዜም ቢሆን በአንድ ነገርና በሌላው መካከል ያለውን
የምርት መስተካከል ማድረግ ብቻ ነው ዋናው ነገር ።

ጥቅላላ ምርትን በፍጹም አይቀንስም ፤ ጠቅላላ ብሎ
ይህ ጠቅላላ ምርትን በታች ወርዶ አያውቅምና።የእንኝ
ከጠቅላላ ምርት ዕቃዎች በታች ወርዶ ... (Distribution
ዕቅዳዊ ምርት ከፍ ሲል ዕቅዳዊ መከፋፈልም
እንደዚሁ ያድጋል ።

ግን በዓይነት ለሕዝቡ አይከፋፈሉም ። መጠቀሚ
ያው መንገድ (የማከፋፈሉ) በምንዳዕ ወይም በአበል ስ
የገንዘብ ለሕዝብ መሠራጨት ነው ። የብሎት ዕቃዎ
ተመን እንደተተመነ ፤ በጠቅላላ ለየሚከፈለው ምን ዕ
አበል ዕቅድም ባይሆን ከጠቅላላ ብሎት ዕቃዎች ተመ
ጋር የተመጣጠነ ይሆናል ። በብሎትና በምርት መካከ
በፍጹም ምንም ልዩነት አይኖርም ። ሰዎች የሚአስፈ
ጓቻውን ነገሮች ሁሉ መግዛት ይችላሉ ። የምርት መ
መር ማለት የሚአስፈልጉ ዕቃዎች መጠን መጨመ
በዚያውም ሕዝቡ የሚወስደው መጠን ማደግ ነው ።

በሶሻሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ስላለው የተመ
ሁኔታ ብዙውን ጊዜ የተሳሳተ አባባል አለ ። በከበርቴወ
ሥርዓት ውስጥ የተመን መዋለል የሚአመለክተው በማ
ረብና በመጠየቅ (Supply & Demand) መካከል ያለው
ግንኙነት ነው ። ተመኑ ከፍ ካለ ምርቱ በጣም እንሏል
ተመኑ ዝቅ ካለም ምርቱ በጣም በገዟል ። ስለዚ
ምርቱ መቀነስ አለበት ማለት ነው ። ስለዚህም ተመ
እንደምርት አርጊ (Regulator of Production) ሆኖ ይ
ራል ። ግን በሶሻሊስት ሕብረተሰብ ተመኖች በቀላ
የብሎት አርጊዎች ናቸው ፤ ምርት የሚሄደው ዕቅዱ
ተከትሎ ነው ። እናም ተመኖች ሆን ተብለው ይተመናሉ
ስለዚህም የሚመረተው ይፈጃል (ያልቃል) ።

ጠቅላላ የብሎት ዕቃዎች ምርቶች ለሕዝቡ እንዴ
ነው የሚከፋፈሉት ? ማርክስ ሁልጊዜም ቢሆን ምር



ዕኩል ይከፋፈላል ብሏል ብሎ ማሰብ ፍጹም የተሳሳተ ዕንስ ሀሳብ ነው ። ለምን አይሆንም ? ምክንያቱም የሶሻሊስት ሕብረተሰብ ፍጹም አዲስ ሆኖ አልተገነባም ፤ ግን ከመሠረቱ ከካፒታሊዝም የሚወርሰው አለው ። ዕኩል መከፋፈል ማለት የኑሮ ደረጃው ከአማካዩ በላይ (Abovs the Average) የነበረውን ሁሉ መቅጣትና እንዳይጠቀም ማድረግ ነው ። ልምድ ያላቸው ሠራተኞች ማለትም ሥራቸው እየጨመረ በሚሄደው ምርት ውስጥ ልምድ ከሌላቸው ሠራተኞች ሥራ ይበልጥ ለሕብረተሰቡ በጣም አስፈላጊ የሆኑትም እንዳይጠቀሙ ይደረጋሉ ። ስለዚህ ካፒታሊዝም በተወለደ ያልተስተካከለ ሁኔታ ላይ እያለን እኩልነት ብንል (በክፍያ) ትክክለኛ ፍርድ አይደለም ። ማርክስ በዚህ ነጥብ ላይ ግልጽ ነበር ፤ እንዲህ ሲል ጽፉል ፡ «መብቶች ፤ ዕኩል ከመሆን ይልቅ ዕኩል አለመሆን አለባቸው ፤ ፍትህ ከሕብረተሰብ ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎችና በነኝህም ከሚወሰኑት ባሕላዊ ዕድገቶች በላይ ሊታይ አይችልም ።»

በእውነት ከሆነ ፤ ከካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ የተገኙት ሰዎች ዕኩል አይደሉም ፤ ስለዚህም ሕብረተሰቡ ለእነሱ ትክክለኛ እንዲሆንላቸው ከተፈለገ ዕኩል ግልጋሎት መስጠት የለበትም ። በሌላ በኩል ፤ ሕብረተሰቡን ካገለገሉ ሕብረተሰቡም ብቻ ለእነሱ ይህ ግዴታ አለበት ። ስለሆነም «የማይሠራ አይበላም» ። ከዚህም በማስከተል ፤ ለሕብረተሰብ በጣም ጠቃሚ ሥራ የሚሠራ በትክክል ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ይሰጠዋል ። ስለዚህ ለብሎት የሚሆኑት ጠቅላላ ምርቶች አከፋፈል የሚመረኮዙበት መርሆ «ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ፤ ለእያንዳንዱ እንደሥራው» የሚለው ነው ።

ግን ሶሻሊስት ሕብረተሰብ ከካፒታሊዝም በወረሰው ደረጃ ብቻ አይቀርም ። በየዓመቱ ምርትን ያሳድጋል ፤ በዚያውም የሕዝቡን ቴክኒካዊ ልምድና ባሕላዊ ዕድገት ያሻሽላል ። እናም በምንዳዕ ዕኩል አለመሆን ልምድና ባሕላዊ ዕድገት ያላቸው ሰዎች ልምድ ከሌላቸው ይበልጥ ስለሚአገኙ እያንዳንድ ሰው ያለውን ወይም ያላትን ብቃት (Qualification) ለማሻሻል አነሳሽ (ገፋፊ) ኃይል ይሆናል ። ከፍተኛ ልምድ ማለት ከፍተኛ ምርት ነው ። ብዙ ዙሪያየሚያስኬድ ነገር አለ ፤ ይህም የእያንዳንዱን የኑሮ ደረጃ ከፍ እንዲል ያስችላል ። በሶሻሊስት ሕብረተሰብ እኩል አለመሆን ማለት በጠቅላላ የሕብረተሰቡ ደረጃ ከፍ የሚልበት መፈንቅል ነው (Lever) ። ግን እንደካፒታሊዝም የብዙዎችን ድህነት የጥቂቶችን ብልጽግና ጨማሪ መሣሪያ አይደለም ።

ይህን ዕኩል ያለመሆን ለወደፊቱ ሕብረተሰብ ቀዋሚ የሆነ ጠባይ አድርጎ ማርክስ ወስዶታል? አይደለም፤ ሕዝቡ ያመረተውን ለሕብረተሰቡ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር በሚመጣጠን መስመር የማከፋፈሉ ወሰን (Limit) አስፈላጊነት የሚከሰትበት ደረጃ አለ ።

ከዚህም በላይ ፤ ምርቱን እንደሠራው ሥራ መጠን ማከፋፈል ወይም ሌላ ዓይነት መርኅ ማለት የሁሉንም ፍላጎት ለማሟላት የሚአስችል ነገር እንደሌለ ማመን ነው ። በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ያለ አንድ ቤተሰብ የሚፈልገውን ያህል ምግብ ማቅረብ የሚችል ከሆነ ምንም ዓይነት የመከፋፈል መርሆ አይቀበልም ። እያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል የሚፈልገውን ያህል መውሰድ ይችላል ። በሶሻሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ምርት በከፍ



ተኛ ደረጃ ሲአድግ ማንኛውም ዜጋ ምንም ንጥረት ሳይደርስበት የሚፈልገውን ያህል መውሰድ ይችላል ፤ የሚወስደውን ነገር የሚለካ ወይም የሚወስን አይኖርም ። ደረጃው ሲመጣ የሚፈለገው ነገር ሁሉ ሲሟላ ፤ ምርትና የምርት አከፋፈል የሚመረኮዙት መርህ «ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደፍላጎቱ» ይሆናል ።

ይህ ነጥብ ነው ኮሚውኒዝምን ከሶሻሊዝም የሚለየው ። «ሶሻሊዝም» ማርክስ ቃሉን እንደተጠቀመበት ፤ አንደኛው ደረጃ ነው ። የምርት መገልገያዎች በሕዝብ ቁጥጥር ሲሆኑ ምንም ዓይነት የሰው በሰው ብዝበዛ አይኖርም ፤ ግን ዕቅዳዊ የሶሻሊስት ምርት የሃገሪቱን የምርት ውጤት በከፍተኛ ደረጃ ከማንሳቱ በፊት ሁሉም ሰው የሚፈለገውን ሊአገኝ ይችላል ።

የኮሚውኒዝም ደረጃ ከቁሣዊ መብቃትም (Material Sufficiency) ይበልጥ ብዙ ይሄዳል ። የሠራተኛው መደብ ሥልጣን ከያዘበትና ወደሶሻሊዝም መለወጥ ከጀመረበት ጀምሮ በሰዎች አመለካከት ላይም ለውጥ ተጀምሯል ። ሁሉም ዓይነት ገደቦች በካፒታሊዝም ጊዜ ጠንካራ መስለው የታዩት ሁሉ ደካማ እየሆኑ ሄዱና በመጨረሻ ስብራቸው ወጥቷል ። ትምህርትና የዕድገት ዕድሎች የወላጆቻቸው የገንዘብ ሁኔታ ወይም ገቢ ምንም ዓይነት ቢሆን ለልጆች እኩል ክፍት የመሆናቸው በየጊዜው እየጨመሩ ይሄዳሉ ። የሕብረተሰቡ የደረጃ ክፍፍሎች ወዲያውኑ ዋናነታቸውን ያጣሉ (የመኳንንት ፤ የባላባት ፤ ወዘተ ልጅ የመባባሉ) ። ልጆች አንጎላቸውንና እጃቸውን እንዲጠቀሙባቸው ይማራሉ ። ይህ የአካላዊና የአእምሮአዊ ዕኩልነት ሥራ ቀስ በቀስ ወደ ሠፊው ሕዝብ ይሠራጫል ፤

ሁሉም «ምሁር» ይሆናል ፤ ግን ምሁራን ደግሞ ከእንግ
ዲህ ራሳቸውን ከአካላዊ (ከጉልበት) ሥራ አይለዩም ።

ሴቶች ከእንግዲህ የበታች ወይም በሕብረተሰቡ ኑሮ
ውስጥ በማንኛውም የሥራ አድማስ ሚናቸውን ለማካ
ፈል የማይበቁ ናቸው ተብሎ የሚወሰድ ነገር የለም ።

ሥራው ቀላል እንዲሆንላቸው ልዩ እርምጃዎች ይወሰዳሉ ።
የሕፃናት መዋያዎች በፋብሪካዎች ውስጥ እና በየቦታው
ይቋቋማሉ ፤ ስለዚህም እናቶች የበለጠ ነፃነት ሊኖራቸው
ይችላል ። በቤት ውስጥ ያለው የሴቶች ሥራ በሕዝብ
ወጥቤቶች ፤ ልብስ ማጠቢያዎች (Lanundries) እና በምግብ
ቤቶች አማካይነት ይቃለላሉ ። ሠራተኛ ሴቶች ሥራቸውን
የሚያቃልሉላቸው ማሙያ ዕቃዎች ይሰጧቸዋል ።

በብሔሮች መካከል ያሉ ድንበሮች (መሰናክሎች)
ይሰባበራሉ ። በሶሻሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ የጎሣ የበላ
ይነት የለም ፤ በቀለሙ ወይም በዜግነቱ የተነሣ ማንም
የበላይነት ወይም የበታችነት ግልጋሎት አይሰጠውም ።
የሁሉም ብሔር ሰዎች ምጣኔ ሀብታዊ ምንጮቻቸውን
እንዲሁም ትምህርትና ልማዳዊ ጽሑፎቻቸውንና ኪነጥ
በቦቻቸውን እንዲአዳብሩ ርዳታ ይሰጣቸዋል ።

ዲሞክራሲ የፓርላማ ተወካይን በየአምስት ዓመቱ
ለመምረጥ የተገደበ አይደለም ። በእያንዳንዱ ፋብሪካ
ውስጥ ፤ በማንኛውም ቦታ ፤ በማንኛውም የኑሮ መልክ ፤
ሴቶችና ወንዶች ኑሮአቸውንና የአገራቸውን መዳረሻ
ይቀርፃሉ ። በአንዳንድ የሕዝባዊ አገልግሎት ክበብ
ውስጥ ራሳቸውንና ሌሎችንም የመርዳት ዕድል እንዲአ
ገኙ ከቀን ቀን የሰዎች ቁጥር ይጨምራል ፤ ይህ በካፒታ



ሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ካለው ዲሞክራሲያ ይበልጥ
በጣም የተሟላና ይበልጥ እውነተኛ ነው ። በካፒታሊስቱ
ግን ሀብትና የግል ጥቅም በዲሞክራሲአዊ ተቋሞች ላይ
ተፅዕኖ ያደርግባቸዋል ።

በከተማና በገጠር መካከል ያለው ልዩነት ንኩት
ኩቱ ይወጣል ። በየመንደሩ ያሉ ሠራተኞች በመኪኖች
መሥራትና መጠቀምን በመማር ከተማውስጥ ካሉት
ሠራተኞች ደረጃ ጋር ቴክኒካዊ ልምዳቸውን ዕኩል ከፍ
ያደርጋሉ ። ትምህርታዊና ባሕላዊ ማሟያዎች ቀድሞ
በከተሞች ብቻ የሚገኙት አሁን በገጠሩም ይስፋፋሉ ፤
ያድጋሉ ።

በአጭሩ ሶሻሊዝም ባመጣቸው የቁሳዊ ሁኔታዎች
ለውጦች ምክንያት በወንዶችና በሴቶች አመለካከትና
ዕድገት ላይም ሠፊ ለውጥ ይታያል ። ሰዎች ባለ ዙሪያ
ገባ ዕድገት ፤ ዙሪያ ገብ ሙያተኛ ፤ ሁሉንም ነገር ሊሠሩ
የሚችሉ ይሆናሉ ።

በአጠቃላይ በካፒታሊዝም ውስጥ ስለራሱ ብቻ
ፈላጊ የሆነው የግለሰብ አመለካከት ቀስ በቀስ ኢውነ
ተኛ ሕብረተሰባዊ አመለካከት ፤ ኖሮት ስለሕብረተሰቡ
ኃላፊነት እንዳለበት አድርጎ ራሱን የሚቆጥር ይሆናል ፤
ማርክስ እንዳስቀመጠው ሥራ የመኖር ዘዴ ብቻ አይ
ደለም ፤ ግን ለሕይወት የመጀመሪያው አስፈላጊም ነገር
ነው ። በኮሚኒስት ሕብረተሰብ ለመሥራት ምንም ዓይ
ነት የመገፋፊያዎች አስፈላጊነት የለም ። ምክንያቱም
በዚህ ጊዜ ያሉት ወንዶችና ሴቶች ሕብረተሰብን ይበ
ልጥ ለማሳደግ ከሚጫወቱት ሚና በቀር ሌላ አመለካ
ከት የላቸውም ።

ይህ ተምኔታዊ ነውን ? በምዕራፍ ፪ ያነሣነው የማርክሲዝም ቁስ አካላዊ መሠረት ምን እንደሆነ ያልተረዳ ሰው ተምኔታዊ ነው ብሎ ሊወስደው ይችላል ። የሰው ልጆች ለዘላለም ነዋሪ የሆኑ ቀዋሚ ጸባዮችና አመለካከት የላቸውም ። በጥንታዊ ጋርዮሽ ሕብረተሰብ ውስጥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይኖር ከነበረው እንኳ እንደምንረዳው ለነገዱ ይሰማው የነበረው ኃላፊነት በጣም ከፍተኛ ነበር ። በኋላ ሕብረተሰቡ በመደብ ሲከፋፈል ስለሕብረተሰብ የኃላፊነት ስሜት ስብርብሩ ወጣ ፤ ግን አሁንም ቢሆን መደቡን በሚመለከት ረገድ የሃላፊነት ስሜት አለ ። በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ በጣም ፅንፋዊ ( Extreme ) የሆነ መለያየት ያለው የሕብረተሰብ ሃላፊነት አለ ፡— ሥርዓቱ « እያንዳንዱ ሰው ለራሱ » የሚል የሕይወት ዋና መርሆ እንዲኖረው ያደርጋል ።

በካፒታሊስት ሥርዓት እንኳ « አንድነት » በሠራተኞች መካከል አለ ። ማለትም የጋራ ፍላጎት ስሜት ፤ የጋራ ኃላፊነት ። ይህ አንድ ሰው አስቦት በሠራተኞች ራስ ውስጥ እንዲቀመጥ የተደረገ አይደለም ፤ ከሠራተኛው መደብ ቁሳዊ ሁኔታ የሚመነጭ ነው ፤ እውነቱ—ኑሮአቸውን በአንድ ዓይነት መንገድ እርስ በእርሳቸው ጎን ለጎን በሚሠሩበት ጊዜ የአገኙት ነው ። ዋናው አጋባሺ ግለሰብ በሌላ በኩል ጋርዮሻዊ ወይም የሕብረተሰብ ኃላፊነት የማይሰማው እርስ በእርሳቸው በመገዳደል የመኖር ትግል በሚአካሂዱ ተወዳዳሪዎች የተከበበው ካፒታሊስት ነው ። እርግጥ የገዥው መደብ አሳቦች (ከአንድነት ይልቅ ውድድርና ጠላትነት) በሠራተኞች መካከል ይሠራጫሉ ፤ በተለይም ለማናቸውም ለልዩ ዕድገት ሲባል በቀጣሪዎች እየተንጠለጠሉ በሚባረሩት ሠራተኞች



ውስጥ ። ግን ለማንኛውም መደብ ለአመለካከቱ ዋና መሠረት (በግለሰቦች ልዩ በመሆን) ኑሮውን የሚአገኝበት የሕይወቱ ቁሳዊ ሁኔታ ነው ።

ስለዚህ ከተል አድርገን ብንመለከተው የሰዎች አመለካከት ሊሰጥ የሚችለው ኑሮአቸውን ሊአገኙ የሚችሉበትን ቁሳዊ ሁኔታ በመለወጥ ነው ። በሶቪየት ሕብረት ገባሮች አመለካከት ላይ ከተፈጠረው ሁኔታ ይበልጥ ሌላ ምሣሌ ሊወሰድ አይቻልም ። ማንኛውም በዛሩ ሩሲያ ውስጥ ስላሉት ገበሬዎች የጻፈ ሁሉ « ራስን መውደድና የግለሰብ አጋባሺነት ጠባይ » እንዳለ ይገልጻል ። ስለአብዮቱ የተወሰዱ ግምገማዎች ገበሬው በፍጹም ወደ ሶሻሊዝም ሊለወጥ እንደማይችልና አብዮቱ በገበሬዎች እንደሚቋረጥ ይናገሩ ነበር ። እናም በትክክል የገበሬው አመለካከት ውሱን እንደ ነበር ፤ ከአሮጌው የአኗኗር ሁኔታም የማይነቃነቅ እንደሆነ ፤ ወደ ሶሻሊዝም በውዝግብ ወይም ደግሞ በኃይልና በማስገደድ ሊገባ ይችል እንዳልነበር በትክክል እውነት ነው ። እነዚህ ግምገማዎች ያላጤኑት ነገር ቢኖር ማርክሳዊ አልነበሩምና ፤ ሠርቶ ማሳያ እርሻዎችን ፤ ባቅራቢያቸው የትራክተር ጣቢያዎችን ማለትም የተሻሉ ሰብሎች ሠፋ ባለ ዘዴ የሚገኙበትንና የሚታዩበትን ተግባር ነው ። እነኛ ሁኔታዎች የተሸነፉትን በመኪናዎችና የግለሰብነትን ወሰን (Individual land Marks) ሰብሮ መሬትን በጋርዮሽ በመጠቀም ብቻ ሊገኙ በሚችሉ ዘዴዎች ነው ። እናም ይህ በተራው የአመለካከታቸውን መከፋፈል (?ልዩነት) በጣጠሰው ። በጋርዮሻዊ የኑሮ መሠረት ሰፈሩና ልዩ ዓይነት ገበሬዎች ሆኑ ። ጋርዮሻዊ ገበሬነት ( Collective Peasantry ) ከጋርዮሻዊ የኃላፊነት ስሜት ጋር ጥቂት ከሶሻላዊ አመለካከት መንገድ ቀረት ያለ ማለት ነው ።

ስለዚህ በማንኛውም አገር ቁሳዊ መሠረቱ ሶሻሊስ ታዊ አመራረትና አከፋፈል ከሆነ ፣ ሁሉም ሰው ኑሮውን የሚያካሂድበት መንገድ በአጠቃላይ ለሕብረተሰቡ በመ ሥራት ከሆነ ፡ እንግዲያስ የሕብረተሰብ ኃላፊነት ስሜት (Sense of Social Responsibility) እንደእውነቱ ከሆነ ተፈጥ ሮአዊ ዕድገት ይኖረዋል ። ከእንግዲህ ሕዝቡ የሕብረተሰቡ መርሖ ትክክል ነው በሚል ፍላጐት ውስጥ አይደለም ፣ ከ ሰው ተፈጥሮ በላይ ራሱን ለማቆም የሚችል ሥውር ሞራላዊ ተግባር የሆነ የመገፋፊያ ፍላጐት ጥያቄ አይደለም ። የሰው ተፈጥሮ ራሱ የሚሸጋገረው በተግባራዊ ሂደት ነው ፣ ልማዳዊ ! ።

እስከዚህ ነጥብ ድረስ በጠቅላላው ዓለምን ስለሚሸ ፍኑት የሶሻሊስት ወይም የኮሚውኒስት እንድምታዎች ( Implications ) አልመረመርንም ። ግን የሶሻሊስት ሕብረተሰብ ዓለማዊ ሥርዓት ማለት የጦርነቶች ማክ ተም ነው ። በእያንዳንዱ ሀገር ውስጥ አመራረትና አከፋፈል በሶሻሊስት መሠረት ላይ ከተደራጁ ፣ በማንኛ ውም ሀገር ውርስጥ ሌላውን ሀገር የመውጋት (የማሸ ነፍ) ፍላጐት የሚኖረው ምንም ዓይነት ቡድን አይኖ ርም ። አንድ የከበርቴ ሃገር የሚወጋው ከእርሱ አንጻር ወደኋላ የቀሩትን ሀገሮች ነው ። ለምን ቢሉ ? ግዛትን ለማ ስፋፋት ፣ ለፋይናንስ ካፒታል መዋዕለ ንዋይ (Investment) ትርፍ የሚአስገኝ አዲስ ዕድል ለመክፈት ፣ አዲስ የባቡ ርና የባሕር ወደቦች ለማግኘት ፣ አዲስ ርካሽ የጥሬ ሀብት ምንጭና ገበያ ለመያዝ ሲባል ነው ። ሶሻሊስት ሕብረተሰ ቦች ጦርነት አያደርጉም ፣ ምክንያቱም እነርሱ ወይም በእነርሱ ውስጥ ያለ ማንኛውም ቡድን ከጦርነት የሚአተ ርፋት ምንም ነገር የለምና ።



በዚሁ ምክንያት ወደኋላ የቀሩትን አገሮች ለመያዝ ...ቶች እንኳን ፍላጐት ያለው የሶሻሊስት መንግሥት ...ለም ። እንዲአውም ፣ በብዛት እያንዳንዱ ሀገር ኢንዱ ...ሪውንና ባሕላዊ ደረጃውን ባሳደገ ቁጥር ለሌሎች ...ሻሊስት አገሮች የተሻለ ይሆንላቸዋል ። በመላው ዓለም የኑሮ ደረጃ ከፍ ይላል የዚያኑም ያህል የኑሮ (ሕይወት) ...ዘት ይበለጽጋል ። ስለሆነም በኢንዱስትሪ የገፉት የሶ ...ሊስት አገሮች በጣም ወደኋላ የቀሩትን እንዲአድጉ ...ረዳሉ ። ይህ መረን በኢንዱስትሪ ላልገፉት አገሮች ሶሺ ...ት ሕብረት ርዳታ እየሰጠች በተግባር እየዋለ ፣ እየዋ ...ም ነው ።

በዚህ ዓይነት አባባል የሶሻሊስት ሥርዓት ምጥቀ ታዊ ዕድገት ሰው ሊሰራው የሚችል ስለሆነ ምናቡን (ግም ቱን (Imaginatinn) ሊቋቋም ይችላል ። ከዚህ በላይ ሊሄድ አይችልም የማለትን ገደብ ይጥላል ። በማንኛውም አገር በሚታቀደው ምጣኔ ሀብታዊ ኑሮ ሁሉና ከእያንዳን ዳንዱ አገር የተለያዩ ዕቅድ ጋር ሊሰምርና ሊጣማ በሚችል የዓለም ዕቅድ በእያንዳንዱ አገር መካከል ባንዴ በሚከፋ ፈሉ ሳይንሳዊ አሰሳዎችና ቴክኒካዊ ፈጠራዎችን(Scientific Disco eries and Technical Inventions) በመጨመር ማንኛውም ዓይነት ባሕላዊ የመለዋወጥ ጭብጥን በማ ከል በእርግጥ ሰው ሠፊና የማያቋርጥ ጉዞ ወደፊት ሊጓዝ የሚችል መሆኑ አሌ የማንለው ሀቅ ነው ።

ወደ ምን ? ማርክስ ትንቢት ሊናገር አልፈለገም ፣ ምክ ንያቱም ለማንኛውም ሳይንሳዊ ትንቢት (Scintific Forecast) ሁኔታዎች በፍጹም የአልታወቁ ስለነበር ። ግን ይህ ግልጽ ነበር ፡— መላው ዓለም ኮሚውኒዝም ሲቋቋም ረጅም የታሪክ ምዕራፍ ያለው የሰው ልጅ በመደብ መከፋፈልና

የመደቦች ትግል ያከትማል ። አዲስ በመደቦች መከፋፈል
አይኖርም ፣ ምክንያቱም በኮሚውኒስት ሕብረተሰብ ለዚህ
መንስኤ የሚሆን የለምና ። በመደቦች መከፋፈል የሰዎች
ምርት ዝቅተኛ በነበረበት ጊዜ አደራጅዎችንና ከፍተኛ
የምርት ኃይሎች ሠረዎችን ነው የአገለገለው ፣ የመ
ደብ መከፋፈል ይህንኑ አሠራር ለማሟላት ቀጠለና በካ
ፒታሊዝም ውስጥ ደግሞ የምርትን መድለብና በሰፊው
የቴክኒክ መሻሻሎችን ረድቷል ።

ግን ፣ ሰው ራሱ በቀን ጥቂት ሰዓቶች ብቻ በመ
ሥራት ምርትን ማሟላት የሚአስችሉ የምርት ኃይሎች
በአሟላበት ደረጃ የመደቦች መከፋፈል ያልቃል ፣ ማለ
ቅም አለበት ። ከዚያ ነጥብ ጀምሮ ሰው ትግሉን ከተፈጥሮ
ጋር እንደገና ይጀምራል ፣ ግን ልዩነቶችን ሁሉ ያራግፋል
ይወረውራል (እንዲአውም አይኖሩ) ። ከእንግዲህ ተፈ
ጥሮን በማይጨበጥ ምኞት ( Magic ) ለማሸነፍ መፍ
ነብ (መሯሯጥ) የለም ወይም የተፈጥሮ አደጋን በጸሎትና
በሚጸ ለይለት መመለስ ። ከእንግዲህ በእውር ጭፍን ተም
ልቶ በመደናበር የራስን ኑሮ በመደብ ትግሎችና ጦርነቶች
መምራት ፣ አይቻልም ። ግን ስለራሱ እርግጠኛ የሆነ የተ
ፈጥሮን ኃይል በራሱ ኃይል ለመቆጣጠር ሙሉ እምነት
ያለውና ወደፊት የሚገሠግሥ ሰው ነው የሚኖር ፣—በማ
ርክስ ሥዕላዊ ገጽ እንደታየው ይህ ነው የኮሚውኒስቱ
ሕብረተሰብ ሰው ።



ምዕራፍ ፯

# ስለተፈጥሮ የማርክሳዊ አመለካከት

ማርክሲዝም ሰዎችንና ሰብአዊ ሕብረተሰብን ከተፈ
ጥሮ ክፍል እንደ አንዱ አድርጎ እንደሚወስዳቸው ከዚህ
በፊት ተወስቶ ነበር ። ስለዚህም የሰው አመጣጥ የሚገኘው
በዓለም የዕድገት ሂደት ውስጥ ነው ። ሰው የተገኘው ቀድሞ
የሕይወት ምንጮች ከሆኑት ነው ። የአዝጋሚ ለውጥ ሂ
ደት አስተሳሰብና ንቃታዊ ክንዋኔ በመልክ እንዲታዩ
ከአደረጋቸው ነገሮች መሆኑ ነው ። ይህ ማለት ቁስአካል
—ንቃት የሌለው ዕውነታ ማለት ነው— ከህሳብ በፊት
ነበር ፣ ንቃት ባለው ዕውነታ ተከተለ ። ህሳብ በሚባለው ።
ግን ይህም ማለት ቁስ አካል ፣ ውጭአዊ እውነታ—ከህሳብ
ውጭ ነጻ ሆኖ ይኖራል ነው ። ይህ ዓይነት የተፈጥሮ አመ
ለካከት ቁስአላዊነት ተብሎ ይታወቃል ።

ተቃራኒ የሆነው አመለካከት ፡— ደግሞ ውጫዊው
ዓለም ዕውነታ አይደለም ፣ በሃሳብ ውስጥ ብቻ ነው የሚ
ኖረው ወይም ከሁሉ በላይ በሆነ የመለኮት ህሳብ ውስጥ
ይኖራል የሚለው ሐሊናዊነት ይሰኛል ። ሐሊናዊነት የተ
ለያዩ መልኮች አሉት ። ግን ሁሉም የተመሠረቱት ሰብ
አዊም ይሁን መለኮታዊ ፣ ህሳብ ቀዳሚ ዕውነት ነው ፣
ቁስአካል ግን ያውም ዕውነታነቱ ቢታመንበት ሁለተኛ
ነው ይላል ።

ለማርክሲስቶች ፣ ኤንግልስ እንዳስቀመጠው ፡« የዓ
ለም ቁስአካላዊ አመለካከት ያለምንም ጥራጣሬ ተፈጥ
ሮን እንዳለ ፣ በሙሉ መገንዘብ ነው ። » ይላል ። ውጫ

ዊው ዓለም ዕውነት ነው ፤ ስለእሱ እኛ ንቃት ይኑረንም አይኖረን ነጻ ሆኖ ይኖራል ፤ እናም ቅስቃሴውና ዕድገቱም በማንም ሃሳብ በማይመራ ግን ሰዎች ሊጠቀሙበትና ሊአ ገኙት በሚችሉት ሕግ የሚገዛ ነው ።

ሕሊናዊነት በሌላ በኩል ፤ ምክንያቱም ቁስአካልን —ውጫዊ ዕውነታን — ለዚያውም እንኳን ዕውነታነቱን ከተቀበለ ነው — ሁለተኛ ዕውነታ አድርጐ ብቻ ነው የሚ ወስደው ። ይህም ብቻ ሳይሆን ዕውነታን በፍጹም ልና ውቅ እንደማንችል ፤ የዓለም ምስጢራዊ ዘዴን በፍጹም እንደማንረዳው ያስገነዝባል ።

ለምንድነው የቁስአካላዊነት ሕሊናዊነትን በመጻ ረር ያለው ክርክር ዋናነቱ ? ምክንያቱም የሥውር (ምስ ጢር) ሀሳብና የግምት ንድፈ — ሀሳብ ጥያቄ አይደለምና ነው ። በአጠቃላይ ትንተና የተግባራዊ ክንዋኔ ጥያቄ በመ ሆኑ ነው ። ሰው ውጫዊውን ዓለም በማየትና በመመራ መር ብቻ የሚረካ ሳይሆን ይለውጠዋልም ፤ እራሱንም ከዚያው ጋር እንዲሁ ።

ሁለተኛ ፤ የቁስ አካላዊ አቋም የሚለው ራሱ ሀሳብ የነቃበት ውጭ አዊ እውነታ ነው ፤ ሀሳቦች ሥውር የሆኑ ከዕውነታ የተገኙ ናቸው ፤ ምንጫቸው ውጭአዊ እውነታ ነው ። በእርግጥም ሁሉም ሀሳቦች እውነት የሆኑ የእውነታ ትክክለኛ ነጸብራቅ ናቸው ማለት ሳይሆን ፤ ነጥቡ « የእው ነታ የዕለት ከእለት ገጠመኝ » ትክክል ወይም ስህተት መሆናቸውን መሞከሪያ እንደሆኑ ማወቁ ላይ ነው ።

ሀሳባዊው በሌላ መንገድ ፡— ለዘላለም በሚኖሩ መር ሆዎች ሲአምን ዕውነታ ጋር ሊስማሙ መቻላቸውን ግን



ማረጋገጥ አይሻም ። በቅርብ ጊዜ ከሆኑት የዚህ ዓይነት ድርጊቶች ምሣሌ አንድ ነጥብየጦርነት ፍጹም አለመኖር (Absolute Pacifism) መርሆ ምን ጊዜም ፍጹም ጸጥ ባይ ነት ነው ። የማንኛውንም ዓይነት ጦርነት አውጋዥ ጠቅ ላላ ሎጅካዊ አመለካከት በአካባቢው ያለውን ዕውነተኛ ዓለምን ይዘነጋል ። ሀሳባዊው በአሁኑ ወቅት ባለው የዕ ለት ከዕለት ገጠመኝ አንድ ኃይል በመመኘት ወይም በተአምር ሊወገድ እንደማይችል ማወቁ አስፈላጊነት እንደሌለው አድርጐ ይወስደዋል። ከብዙ ገጠመኞች እንደ ምናየው ኃይልን አለመቋቋም ተጨማሪ ኃይል ፤ ወረራንና ጭካኔን እንደሚአመጣ ተረድተናል ። ምንጊዜም የፍጹም ጸጥ — ባይነት ዋና መሠረቱ የዓለም ሕሊናዊ አመለካከቱ በውጭአዊው ዓለም ያለማመኑ እና ከዚህም ይበልጥ ስለ ራሱ ፍልስፍናዊ አመለካከት እንኳ ንቃት አለመኖሩ ነው ።

ስለዚህ ማርክሲዝም ንድፈ — ሀሳቡን በሙሉ የሚ መሠርተው በዓለም ቁስአካላዊ ግንዛቤ ሆኖ ፡ ከዚህ አቋም ላይ በመሆን ዓለምን ይመራመራል ፡ ዓለምን የሚገዛውን ሕግ ለማግኘት ይሞክራል — ሰውም የዕውነታ ክፍል ነውና የሰብዓዊ ሕብረተሰብን ዕድገት የሚገዛውን ሕግ ያጠናል ፡ ይመራመራል ። አሰሳዎቹን ( Discaveries ) ሁሉንም መደምደሚያዎቹን ፡ ንድፈ ሀሳቦችንና መዝገ ያዎችን በመቃወም ወይም በማሻሻል — ቀለል ያለውን ሐረግ ለመጠቀም ፡ ከዕውነቶች የማይገጥሙትን ለማግ ኘት ፤ የዕለት ከዕለት ገጠመኞችን በመያዝ ይፈትናቸዋል ይሞክራቸዋል ።

ዓለምን በዚህ ዓይነት መቅረብ (ሁልጊዜም ሰብዓዊ ሕብረተሰብን በመጨመር) ዕውነት የሆኑትን ጠቅላላ ጠባ

ዮች ፣ በሀሳብ የተፈጠሩትን ሳይሆን ከነባራዊው የተንጸባ
ረቁትን ግልጽ ያደርጋል ። ማርክሳዊ ትኩረት ከዕውነት
የተወሰደ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ሳይንሳዊ ነው ። በአ
ንድ ጉበዝ አሳቢ የተሠራ ሥርዓት አይደለም ። ማርክሲ
ዝም ዓለምን የሚአየው እንደ ቁስ አካላዊ አድርጎ በመ
ሆኑ ፣ እውነት የሆኑ ጸባዮችን « ዲያሌክቲካዊ » (ሃቲታዊ)
በሚል ቃል ተሸፍነው ያገኛቸዋል ። « ዲያሌክቲካዊ ቁስ
አካልነት » የሚለው ሐረግ — የዓለምን ማርክሳዊ ጽንሰ
ሀሳብ የሚአብራራው — በአጠቃላይ ምስጢራዊ ሆኖ
ተወስዷል ። ግን በእውነት ምስጢራዊ አይደለም ፣ ምክ
ንያቱም በእውነት ያለው ዓለም ነጸብራቅ ነውና ፣ እናም
« ዲያሌክቲካዊ » የሚለውን ቃል የተለመዱ ነገሮችን
በማብራራት ማንም እንዲ ገነዘበውና እንዲአስታውሰው
ማድረግ ይቻላል ።

በመጀመሪያ ደረጃ ፣ ተፈጥሮ ወይም ዓለም ፣ ሰብ
ዓዊ ሕብረተሰብንም በመጨመር በጠቅላላው ልዩና ነጻ
ከሆኑ ነገሮች የተሠሩ አይደሉም ። ማንኛውም የሳይ
ንስ ሊቅ ይህን ስለሚአውቅ የሚአጠናውን ልዩ ነገር ብል
ሽት ወይም ልማት ሊአደርስበት የሚችለውን ዋና ጸባይ
ለማወቅ ከፍተኛ ችግር ይደርስበታል ። ውኃ ውኃ ነው ፣
ግን ሙቀቱ እስከተወሰነ ደረጃ ከጨመረ እንፋሎት ይሆ
ናል ፣ ሙቀቱ ከአዘቀዘቀ በረዶ ይፈጠራል ፣ የተለያዩ
ዓይነት ጸባዮች ሁኔታውን ያቃውሱታል ። ማንኛውም
ሰው ይህን ይረዳል ፣ ነገሮችን ሁሉ ከመረመረ እውነት
ለመናገር ምንም ነገር ሙሉ በሙሉ ነጻ የሆነ ነገር አይ
ገኝም ፣ ማንኛውም ነገር ከሌላው ጋር የእርስ በእርስ ጥገ
ኝነት አለው ።

እርግጥ ፣ ይህ የነገሮች የእርስ በርስ ጥገኝነት ግልፅ
የሆነ ቢመስልም ምንም የሚአመጣው ለውጥ ያለ አይ



መስለን ይሆናል ። ግን በእውነት ከሆነ ሰዎች ሁልጊዜም
የነገሮችን የእርስ በእርስ ጥገኝነት አያስታውሱም ። በአ
ንድ በኩል እውነት ያልሆነው ነገር በሌላ ሁኔታ እውነት
የሚሆን መሆኑን አይገነዘቡም ፣ በአንድ ዓይነት መንገድ
ብቻ የታሰቡ ሃሳቦችን በማከታተል በተለያዩ ሁኔታዎች
ሁሉ ያውላሉ ። ለዚህ ጥሩ ምሣሌ የሚሆነው « የተዋጊ
ጀልባ « ( Gun — Boat ) ዲፕሎማሲ ነው ። በኢምፔ
ሪያሊዝም የመጀመሪያ ዘመን ጊዜ የአንድ የአካባቢ የጎሣ
አለቃ ለማስፈራራትና ቃል ለማስገባት አንድ ተዋጊ —
ጀልባ መላክ ብቻ በቂ ነበር ። ግን አሁን የቅኝ ግዛት አገ
ሮች መቋቋም ጀመሩና የተዋጊ ጀልባ ዲፕሎማሲ ዜሮ
ገብቶ የኢምፔሪያሊስቶች ጠንካራ ያልሆኑ መርከቦች
መበሳጨት እየጨመረ ሄደ ።

ዲያሌክቲክስ በዓለም ላይ ያለ ነገር ሁሉ በዕርጋታ
ላይ ሳይሆን በእንቅስቃሴ በለውጥ ላይ እንዳለ ነው የሚ
መለከተው ። እየናረና እየዳበረ ወይም እያሽቆለቆለና የአ
ሞተ ማለት ነው ። ሁሉም ሳይንሳዊ ዕውቀት ይህን የአ
ረጋግጣል ። ስለዚህም ለማንኛውም ዕውነተኛ ሳይንሳዊ
ምርመር እውነት ሁሉ ይህን ለውጥ ማየት እንዳለበትና
ነገሮችን ሲመለከት ዘለላለም የተወሰኑና የአለቀላቸው
አድርጎ አለመገንዘብ ዋና ቁም ነገር ነው ።

እንደገናም ሲተነተን ግልፅ የሆነውን የዕውነት ጸባይ
ማምጣት አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ለምንድነው ? ምክ
ንያቱም በተግባር ሰዎች ፣ በተለይም የሰብአዊ ሕብረተ ሰብ
ንና በዚሁም የተነሣ የእያንዳንዱ ወንድና ሴት ዕውነታ
የሚአገኙት (የሚቀርቡት) በዚህ ዓይነት መንገድ አይደለ
ምና ነው ። ብዙ ሰዎች « ምርት ለትርፍ ማምረት የሰብአዊ
ሕብረተሰብ ቀዋሚ ጸባይ ነው » ብለው ያምናሉ ። እናም

ይህ ስለሆነ ፡ «እንደነበረ ወደፊትም ይሆናል » የሚለው ጸንሰ ሀሳብ ብዙውን ጊዜና የትም ቦታ ይሰራጫል ፡ በግለ ሰቦችና በሕብረተሰብ ዕድገት ውስጥም ቀዋሚ ገደብ ይሆናል ።

በትክክል ከመገንዘብ የተነሣ የሚገኝ መጠቅ ያለ ነጥብ አለ ፡ « ሁሉም ነገር ይለወጣል ፡ ይዳብራል ወይም ይሞታል » የሚል ። እንዲህም ስለሆነ እያንዳንዱ ነገር የደረሰበትን ደረጃ መገንዘብ ከፍተኛ ተግባራዊ ዋናነት አለው ። አንድ ገበሬ አንድ ላም ሲገዛ ይህ በደንብ ግልፅ ይሆንለታል ፣ ቤት የሚገዛ ሰውም በአእምሮው ሁኔታውን ይረዳል ፡ ስለሆነም በዚህ ቀላል የኑሮ ተግባራዊ ሂደት ውስጥ ማንም አጠቃላይ ሕጎችን አይዘነጋቸውም ። ግን እንደጋጣሚ ሆኖ ሰብአዊ ተቋሞችን በሚመለከት ረገድ በተለይ የአመራረት ሥልትንና ከዚህም ጋር የሚሄዱትን ሀሳቦች (ኋላ የማእድገትን) መተንበይና እንዲህ ናቸው ማለት የሚደግፍ አይደለም ።

የነገሮች የእርስ በእርስ ጥገኝነትና ነገሮችም በለውጥ ሂደት ላይ መሆናቸው ግልፅ የዕውነታ ጸባይ እንደሆነ ተረድተናል ። በዳያሌክቲካዊ የእውነታ አቀራረብ ውስጥ ሶስተኛው ጸባይ ግልፅ ያለ አይመስልም ፣ ቢሆንም እውነትነቱ አንድ ጊዜ ከታተተ መገንዘብ ቀላል ነው ።

ይህ ጸባይ እንዲህ ነው ፡— በነገሮች ውስጥ የሚፈጠረው ዕድገት ቀላልና ውጣ ውረድ የሌለበት አይደለም ፡ ነገር ግን በደንብ ካየነው ቅራኔው ትብ በሆነበት መንገድ ሁሉ አንድ የተወሰነ ነጥብ ላይ የተፈጥሮ የመሸጋገሪያ ሁኔታ ይፈጥራል — እመርታ ። በአንድ ነገር ውስጥ ልዩ የሆነ ጸባይ ካለ ቀላልና ለስለስ ያለ ዕድገት ረጅም ጊዜ



ሊካሄድ ይችል ይሆናል ። እንደገና የውኃውን ምሳሌ ብን ወስድ ሙቀቱ ከፍ እንዲል ቢደረግ የውኃን አጠቃላይ ጸባዮች እንደያዘ ውኃው ውኃ እንደሆነ ይቆያል ፤ ግን በውስጡ ያለው ሙቀት ይጨምራል ። እንደዚሁም ፣ ሙቀቱ እንዲቀንስ ቢደረግ ውኃው ውኃ እንደሆነ ይቀራል ፣ ግን በውስጡ ያለው ሙቀት ይቀንሣል ።

ይሁንና በዚህ የመለወጥ ሂደት አንድ የተወሰነ ደረጃ ላይ — የመፍያ ወይም የመቀዝቀዣ ነጥብም ይሁን — ቅፅበታዊ ሁኔታ ይፈጠራል ፤ ውኃው ሙሉ በሙሉ ጸባዩን ይለውጣል ፣ ከእንግዲህ ውኃ አይደለም ፣ ግንተን ወይም በረዶ ነው ። ይህ የዕውነታ ጸባይ የአንድ የተለየ ነገር ይዘት ማነስ ወይም መብዛት ሙሉ በሙሉ አንድን የውጤት ጸባይ እንደሚለውጠው በተለይ በኬምስትሪ ውስጥ ግልፅ ነው ።

በሰብአዊ ሕብረተሰብ ውስጥ በሕብረተሰቡ ባሕርይ ላይ ያለምንም መሠረታዊ ለውጥ የረጅም ጊዜ የቀስ በቀስ ለውጥ ይካሄዳል ፤ በኋላም እመርታ ይመጣል ፣ አብዮት ይኖራል ፣ አሮጌው ዓይነት ሕብረተሰብ ፍርክስክሱ ይወጣል ፣ እናም አዲስ ዓይነት የሕብረተሰብ ሕልውና ተከሥቶ የራሱን የዕድገት ሂደት ይጀምራል ። ስለዚህ በመልከኛው ሕብረተሰብ ሥርዓት ውስጥ ፣ ምርት ለአገር ውስጥ ብሎት በነበረበት ትርፍርፍ ምርትን የመግዛትና የመሸጥ ሁኔታ ለገበያ የሚሆኑ ምርቶችን ወደማምረት አተኩረና ይህም ወደ ካፒታሊስት ምርት ጅመራ አመራ ይህ ሁሉ የቀስ በቀስ ዕድገት ሂደት ነው ፤ ግን አንድ የተወሰነ ነጥብ ላይ እያደገ የመጣው የካፒታሊስት መደብ ከመልከኛው መደብ ጋር ተጋጨ ፣ ወረውረውም ፣ እናም የምርትን ጸባይ ሁሉ አሸጋገረው ለወጠው ። የካፒታሊ

ስት ሕብረተሰብ የመልከኛውን ቦታ ተካውና በጣም ከፍ
ተኛ ኃይል ያለውን ዕድገት ጀመረ ።

አራተኛው ዲያሌክቲካዊ ጸባይ « ከዚህ በፊት ያየነ
ውን » ሁለንታዊ የሆነውን ዕድገት የሚአመጣው ምንድ
ነው ? የሚለው ፅንሰ — ሀሳብ ነው ። ስለ ነገሮች ያለን
ዲያሌክቲካዊ አቀራረብ እንዲሚአሳየን ነገሮች ቀላልና
ሙሉ በሙሉ አንድ ዓይነት ጸባይ የላቸውም ፤ ማንኛውም
ነገር ተጻራሪና የማይጻረር ጉኖች አሉት ፡ ሁሉም ነገር
በውስጡ የመዳበር ጸባዮች አሉት — ዋና ወራሽና ገዥ
የሆነው አሳፉ ጠፊ ገዥነቱ እየቀነሰ የሚሄደው ማለት
ነው ። አንድ ጸባይ ሁልጊዜ ይስፋፋል ሌላው ጸባይ ደግሞ
ያን መስፋፋት ይቋቋማል ። እናም በነዚህ ተቃራኒዎች
መካከል ያለው ግጭት ነው ( የሌላውን የበላይነት ለማ
ጥፋት በሚወለደው ጸባይ ትግልና የበላይ የሆነው አዲ
ሱን ጸባይ እንዳያድግ እንዳይዳብር ለማድረግ የሚአካሂ
ደው ትግል) የቀድሞውን ለመሻር ሲል ኃይል በመጠቀም
አወዳድሞ አሮጌውን ትግል እንዲከትም የ ሚአደርገው
አጠቃላይ ዋናው የለውጥ ሂደት ይዘት ።

ይህ በደንብ ግልፅ ሆኖ የታየው በሰብአዊ ሕብ
ረተሰብ ነው ። በእያንዳንዱ የታሪካዊ ደረጃ በመ
ደቦች መከፋፈል ነበር ፤ አንደኛው ሲአድግ ሌላው
የሚሞትበት ። ይህ ነበር በመልከኛው ሕብረተሰብ ውስጥ
ካፒታሊዝም ከአምቡጥነት እያደገና ፤ አድጎም ከመልከ
ኛው ጋር ከቀን ቀን ወደግጭት እየገባ ሲሄድ የታየበት ።
በካፒታሊስት ጊዜም ይኸው ነው ፡— « የወደፊቱ ዘመን
በጁ የሆነው » የሠራተኛው መደብ እያደገ መጣ ። የካፒ
ሊስት ሕብረተሰብ ሁሉም አንድ ዓይነት ዓይደለም ፤ ከበ



ርቴው ሲአድግ ሠራተኛውም እንዲሁ ። በነዚህ መደቦች
መካከል ያለው ግጭትም ይዳብራል ። ይህ ቅራኔ ነው ፤
ይህ ግጭት ነው በካፒታሊዝም ውስጥ ከመደቦች መከፋ
ፈል በሚመጣት የዕለት ተዕለት ትግሎች በመጨረሻ
ትብ ወደሆነው እመርታ መርቶ የሕብረተሰብን አብዮታዊ
ለውጥ የሚአመጣው ።

. . . .

አሁን « ዲያሌክታዊ ቁስ አካልነት » በተባለው
ሀረግ ተሸፍነው የሚገኙትን የተለያዩ ሀሳቦች በአንድነት
ለማስቀመጥ ይቻላል ። ይህ አመለካከት ነው « እውነታ
ስለእርሱ ከአለን አስተያየት ተለይቶ ይኖራል » የሚለ
ውን የሚይዘው ፤ እናም ይህ እውነት ተበጣጥሶ ለየብቻ
የተቀመጠ አይደለም ፤ አንዱ በአንዱ ላይ ጥገኝነት ያለው
እንጂ ፤ በእርጋታ ላይ አይደለም ፡ በመሞትና በመውለድ
በተሻሪነትና በሻሪነት በአጠቃላይ በቅ ስቃሴ ላይ እንጂ ።
ይህ ዕድገት እመርታ ተፈጥሮ አዲስ እስከመጣ ድረስ
የቀስ በቀስ ነው ፤ ዕድገቱ የሚፈጠረው በውስጣዊ ግጭ
ትና ሻሪው በተሻሪው ላይ ማቆጥቆጥ በሚአደርገው ትብ
የትግል እመርታ ነው ።

ይህ የዓለም ግንዛቤ ነው ሰብዓዊ ሕብረተሰብን በመ
ጨመር ስለ እውነታ ያለውን የማርክሲዝም አቀራረብ
ከሌሎች በትክክል የሚለየው ። እርግጥ ዲያሌክታካዊ
ቁስ አካልነት ከእውነታ በላይ ያለ አይደለም ወይም ደግሞ
ዓለምን የሚስማማ በሰዎች የግምት አስተሳሰብ የተፈጠረ
ርዕዮተ ዓለምም አይደለም ። እንዲአውም ፡ በጣም ትክ
ክል በሆነ መንገድ ዓለምን የሚወክልና የሚቀርብ ፡ እን
ዲሁም ከተጠራቀመ የሰው ዕውቀትና ገጠመኝ የሚገኝ
ነው ። በማርክሲስቱ አንጎል ውስጥ ነው ፤ ምክንያቱም
በውጫዊው ዓለም ውስጥ ነውና ፤ የነገሮች ዕውነተኛ ቅርፅ
ነው ።

ይህ እንዲህ እንደሆነ የሚአረጋግጡት በየጊዜው
የተገኙት የሣይንስ አሠሣዎች ናቸው ። በዳይሌክ ቲካዊ
አመለካከት አንጻር ተፈጥሮን ሚመረምሩት የሳይንስ
ሊቆች አዲስ ዕውነቶችን ለማግኘት እንደሚረዳና ሊብ
ራሩ ሊገለጹ የማይችሉ መስለው የሚታዩ ነገሮችን ሁሉ
በመድረክ ላይ እንደሚአመጣ ተረድተዋል ። በአሁኑ
የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ በሰብአዊ ሕብረተሰብ አንጻር
የዲያሌክቲካዊ ቁስ አካልነት አመለካከት በጣም ዋናነት
አለው ።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ቀደም ብለው የተሰጡ ምሳ
ሌዎች የሕብረተሰብን ዕድገትና ከዚህ ዕድገት የሚመነ
ጩትን ሀሳቦች በሚመለከት ረገድ የማርክሳዊያንና ማር
ክሣዊ ባልሆኑት ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለማ
ሳየት ያገለግላሉ ። በሌሎች ምዕራፎች ሌሎች ምሳሌዎ
ችም አሉ ። ግን በሰዎች ሕይወትና ክንዋኔ ውስጥ የዕው
ነታ አመጣጥ ጥያቄዎች ላይ ጠለቅ ያለ ጠቃሚ ጥናት
መውሰድ አስፈላጊና ተግባራዊ ነው ።

ከዚህ በፊት የቁስ አካላዊ አመለካከት ማለት የቁስ
አካል ፣ ውጭአዊው ዕውነታ እንደቀዳሚና አሳብ ደግሞ
እንደተከታይ ሆኖ ከቁስ አካል እንደሚንጸባረቅ ተነግሮ
ነበር ። ከዚህ ተያይዞ የሰዎች አካላዊ ሕልውናና እነሱም
ሕይወታቸውን የሚጠብቁበት መንገድ ሰዎች ከሕይወታ
ቸውና ከአኗኗር ዘዴአቸው ከሚያስገኙት ሀሳብ ቀድሞ የሚ
ገኝ ነው ። በሌላ አነጋገር ፡— ተግባር ከንድፈ — ሀሣብ
ቀድሞ ይመጣል ። ሰው ራሱን ነዋሪ ሆኖ ያገ
ኘው ስለራሱ ከማሰቡ ከረጅም ጊዜ በፊት ነበር ። ግን
ሀሳቦቹንም እያዳበራቸው ሲሄድ ካለው ተግባር ጋር ተዛ
መዱ ፣ ማለትም ንጹሕ ሀሳብና ተግባሩ ባንድነት ተጓዙ ።



ይህ በጥንታዊ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም የሕብረተሰብም
ደረጃ ነበር ። ሰዎች ኑሮአቸውን ለመመሥረት የተገለገሉ
ባቸው ተግባራዊ መንገዶች የሀሳቦቻቸው መሠረት
ናቸው ። ፖለቲካዊ ሀሳቦቻቸው ከዚሁ ይመነጫሉ ፤ ፖለ
ቲካዊ ተቋሞቻቸው ያለውን የአመራረት ሥልት ለማቆ
የት ከሚከሄደው ተግባር የሚመጡ እንጂ ከሥውር (ምስ
ጢር) መርሆዎች የሚፈልቁ አይደሉም ። እያንዳንዳቸው
ተቋሞችና ሀሳቦች በዘመኑ ከነበረው ተግባር የተንጸባረቁ
ናቸው ። ከዚህ ውጭ ነጻ የሆነ ከሀሳብ ሀሳብ እየዳበረ
የሚሄድ ታሪክና ሕልውና የላቸውም ፤ ግን የሚዳብሩት
ቁሳዊው ሥልተ ምርት ሲለወጥ ነው ።

ግን አሮጌዎቹ ሀሳቦችና ተቋሞች ከአዲሱ ጋር ጎን
ለጎን ይኖራሉ ። ከመልከኛው የአመራረት ሥልት
ውስጥ የተገኙት ሀሳቦች ለመኳንንቱና ለዘውዳዊው ክብር
እንደመስጠት ያሉት — በካፒታሊስቷ ብሪቴይን ውስጥ
ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ፤ ከካፒታሊስት የአመራረት
ሥልት የተገኙ ሀሳቦችም አሉ ፤ አሮጌዎቹ መልኮች ተሻ
ሽለው ከመኳንንቱ መወለድን ሳይመለከት ሀብትን ብቻ
በማየት የሚያደርግ ክብር ። ኋላም የሶሻሊስት ሀሳቦች
አሉ ፤ ምርት በካፒታሊዝም ውስጥ በየጊዜው ሕብረተሰ
ባዊ ጸባይ ፣ ጋርዮሻዊና የአንዱባንዱ ጥገኝነት እያያዘ በመ
ምጣቱ የተገኙ ። እነኝህ ሶስቱ ዓይነት ሀሳቦች በአሁኑ
የሕብረተሰብ ዘመን ጊዜአዊ ተቀባይነት ያላቸውና ፍጹ
ማዊ ዕውነት (Absolutely True) ያልሆኑ ቀዋሚነታቸው
ያልተመሠከረላቸው ናቸው ።

ይህም ይሁንና ማርክሲዝም ሁሉንም በእኩልነት
እውነት አይደሉም ብሎ ይወስዳቸዋል ማለት አይደለም።
እንዲአውም ማርክሲዝም የመልከኛውን ሀሳቦች ሙሉ

በሙሉ እንዳለፉ ፣ የካፒታሊስቱ ሀሳቦች የቁልቁለት ደረጃ
በመውረድ ላይ እንዳሉ ፤ የሶሻሊስት ሀሳቦች ጠቃሚነታ
ቸው እየተረጋገጠ እንደሚሄድ ነው የሚአየው ። ከዚህም
በላይ ይህ በዚህ ደረጃ የመምጣትም ብቻ አይደለም ። ከጥ
ቅምት ፲፱፻፲፯ ዓ ም ጀምሮ በዕለታዊ ገጠመኝ የሶሻሊስት
ሀሳቦችን መሞከር ተችሏል ፤ ከእውነታ ጋር ሊሠምሩ
መቻላቸውን ለማረጋገጥ ማለት ነው ። ዋናው ሀሳብ ግዙ
ፍና ውስብስቡ ዘመናዊ የምርት መኪና( Machiuery ) ለት
ርፍ ሳይሆን ለጠቀሜታ ብቻ ሊዘጋጅ እንደሚቻል በተ
ግባር ተመስክሯል ። ገጠመኝ እንዳሳየው የምርትም በሠ
ፊው መጨመር ፣ የቀውሶች መወገድና የሰዎች የኑሮ ደረጃ
በማያቋርጥ ሁኔታ እያደገ መሄድ ማለት ነው ። በሌላ
አነጋገር የሶሻሊስት ሀሳቦች ከምጣኔ ሀብታዊና ከሕ
ብረተሰብ ዕድገቶች ተገኝተው በማርክስ ሳይንሳዊ
ዘዴ የአደጉት ዕድገቶች እስከ ፲፱፻፲፯ ዓ. ም. ድረስ
ሳይንሣዊ መላ — ምት ሆነው ቀርተው ነበር ፣ አሁን
ግን ገጠመኞች እውነት መሆናቸውን አስመሰከሩ ።

የሩሲያ ኮሚውኒስት ፓርቲ ንቃታዊ ከንዋኔ አመለ
ካከቱ ማርክሳዊ የሆነው ፣ የአሮጌውን ሥርዓት ወርውሮ
የአዲሱን መቋቋም አምጥቷል ።ከዚያ ነጥብ ጀምሮ የሩሲያ
ሕዝብ ብዙዎቹ አመለካከቻቸው ማርክሳዊ አይደለም —
አዲሱን ሥርዓት መለማመድ ጀመረ ፤ በተግባር ሶሻሊስት
ለመሆን መሆኑ ነው ። በዚህ ላይ በመንተራስ የንድፈ —
ሀሳባውያን ሶሻሊስቶች ( Theoretical Socialists ) የንቃት
ትምህርት ሥራቸው ፈጣንፍሬ እያሳየና የትምህርትና የተግ
ባር ውህደትም የአጠቃላዩን ሕዝብ አመለካከት በፍጥነት
እያሻገገረው ሂደ ።



ማርክሲዝም « ዲያሌክቲካዊ ቁሳአካልነት » ስለተ
ባለው አመለካቱ አይደለም ይበልጥ መጤን አለበት የሚ
ለው ፤ ግን ይህ አቀራረብ ለማንኛውም ሳይንስ መስክ አን
ድን ተመራማሪ እውነቶችን እንዲገነዘባቸው መርዳቱ
ላይ ነው ዋናው ቁም ነገር ። ዲያሌክቲክስ በእያንዳንዱ
መስክ የተለዩጥናት መወሰድ ስላለበት ዝርዝር ሁኔታ
ምንም አይነግረንም ። ማርክሲዝም — ከፍተኛ ግንዛቤና
ክብደት ሊሰጠው የሚገባና ሳይንሳዊ እውነት ሊገነባ
የሚችለው ዕውነቶችን ከሩፍሎ በማጥናት ላይ ተመስርቶ
መሆኑን አይክድም ። ግን የሚአስገነዝበው አንድ ነገር ባን
ደኛው ላይ ጥገኝነቱ ሲመረመር እውነት መሆኑን ፣ ዕድገ
ታቸውን ፣ ከመጠን ወደ ዓይነት የመለወጣቸውን ፣ ውስ
ጣዊ ቅራኔአቸውን ፣ የሚገኘው ሳይንሣዊ እውነት ወሰን
የሌለውና ይበልጥ ጠቃሚነት እንዳለው ፣ ይበልጥ እውነት
ነቱን ፣ እና ስለዚህም ለሕብረተሰብ ይበልጥ መጥቀሙን
ነው ።

በሕብረተሰብ ሳይንስም ውስጥ ይህ ጥሩ ቦታን ይይ
ዛል ። የእያንዳንዱ ወንድና ሴት ጥናት ወይም በሙሉ የሕ
ብረተሰቡ በአንድ ጊዜና ባንድ ቦታ ፣ በጣም የተወሰነ
ጥቅም ብቻ ሊአስገኝ የሚችል መደምደሚያ ነው የሚአ
መጣው ፤ በሌላው የሕብረተሰብ ክፍል ላይ ወይም ለዚ
ያው ሕብረተሰብ በሌላ ጊዜ ሊውል አይችልም ። የሕብ
ረተሰብን ማርክሳዊ ጥናት ልዩ ዋጋ የሚአስገኘው ሕብ
ረተሰቡ አሁንም እዚህ በሚኖርበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን (እር
ግጥ ይህም አስፈላጊ ነው) ግን ባለፈው ጊዜም ስለ ኖረ
ውና በውስጣዊ ቅራኔው ምክንያት ስለአደገው ሕብረተ
ሰብ ሠፊ ምርመርና ጥናት ማካሄዱ ላይ ነው ። ይህ ለስ

ዎች « በክንዋኔ ላይ ያለውን ሂደት የሚወስኑ የመጀ መሪያውን ንቃታዊ ዕድል » ይሰጣቸዋል ። ይህም ማርክስ ለማየት ጥንቃቄ ከወሰድን « ፊት ለፊታችን በዓይናችን ሥር የሚካሄደውን እንቅስቃሴ ማትኮር ነው » ብሎ የተናገረውን ነው ። በሌላ ሥውር መርሆዎች ወይም ያለፈውን ነባር አመለካከት በሚወክሉ አስተያየቶች ሊገኝ የማይችል ለክንዋኔአችን መምሪያ ይሰጠናል ።








# የተግባር መመሪያ

ማርክስ ከጥንት ሥራዎቹ ባንዱ «ፈላስፎች ዓለምን በተለያዩ መንገዶች ተርጉመዋታል ፤ ይሁንና ቁምነገሩ ከመለወጡ ላይ ነው» ብሎ ነበር ። ለማርክስ ስለ ዓለም ያለው አመለካከት ባሕርይ ይህ ነበር ። ማርክሲዝም እንዲሁ ብቻ አካዳሚአዊ ሳይንስ አልነበረም ፤ ግን ዓለምን ለመለወጥ ሰዎች የሚጠቀሙበት ዕውቀት ነው ።

ካፒታሊዝም የሚአልፍ ደረጃና በሶሻሊዝም የሚወረስ (የሚተካ) መሆኑን ብቻ ማወቁ በቂ አልነበረም ፤ ይህ እንዲሁ እራሱ በንጹህ ምጣኔ ሀብታዊ ለውጦች ውጤት ምክንያት ሊመጣ አይችልምና ። ምንም ብዙ ቀውሶች ቢፈጠሩ ፤ ምንም በካፒታሊዝም ምክንያት ብዙ ሥቃዮች ቢመጡም ፤ ውኃ ሙቀቱ ወደ ፻፸፰-ሩ ዝቅ ሲል ወደ በረዶነት እንደሚለወጥ ሁሉ ካፒታሊዝም በቅፅበት ወደ ሶሻሊዝም የሚለወጥበት ነጥብ የለም ። ሰው ከአንድ የአመራረት ሥልት ወደሌላው የሚአሻግር እመርታ ሰብአዊ የክንዋኔ ውጤት ካልተካሄደ በቀር ሊፈጥር አይችልም ። ማርክሲዝም ፤ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ፤ የሰውን ክንዋኔ ወደ መጨረሻው ግብ ሊመራ የሚችል ዕውቀት ከሰዎች ገጠመኝ ነው የሚአገኘው ።

ሕብረተሰብን ስለሚለውጠው ጠቅላላ የክንዋኔ ዓይነት የማርክስ አስተያየት በምዕራፍ ፪ እንደተገለጸው ፡— የመደብ ትግል ነው ፤ በአሁኑ ደረጃ በሠራተኛው መደብ

እና በከበርቴው መደብ የሚካሄድ ትግል ። ግን ይህ አጠቃላይ ቀመር በዕለታዊ ገጠመኝ ተሚልቶ ፤ በእያንዳንዱ ሀገር ሁኔታና በእያንዳንዱ የዕድገት ደረጃ ላይ መዋል አለበት ።

ማርክስ ይህን ፕሮብሌም በመከታተል ይሠራ የነበረው ሥውር በሆነ መንገድ ሳይሆን ግን በየዕለቱ የሚሆነውን ነገር በመመርመርና ወደፊት የሰው ልጅ ዕድገት መሠረት ይሆናሉ የሚላቸውን የተለያዩ የሠራተኛ መደቦች ድርጅቶች እንዲገነቡ በመርዳት ነበር ። የታወቀው የ፲፰፻፵፰ ዓ. ም የኮሚውኒስት መግለጫ የኮሚኒስቶች ማህበር አዋጅ ነበር ፡— ለብዙ ዘመናት ማርክስ ንቁ ተሳታፊ የነበረበት ማኅበር መሆኑ ነው ፤ የዓለም አቀፍ የሠራተኛ ሰዎች ማኅበር የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ተብሎ የሚታወቀው በ፲፰፻፷፬ ዓ. ም. በእርሱ ጥረት ነው የተመሠረተው ። በዘመኑ ከነበሩት የእንግሊዝና የሌሎችም አገሮች የሠራተኛ ንቅናቄዎች ጋርም የቅርብ ግንኙነት ነበረው ።

በነዚያ ዘመናት ብቻ ነው የሠራተኛው መደብ አነስተኛ ክፍል በሙያ ማህበርና በሕብረት ሥራዎች እንኳን ቢሆን የተደራጀው ። እናም የትም አገር የሠራተኛው መደብ ፓርቲ መጠኑ ወይም ተፅዕኖው ምንም ይሁን አልተመሠረተም ነበር ። በብዙዎቹም አገሮች ራሱ የሠራተኛው መደብ እንኳን አልነበረም አልተመሠረተም። ከእንግሊዝ ውጭ ፡ የካፒታሊስት ኢንዱስትሪ ገና በጨቅላነቱ ነበር ፤ በብዙ አገሮችም እያደገ የመጣው የካፒታሊስት መደብ ራሱን ለማቋቋም ከመልከኛው መሣፍንትና አገልጋዮች ጋር ትግል ያካሄድ እንደነበር ፡ ግልፅ ነው።



ያለፈው ምዕተ — ዓመት ማለቂያ አካባቢ በብዙ አውሮጳውያን አገሮች የሠራተኛው መደብ ፓርቲዎች ተፈጥረው በፓርላማ ውክልናን ለማግኘት ቻሉ ፤ በእንግሊዝ የሠራተኛው ፓርቲ ምዕተ — ዓመቱ ሲአልቅ ተመሠረተ ፤ ይሁንና መሪዎቹ በአመለካከት ሶሻሊስት ከመሆን ይልቅ ሥርነቀሎች ነበሩ ።

በዚህ ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ በምዕራፍ ፬ የተገለጸው ካፒታሊዝም ወደ ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ ሲደርስና « የጦርነቶችና አብዮቶች ወቅት » ሲከፈት የመደብ ትግልስትራቴጅና ታክቲክ ማርክስና ኤንግልስ ከሚኖሩበት ዘመን ይበልጥ ማደግ ነበረበት ። ይህ ማክርሲዝምን በኢምፔሪያልዝም ዘመን በተግባር የማዋል ሥራ የተካሄደው በሌኒን ነው ።

በዚህ ዘመን አሮጌው ዓይነት የሠራተኛ መደብ ፓርቲ ክንዋኔው አብዛኛውን ጊዜ ፓርላማዊና ፕሮፓጋንዳዊ የነበረው ብቁ እንዳልሆነ አሳዩ ። የካፒታሊዝም ማክተም በአጀንዳዊ ሆነ ፤ ይህ በመሆኑ አዲስ ዓይነት ፓርቲ አስፈላገ ። ፓርላማዊ ትግሉን በፋብሪካዎች ውስጥና በመንገድ ላይ ካለው ትግል የሚአዋህድ ፡ ሠራተኛውን መደብ ካፒታሊዝምን ደምስሶ ሶሻሊዝም ወደሚገነባበት ሊመራው የሚአልም ( Aimed ) ፓርቲ ማለት ነው ።

ማርክስ በመደጋገም አሮጌውን የገዥ መደብ የሚደረባው አዲስ መደብ ከሌላው የሕዝብ ክፍል ዕርዳታ እንደሚአስፈልገው ገልጿል ። ሠራተኛው መደብ በገዋ ውስጥ የሚኖር አይደለም ፤ ሌሎችንም መደቦችና የመደብ ክፍሎችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እና ከአገር አገር የሚለያዩትንም ጨምሮ በዙሪያቸው በደንብ የተወሰነና ዕውነት

የሆነ ዓለም አላቸው ። የአዲሱ ዓይነት የሠራተኛ መደብ
ፓርቲ የስትራቴጅ ችግር ችግርነቱ የሠራተኛው መደብ
ብቻ ሳይሆን በተወሰነ ዘመን ለሕብረተሰብ ዕድገት ዋና
ጠላት የሆነውን ለመጣልና ለማሸነፍ የሌሎችም የሕዝብ
ክፍሎች ተግባር ጭምር ችግር ነው ።

የሠራተኛው መደብ ዋና ጠላቱን ለመቋቋም እንዲ
ችል ከሌሎች ክፍሎች ጋር የሚአደርገው የመደብ ኪዳን
ንድፈ — ሀሳብ በተግባር ተሠርቶ የታየው በሩሲያ ሁኔታ
ላይ በሌኒን ነው ፤ ይህ ማርክሲዝም ለሠራተኛ መደብ
ክንዋኔ እንደመምሪያ ሆኖ ከፍተኛ ዕድገት እንዲአሳይ
ዓይነተኛ ሆኗል ።

ሠራተኛው መደብ ብቻ ነው ብቃት ኖሮት ካፒታሊ
ዝምን ሊዋጋ የሚችለው ፤ ካፒታሊዝም በተስፋፉ መጠን
የዚያኑ ያህል ያድጋል እናም በቀጥታ በካፒታሊስቱ መደብ
ይበዘበዛል ። ስለሆነም በካፒታሊስቱ መደብ አንጻር የመ
ደቦች ሕብረት ፅንሰ ሀሳብ ሠራተኛው መደብ የሕብረቱ
አስኳልና መሪው ኃይል እንደሆነ ያመለክታል ። ሠራተ
ኛው መደብ ግን ሕብረቱን የሚፈልገው ምክንያቱም የከ
ረብቴውን መደብ በሚዋጋበት ጊዜ ሌሎች ክፍሎች ወደ
ሠራተኛው መደብ ወይም ወደ ካፒታሊስቱ ስለሚሳቡ
ነው ። ሌሎችን ክፍሎች ወደ ሠራተኛው መደብ ኪዳን
ማስገባት ፤ ካፒታሊስቱ ከነዚያ ክፍሎች ያገኝ የነበረ
ውን ድጋፍ ማሳጣት ይሆናል ።

በዋናው የሕብረተሰቡ ዕድገት ጠላት ላይ በሠራተኛ
ውና በሌሎችክፍሎች መካከል ሕብረት የመፍጠሩ ሁኔታ
ይበልጥ አመቺ እየሆነ ይሄዳል ፤ ምክንያቱም በካፒታሊ
ዝም የመኖፖሊ ደረጃ ላይ ምጣኔ ሀብታዊ ኃይል (ፖለቲ



ካዊም ነው) በጣም ሀብታምና ጥቂት ቡድኖች እጅ ውስጥ
ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደለበ ስለሚሄድ ነው ። የካፒታሊስቱ
መደብ ሁልጊዜም በጣም የበለጸጉና መለስተኛ የሆኑ ግለ
ሰቦች በውስጡ እንዳሉበት እውነት ነው ። ግን በዓለም
አቀፍ ሞኖፖሊዎች ደረጃ ሞኖፖሊ ካፒታሊስቶች ከብ
ዙዎቹ መለስተኛ ከበርቴዎች በትልቅ ድንበር ተከፋፍለ
ዋል ። የሞኖፖሊዎች ፍላጐት በኢንዱስትሪና በንግድ
ላይ ይዞታቸውን ለማስፋፋት ሲሉ ፤ ለመበዝበዝ አዲስ
ግዛት አሸንፎ መያዝና በሌሎች አገሮች ካሉ ተወዳዳሪ
ዎቻቸው ጋር ሲዶልቱ (በመካከላቸው ገበያን መከፋፈል ፤
የተመን ውሣኔ ስምምነቶች መሥራትና ፤ ወይም በታሪፍ
መዋጋት ካልሆነም በጦርነት ) ከአነስተኛ ባለሱቆችና
ቀሪዎች ፍላጐት ጋር በቀጥታ ግጭት ይፈጥራሉ ። አነ
ስተኞች በሞኖፖሊዎች ኃይል ከሕልውና ተጨምቀው
የተጣሉ መስሎ ይሰማቸዋል ። ከአንዱ ጥያቄ ወደ ሌላው
ስንተላለፍ ፤ በመጀመሪያ እንደ ግለሰብ ብቻ ፤ ግን እን
ዳዬ እንዳአጠቃላዩ ክፍል — አነስተኛ ባለሱቆች እና
ቀጣሪዎች ፤ ገበሬዎችም መኖፖሊዎችን« እንደዋና ጠላ
ታቸው » አድርገው ይወስዳሉ ።

ይህ ቅዋሜ የሚመጣው በቀጥታ ከምጣኔ ሀብታዊ
መሠረት ብቻ አለ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው ። ም
ጣኔ — ሀብታዊ ሞኖፖሊ ሠራተኛውን መደብና የቅኝ
ግዛት ሕዝቦችን እንዲሁም አነስተኛ ካፒታሊስቶችን ከመ
ቃዎም የሚመጣው የማይቀረው ግፊት በሀገር ውስጥና
በውጭ ሀገር አድሃሪ ፖሊሲዎችን እንዲአወጣ ያደርገዋል።
አነስተኛ ካፒታሊስቶችና መካከለኛ መደቦች ፤ በሙያ
ቸው የሠለጠኑ ሠራተኞችና የምሁራን ሠፊው ክፍል ፤ ከጥ
ንቱ የካፒታልስት ዘመን በተያያዘ ለዘብተኛና ዲሞክራሲያ
አዊ ውርስ ውስጥ የመጡት እነዚህን ውርሶች (Traditions)

የሚጥሉባቸውን ሞኖፖሊዎች ሥሩባቸው ። የዚህ ንጹህ
የሌለው የፋሺዝም አምባገነናዊነት ነው ።
ምሳሌ በሰፊው « ቅዋሜው » መድረክ ላይ የወጣው ፤
ዲሞክራሲአዊ ድርጅቶችንና ተቋሞችን ሰባብሮ በሰፊው
ተቀባይነት ያገኙትን ሰብዓዊ መርሆዎች የጣሰው ገደብ
የሌለው የፋሺዝም አምባገነናዊነት ነው ።

በእነዚህ ሁኔታዎች ፋሺስቶች ለሰላምና ለሕብረተ
ሰብ ዕድገት ዋና ጠላት ኗታቸው በሰፊው ሕዝብ ሲታይ ፤
የሠራተኞችና የመካከለኛ ክፍሎች ፍላጎቶች ተስማሙና
ሠፊ ሕብረት ለመፍጠር አስቻለ—« ሕዝባዊ ግምባር »
ፋሺስቶችን በመቃወም መሆኑ ነው ። የሠራተኛው
ፍላጎት ከሌላው የሕዝብ ክፍል ፍላጎት ከሌ
ጣማ ካልተስማማ በቀር ሌላ እውነት የሚሆን ኪዳን
(ሕብረት) ሊፈጠር አይችልም ። የራሳቸውን ፍላ
ጐት አለማስማማት ወይም እንደራሳቸው እውነተኛ ዓላማ
በኪዳኑ ውስጥ ጓደኞቻቸውን ማታለሉ የሠራተኞች ወይም
የአጋሮቻቸው ጥያቄ አይደለም ። የመደብ ኪዳን ባሕርይ
ለጊዜው ፡ በልዩ ሁኔታዎች ፤ የኪዳን ሠሪዎች ፍላጎት
መመሳሰል ነው ። ይህ ነው የስፓኝ ሠራተኞችን ፤ ገበሬ
ዎችን ፡ መካከለኛ መደቦችን ፡ አነስተኛ ካፒታሊስቶች
ንና ብሔራዊ ቡድኖችን በ፲፱፻፴፪ ዓ. ም. ከትልልቅ
መሬት ከበርቴዎችና ባንኮች እንዲሁም ከጄኔራል ፍራ
ንኮ ጋር ከተባበሩት የውጭ ወራሪዎች አንጻር በመቆም
ኪዳን (ሕብረት) እንዲፈጥሩ የአደረጋቸው ።

በጣም ብዙውን የሕዝብ ክፍል ከውጭ ተዋጊዎ
ችና ወራሪዎች አንጻር በማቆም ሕዝቡን ለትግል የሚአ
ሳትፉ ለምሳሌ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንደነበረው
ያለ « ብሔራዊ ግንባር » እንደነበሩ ታሪክ ብዙ ምሳሌ



ዎችን አሳይቷል ። የውጭ ኢምፔሪያሊስት ገዥዎ
ችን ለመታገል የቅኝ ግዛት ሕዝቦች የሚፈጥሩት
« ብሔራዊ ግንባር » ግልፅ ምሳሌ ነው ። በመጀመሪያ ፣
እነዚህ የብሔር አርነት ትግሎች አብዛኛውን ጊዜ የሚ
መሩት እየደጉ በሚሄዱት ካፒታሊስቶች ነው ። ግን የካ
ፒታሊዝም በቅኝ ግዛት አገሮች ውስጥ ዕድገት ከውጭ
የኢምፔሪያሊስት ብዝበዛ ጋር የሠራተኛውን መደብ ይፈ
ጥራል ፤ እናም ይህ በቁጥር በአደገና በተደራጀ ቁጥር
የአርነት ትግሉን ለመምራት ኃይሉን እየጨመረ ይሄዳል።
የማርክሳዊ ፓርቲዎች መመሥረት ። ይህ ሂደት ወደ ፊት
እንዲገፉ ይረዳዋል ማለትም በመጀመሪያ ከአርነት ዕንቅ
ቃሴዎች ጋር ከተባበሩት የካፒታሊስት ክፍሎችና ኋላም
ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በማበር በሕዝብ ላይ በጠላትነት
በቆሙት አጠቃላይ ገጠመኞች ይበልጥ የተፋጠነውን
ሂደት ማለት ነው ።

የቻይና ሁኔታ ይህንን ግልፅ ለማድረግ ሊወሰድ
ይችላል ። በ፲፱፻፲፩ ዓ. ም. የቡርገርዋው አብዮት በውጭ
ኢምፔሪያሊስቶች በሚደገፈው የመልከኞች ገዥነት
አንጻር በመቆም ወሳኝ ደረጃ ላይ ደረሰ ። በ፲፱፻፳ ምቹ
በኢንዱስትሪ ከተሞችና ወደቦች ውስጥ የሚገኘው የሠ
ራተኛ መደብ በጥንካሬና በድርጅት በሚአስደንቅ ሁኔታ
አደገ ። ስለሆነም በ፲፱፻፳፩ ዓ. ም. የኮሚኒስት ፓርቲው
ተመሠረተ ። በዚህ ዘመን ውስጥ በሙሉ ለብሔር አርነቱ
እንቅስቃሴ ዋና ኃይል የነበረው ፡ በ፲፱፻፲፱ ዓ. ም. በሱ
ንያትሰን የተመሠረተው የኮሚንታንግ ፓርቲ ነው ። ግን
ለውጭ የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች የራስ ምታት እየሆነ
ባቸው የሄደው አድማውንና ሰላማዊ ሠልፎችን በኢንዱ
ዱስትሪያዊ ማዕከሎች በ፲፱፻፳፬ ፤ በ፲፱፻፳፭ እና በ፲፱፻፳፮
የመራው የሠራተኛው መደብ ነው ። ከ፲፱፻፳፭ ዓ. ም.

የሱንያትስን ሞት በኋላ የኮሚንታንግ ሠራዊቶች በሠ
ራተኛው መደብና በኮሚኒስት ፓርቲው ሙሉ ድጋፍ ቻይ
ናን አንድ ለማድረግና ሶሻል ጥገናዎችን ለማካሄድ በሚል
ዓላማ ከካንቶን ወደ ሰሜን ዘመቱ ። ይሁንና በሚያዝያ
፲፱፻፳፯ ዓ ም ቻንጋይ ሼክ — የኮሚንታንግ ሠራዊት ወታ
ደራዊ መሪ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር ተስማማና በኮሚኒ
ስት ፓርቲውና በሠራተኛው መደብ ላይ እጁን አነዘረ ።
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴው
የተመራው በኮሚንታንግ ሳይሆን በኮሚኒስት ፓርቲው
ነው ። ይሁንና ኋላ ከጃፓን ወራሪዎች ጋር ባለው ትግል
አንድ የተወሰነ ደረጃ ላይ እንደገና የጋራ ብሔራዊ ግንባር
ተመሥርቶ ነበር ።

የሠራተኛው መደብ ከሌሎች የሕዝብ ክፍሎች ጋር
ከዋናው ጠላት አንጻር በመቆም የሚፈጥሩት የኪዳን ንድፈ
ሀሳብ የሚገኝ በካፒታሊስት ፣ በቅኝ ግዛት ወይም ግማሺ
ቅኝ ግዛት አገሮች ውስጥ በሚካሄደው ትግል የዕለት
ተዕለት ገጠመኝ ነው ። እርግጥ ማርክሳዊ ንድፈ ሀሣብ
የገጠመኝ ማጠቃለያ ነው ፤ እናም እንደሌሎች ሳይ
ንሣዊ ንድፈ ሀሣቦች ሁሉ መጠቅ ባለ ገጠመኝ ይዳብ
ራል ወይም ይሻሻላል ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት
ጊዜና በተለይም ከአለቀ በኋላ ፣ በብዙ አገሮች አዳዲስ
ወደ ፍፁም አዲስ የሕብረት ንድፈ ሀሣብ ዓይነተኛ ዕድ
ገቶችና ሶሻሊዝምን ለማስገኘት ወደሚአስችሉ የሠራተ
ኛው መደብ ስትራቴጂዎች የሚመሩ ገጠመኞች ታይተ
ዋል ።

በጦርነቱ ጊዜ በናዚ ጀርመን ኢምፔሪያሊስቶች
ተይዘው በነበሩ የአውሮጳ አገሮች ጥንካሬውን በሠራተ
ኛው መደብ አድርጎ በኮሚኒስት ፓርቲው የሚመራ ፣ ግን



ለሀገራቸው ከሃዲዎች ወይም ከጠላት ባለሥልጣኖች
ያልነበሩትንም በመጨመር ብሔራዊ የመቋቋም እንቅስ
ቃሴዎች ታዩ ። ከነኝህ ከሃዲዎ ችዋናዎቹ ከናዚ ወራሪዎች
(Quislings) ጋር ተጣምተው ተስማምተው የነበሩት ትላልቅ
የመሬት ከበርቴዎችና ካፒታሊስቶች ነበሩ ። ለምን ? ትር
ፋቸውንና ጥቅማቸውን ለማቆየት ። በሌላ በኩል የካፒታሊ
ስቱን ብዙውን ክፍል የያዙት አነስተኛ ከበርቴዎችና አብ
ዛኛው የመካከለኛው መደብ ክፍል ከሠራተኛውና ከገበ
ሬው መደብ በመዋሀድ አገራቸውን ነጻ ለማውጣት በና
ዚ ወረራ አንጻር ቆሙ ።

የናዚዎች በወታደራዊ ኃይል ድል መሆንና የተወ
ረሩት አገሮች ነጻ መውጣት በእያንዳንዱ ሀገር ይህ ብሔ
ራዊ አንድነት (ሕብረት) በውስጡ የኮሚኒስት ፓርቲዎች
ኮሚኒስትና ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች በሚአስደንቅ
ሁኔታ ጥንካሬ የአገኙበት ጊዜአዊ መንግሥት መሠረት
ሆነ ። ሕዝባዊ ኮሚቴዎች በብሔራዊ አንድነቱ መሠረት
ተቋቋሙ ፤ ግን ወደሠሬው ሠራተኛ ሕዝብ በጣም የቀረ
ቡና እንዲሁም የሠራተኛ መደብን ተዕዕኖ ያጠነከሩ ከመ
ሆናቸው በላይ የቀድሞዎችን ትላልቅ የመሬት ከበርቴ
ዎችና ካፒታሊስቶች የሀገር ውስጥ ተፅእኖ ስብርብሩን
አውጥተውታል ። የመንግሥታቱ ዕቅድ በእነዚህ ጸባዮች
ምክንያት ተራማጆች ነበሩ ፣ በምሥራቅ አውሮጳ ትላ
ልቅ ኩዳዶችን ( Estates ) በመውሰድና ለገበሬዎች
በማከፋፈል ፣ ባለፈው ጊዜ ሀገራቸው መልከኛ ወይም
የፋሺስት አምባገነንነት ሥር በነበሩት በብሔራዊና በገዛቅ
ተኛ ደረጃ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን በመመሥረት
ተግባር ላይ ውለዋል ። ይህ ነበር በምሥራቅ አውሮፓ አገ
ሮች የመጀመሪያው ደረጃ « ሕዝባዊ ዲሞክራሲ ። » . . .

የእነዚህ አገሮች የኮሙኒስት ፓርቲዎች ይህ አዲስ
ዓይነት አገዛዝና መንግሥት ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም
የሚካሄደውን ለውጥ ለመሸከም ወደሚችል መሣሪያነት
እንደሚአገለግል አይተው ነበር ። በሌላ በኩል ፦— የካፒ
ታሊስቱና የገበሬው ፓርቲ መሪዎች ፣ እንዲሁም አንዳ
ንድ የሶሻል ዲሞክራቲክ መሪዎች የመሠረታዊ የሕብ
ረተሰብ ለውጥ ውዴታ አልነበራቸውም ፤ እናም በሕ
ዝባዊ ግፊት ምክንያት እንዲቀበሉ የተደረገትን የመን
ግሥቱን የአጭር ጊዜ ፕሮግራም የለውጡ ማቆሚያ
እንደሆነ ቆጠሩት ። በሌላ መንገድ ፣ በገጠርና በከ
ተማ ያለው ሠራተኛ ሕዝብ በአርጌው ገዥ መደብና በፋ
ሺዝም ላይ ድል በመጐናጸፉ ልበ ሙሉ የሆነውና ለመ
ጀመሪያ ጊዜም ሙሉ የፖለቲካ መብት የተሰጠው ፣ በኮ
ሚኒስት ፓርቲው ለከፍተኛ ዕድገት የተወሰደውን እር
ምጃ ሙሉ በሙሉ ደገፈው ። ይህ የሶሻል ዲሞክራቶችን
ወደ ኮሙዩኒስት ፓርቲዎች መዋሃድ ፈጥሮ በማርክሲዝም
መሠረት የሠራተኛውን መደብ አንድ ፓርቲ እንዲመጣ
አደረገ ።

በሠፊው ሕዝብ ድጋፍ በተከታታይ በተወሰደው
ፓርላማዊ ውሳኔ ንግድና ኢንዱስትሪ በመንግሥት ተወር
ሰው ዕቅዳዊ ምጣኔ ሀብት አደገ ። ተራው ወደ ጋርዮሻዊ
እርሻ ሆነ ። በጦር ኃይሎች ፣ በሲቪል አገልግሎቶች ፣
በተወረሱ ኢንዱስትሪዎችና ንግዶች ፣ ቁልፍ ቦታዎች
የካፒታሊዝምን አቀንቃኞች በመተካት በሶሻሊዝም ጠበ
ቆች ተሞሉ ።

ይህ በሕዝባዊ ዲሞክራሲ አማካይነት ወደ ሶሻሊ
ዝም መሸጋገር የተቻለውና ርዳታ የተካሄደው ሙሉ በ
ሙሉ በሶቪየት ሶሻሊስት ሕብረት ነው ። የናዚ ወታደሮች



በሶቪየትና በብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ ሠራዊቶች ከተ
መቱ በኋላ በእያንዳንዱ ሀገር የተቋቋመው ጊዜአዊ መን
ግሥት በስምምነት የወጣውን ፕሮግራም ፣ ሶቪዬት ሕብ
ረት በመጀመሪያ ጊዜ ገጥሟት እንደነበር የኢምፔሪያሊ
ስት ጣልቃ ገብነት ሳይገጥማቸው ማካሄድና ማራመድ
ችለው ነበር ። ብቻን ተገንጥሎ ጭቆና በበዛበት ዓለም ሶሻሊ
ዝምን ለመገንባት ከመሞከር ይልቅ — ሶቪዬት ሕብረት
ገጥሟት እንደነበረው ሳይሆን — ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዎች
ከወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ተጠበቀው ፣ የምግብ ዕርዳታ
አግኝተው ፣ በሶቪየት ሕብረት ማቴሪያሎችና ሚሽኖች
ተሰጥተዋቸው ፣ ከዚህም በላይ በምጣኔ ሀብት ፤ በፖለቲካ
ዊና በሶሻል ችግሮች ሶሻሊስታዊ መፍትሔ በመስጠት
በሶቪየት ሕብረት ከደለበው ገጠመኝ በሠፊው ዕርዳታ
በመውሰድ ማካሄድ ተችሏል ። በሶቪዬት ሕብረት ላይም
ጥገኛ መሆን ጉጂ ጐን አለው ፤ ከዚህ በፊት የተደረገውን
በመመልከት ብቻ የሚፈጸም የሶሻሊስት መርሆዎች ማው
ገርገር (Distortions) ና በእያንዳንዱ ሀገር ያለውን ሁኔታ
በቂ ግንዛቤ ሳይሰጡ የሶቪየትን ዘዴዎች የመገልበጥ
ዝንባሌ ሊመጣ ይችላል ። ግን በነዚህ አገሮች የተ
ጣለውን የሶሻሊዝም መሠረት (ለሶቪዬት ዕርዳታ ምስ
ጋና ይግባውና) እውነት መልኩን ሊለውጠው አይችልም።

ከሕዝባዊ ዲሞክራሲዎች ጋር ተመሳሳይነት ያለው
በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የጃፓኖች በቻይና ድል መሆን
በኋላ የተፈጸመው ድርጊት ነው ። በሻንጋይ ሼክ እና በሰ
ሜን ምዕራብ ተቋቁሞ በነበረው የኮሚኒስት አስተዳደር
መካከል ያለው የመሣሪያ ትግል ጃፓኖችን ለመቋቋም
በተደረገው የኮሚኒስቶች ብሔራዊ የሕብረት ጥሪ ይነሰም
ይብዛም ቆሞ ነበር ። ግን ጦርነቱ አልቆ ፣ ለቻይና የተባ
በረ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማምጣት በተደረገው

የኮሚኒስት ፓርቲው ጥረት በከፍተኛ ወታደራዊና የገን
የኮሚኒስት ፓርቲው ጥረት በከፍተኛ ወታደራዊና የገን
ዘብ ምንጮች በዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት በሚረዳው
ሻይንጋይ ሼክ የወታደራዊ መቋቋም ኃይል ገጥሞት
ነበር ። በ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. ሻንጋይ ሼክ ድል ሆኖና
ከፍተኛ ጥፋት ደርሶበት ወደ ታይዋን (ፎርሞሳ) ከኰሬ ፤
ኮሚኒስት ፓርቲውም አዲስ መንግሥት ለማቋቋም «የሕዝብ
አማካሪ ቆንሲል» ጠራ (People's Consultative Council) ።
የቻይናው ሕዝባዊ ሬፑብሊክ ተመሠረተ ። መንግሥቱ በሠ
ራተኛው መደብ ፡ በገበሬው ፡ በከተማው ንዑስ ከበርቴና
በብሔራዊ (አርበኛው ማለት ነው) ካፒታሊስት ላይ ተመ
ሥርቶ በቢሮክራሳዊ ወይም በሞኖ ፖሊ ካፒታሊ
ስቱ ቡድን ኪታንግይካይ — ሼክ ከተዘመደው አንጻር
ቆመ ። ስለዚህ ሕዝቡ በጥቂት ከሃዲዎች አንጻር በመቆ
ም ተባበረ ። ከሃዲዎች በሕዝቡ ኪሣራ ሊአካብቱና ሊበለ
ጽጉ የሚፈልጉትና ለዩይናትድ ስቴትስ ኢምፔሪያሊስ
ቶች የወጥ—እንጨት የሆኑት ናቸው ። የመሬት ከበርቴ
ዎች መሬት ለገበሬዎች ተከፋፈለ ፤ ኢንዱስትሪና ንግድ
በመንግሥቱ ቁጥጥር ግን በተለይ በግል ንብረትነት ሥር
በመሆን ተጠናከሩ ፤ ዲሞክራሲያዊ ተቋሞች በከተማና
በገጠር ተቋቋሙ ። በዲሞክራሲያዊትና በተባበረችው
ቻይና ውስጥ ሕዝባዊ ሬፑብሊክ በደንብ ተመሠረተ ፤
እንዲሁም የአገሪቱ ምጣኔ — ሀብት ሽግግር — ወደሶሻ
ሊዝም ለማደግ ለሚደረገው መሠረት — በኮሚኒስት ፓር
ቲው እየተመራ በመንግሥቱ የብሔራዊ አንድነት ሠፊ
መሠረት ሥር ተጀመረ ።

እነዚህ ገጠመኞች በምሥራቅ አውሮጳና በቻይና
ወደሶሻሊዝም የሚደረገውን የዕድገት ትግል መፍትሔ
የሚሰጡ አዲስ ሁኔታዎችን አሳዩ ። በካፒታሊዝም ጠቅ
ላላ ቀውስ ውስጥ የሞኖፖሊ ቡድኖች በሕዝቡ ላይ ያላቸ



ውን ዝር ፉያ ለመጠገን በሚአደርጉት ጥረት በየጊዜው
ቀን ተቀን ተስፋ ወደሚአስቆርጥ ርምጃ ተነዱ ። ፋዝሺዝም፤
ጦርነትና የሠራተኛውን ሕዝብ ሁኔታዎ ችግሬን — ይህ
ነው የስዕሉ አንድ ገጽ ። ሌላው ገጽ በዓለም የሶሻሊስት ክበብ
ማደግ ፤ እያደገ የሚሄደው የሠራተኛውና የቅኝ ግዛት ሕዝ
ቦችን መቋቋም ኃይል ፤ እናም ከማዕከላዊ አመለካከታ
ቸው ጋር የኮሚኒስት ፓርቲዎች ችሎታ—ማለትም የሠ
ራተኛውን መደብ ብቻ ሳይሆን የሰፊውን ሕዝብ ትግልም
በሞኖፖሊዎች አንጻር ለማቆም ብቃት ማግኘት — ነው ።
በሁሉም በከበርቴና በቅኝ ግዛት አገሮች ውስጥ ሞኖፖሊ
ዎች ራሳቸውን ብቸኛ አድርገው ያዩታል ፤ ግን የሕዝቦች
ኪዳን በእነሱ አንጻር ሰላምን ለማምጣት ለብሔራዊ አር
ነት ፤ ለዲሞክራሲና ለተሻለ ኑሮ ለሚደረገው ጦርነት
ዕድገቱ ሰፊና ጠንክሮ ይታያል ።

በሞኖፖሊዎች ላይ ድልን ለመቀዳጀት የሚጠይቀው
የመጀመሪያ ሁኔታ በሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ ውስጥ
ያለውን አድርባይነት ድል ማድረግ ነው ። በማርክሲዝም
ውስጥ ያሉት የታሪክና የሠራተኛው መደብ ገጠምኞች
እንደሚአሳዩን ወደ አዲስ የሰብአዊ ሕብረተሰብ ደረጃ
የሚአመራው መንገድ የሚንተራሰው በመደብ ትግል
እንጂ ልብሱ ካለቀ ሕብረተሰብ (አሮጌ) ገዥዎች ጋር ኪ
ዳን በመፍጠር አይደለም ። በሃገርም ውስጥ ይሁን ወይም
በውጭ የሁለትነት ( Bi-Partisan ) ፖሊሲ የለም ፤
ግን የሠራተኛውን መደብ ፖሊሲ መደገፍ ብቻና በሞኖ
ፖሊዎች የወጣውን ፖሊሲ ለመቋቋም ንቁ ተሳትፎ
ማካሄድ የሠራተኛውን መደብ ምንም ኃይል የማይቋቋ
መው ጥንካሬና ቆራጥነት በታሪካዊ ተልዕኮው ውስጥ
እንዲኖረው ያደርገዋል ።

በማርክስና በሌኒን ካለፈው ገጠመኝ የተገኙት መሠረታዊ ትምህርቶች ጠቃሚነታቸው ፣ ቀዋሚነታቸው ተረጋግጧል ። ከፍተኛ የሕብረተሰብ ዕድገት ሊገኝ የሚችለው ከካፒታሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ጋር ትግል በማካሄድ ብቻ ነው ። ሊገነባ የሚችለው ከውስጥ ካሉ የአሮጌው የገዥ መደብርዝራሮች ከውጭ ኢምፔሪያሊስቶች ጋር የማያቋርጥ ትግል በማንሳት ብቻ ነው ። የሕብረተሰብ ሽግግር ሊረጋገጥ የሚችለው የፖለቲካ ሥልጣንን በማሸነፍ ነው ። ይህ ደግሞ የሠራተኛን ሕዝብ ኪዳን መኖርንና በሠራተኛው መደብ ግምባር ቀደምትነት መመራትን ፤ በዚህም ላይ ከራሱ ከመደብ ትግል በማርክሲዝም የተገኙትን ትምህርቶች የራሱ በአደረገ አብዮታዊ ፓርቲ የሚመራ መሆኑን ይጠይቃል ።

ወደሶሻሊዝም የሚአመራው መንገድ እንዲህ ቀላል አይደለም ። ግን በአሁኑ ወቅት ችግሮችን ለመወጣት እንደበፊቱ ከባድ አይደሉም ፤ ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ በጥቅምቱ ፲፱፻፲፯ ዓ. ም. የሩሲያ አብዮት ሁኔታና ኋላም በዓለም ውስጥ ጥልቀት ያላቸው ለውጦች በመምጣታቸው ነው ። አንድ ሺህ ሚሊዮን ሕዝቦች ከሰው ዘር ፩/፫ኛው በላይ — የመልከኛውንና የመጀመሪያውን ካፒታሊዝም ሰባብረው ማርክስና ኤንግልስ በኮሚዩኒስት ማኒፌስቶ « የእያንዳንዱ ነጻ ዕድገት ለሁሉም ነጻ ዕድገት ምክንያት ነው » ብለው ባስቀመጡት መርሆ መሠረት አዲስ ሕይወት እየገነቡ ናቸው ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተገኙት ገጠመኞች ሁሉ በሞስኮ ጥቅምት ፲፱፻፷ ዓ ም በተካሄደው የኮሚኒስትና ሠራተኞች ፓርቲዎች ስብሰባ ላይ በተሰጠው ሀተታ ተጠቃለዋል ። « የእነዚህ ዓመታት ዋናው ውጤት የዓለም ሶሻ



ሊስት ሥርዓት ኃያልነትና ዓለም አቀፋዊ ተፅዕኖ ፈጣን ዕድገት ማሳየቱ ፣ በብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ ኃይል ሂደት ማግኘት ምክንያት የቅኝ ግዛት ሥርዓት መበታተን ፤ በካፒታሊስት ዓለም የመደብ ትግሎች መጠናከርና የተከታተለ የዓለም ካፒታሊስት ሥርዓት መበስበስና ማሽቆልቆል ነው ። »

ሀተታው እንዲህ ይላል ፡— የዘመናችን ዋናው ይዘት ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም መሸጋገር ነው ፤ ይህንና ይህ ትዕበታዊ ሂደት አይደለም ፤ በሁለት ተቃራኒ ሥርዓት—ማኅበሮች መካከል ትግል የሚካሄድበት ጊዜ ነው ፤ የኢምፔሪያሊዝም መሰባበርና የቅኝ ግዛት ሥርዓት መወገድ ፤ የብዙ ሕዝብ ወደሶሻሊዝም መንገድ መሸጋገር የሶሻሊዝምና የኮሚኒዝም በዓለም ደረጃ መንሰራፋት ነው ።

በዚህ ዘመን የሕብረተሰብ ዕድገት ዋናዎቹ ጸባዮችና አቅጣጫዎች የሚወሰኑት በኢምፔሪያሊዝም አይደለም ፤ ይልቅዬስ በዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት ኢምፔሪያሊዝምን በሚዋጉት ኃይሎች ነው ። የነዚህ ኃይሎች የተባበረ ጥንካሬ ኢምፔሪያሊስቶች ሌላ አዲስ የዓለም ጦርነት እንዳይከፍቱ ያግዳቸዋል ። በእነዚህ ሁኔታዎች ምክንያት በየሃገሩ ያሉት ኮሚኒስቶች ዓለም ብዝበዛንና ድኅነትን ከዓለም ገፅ ማጥፋትና ስለዚህም የጦርነት ምክንያቶችን እንዲአከትሙ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በአሁኑ ጊዜ አዲስ የዓለም ጦርነት ይመጣል ከሚለው ፍርሃት የሰው ልጆችን ነጻ ማውጣትም ነው ።

በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሠራተኛውን መደብና የሕዝቡን ሰፊ ክፍል ሕብረት ለመፍጠር የሚአስችል

አመች ሁኔታዎች ተፈጥረዋል ፤ ስለዚህም ለሰላም ፤ ለዲሞ
ራሲና ለሕዝቦች ዋና ፍላጐቶች ሲባል ከሞኖፖሊዎች
ጋር የተጠናከረ ጦርነት ማካሄድ ይቻላል ። እናም የሠራ
ተኛው መደብ በብዙ የካፒታሊስት አገሮች የመንግሥት
ሥልጣን አሸንፎ የመያዝ ዕድል እንዳለፈው የሶሻሊስት
አብዮት ያለ ሕዝባዊ ጦርነት ማካሄድ እንደሚችል ተገን
ዝቧል ፤ ይሁንና ኃይልን የመጠቀም ሁኔታ ከበዝባዡ መ
ደብ በኩል ሊመጣ ይችላል ።

በመጨረሻ ሐተታው በ፹፯ አገሮች የፈለቁ ኮሚኒ
ስት ፓርቲዎች እንዳሉና በጠቅላላም ፴፮ ሚሊዮን አባላት
እንዳሏቸው መዝግቦ ፤ ለጠቅላላው የሰው ልጅ የወደፊት
ዕድገት ትግሎች አዲስ ድሎች ዋስትና እንዲሆን በማርክ
ስና በኤንግልስ ትምህርቶች ላይ የተመሠረተ የኮሚኒስት
ሕብረት ፍላጐት ዓይነተኛነትን ያስገነዝባል ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የኢምፔሪያሊ
ስት ኃይሎች ይህንን ሂደት ለማገድ በኃይል የመጠቀም
ተስፋ አላቸው ፤ እናም ምናልባት የሶሻሊስት አገሮችን
እንኳን ለመሰባበር ይጥራሉ ፡ የሰሜን አትላንቲክ የስም
ምነት ድርጅት ( N.A.T.O. )እና በዩናይትድ ስቴትስና
በምዕራብ አውሮጳ ካፒታሊስት አገሮች እንዲሁም በም
ዕራብ ጀርመን የሚካሄደው የእንደገና ትጥቅ ባሕሪው
ይህ ነው ፤ ሌላ አይደለም ፡ በደቡብ ምሥራቅ እስያ የስ
ምምነት ድርጅት ( S.E.A.T.O. ) በሩቅ ምሥራቅ የኢ
ምፔሪያሊስቶች ኪዳን መስፋፋት ባሕርይ ነው ፤ ሌላም
አይደል ፡ የእንግሊዝም በባግዳዱ ስምምነት መሠረት
ተመሳሳይ የሆነ የመካከለኛው ምሥራቅ ግንባር የመ
ፍጠር ሙከራ ሌላ ምክንያት የለውም ። በዩናይትድ ስቴት
ጠብ አጫሪ ኢምፔሪያሊስቶች የኮሪያን ጦርነት በቻይና



ላይ ወደተስፋፋ ጦርነት ለማስመሰል የአደረጉት ሙከራ
ይኸው ፀባይ ነው ያለው ። በኮንጎ የነበረው የዩናይትድ
ስቴትስ ጣልቃ ገብነትና ግብ የመታውን የኪዩባን አብ
ዮት የማስፈራራት ሙከራና በመላው ላቲን አሜሪካ ውስጥ
በብሔራዊ አርነትና ተራማጅ ንቅናቄዎች የተዘዋዋሪ ጥ
ቃት ፤ ከዚህም በላይ በቬትናም ሕዝብ ላይ ሙሉ በሙሉ
የወሰደቻቸው የወረራ ድርጊቶች ሁሉ ሌላም መልክ የላ
ቸው ፤ የሕብረተሰብን ዕድገት ለመቀጨት ለማገድ ካል
ሆነ በቀር ። ከእነኝህ የዓለም አቀፍ ካፒታሊስቶች ማዕ
በሉን ለማገድ ከሚአደርጉት ጥረት ጋር ፤ እንግሊዝ በማ
ላያ ፤ በኬንያ ፤ በብሪቲሽ ጉያና ፤ በቆጵሮስና ግብጽ ላይ
ኃይል ተጠቅማለች ። ሆላንድ አልሆነላትም እንጂ የነጻ
ነት እንቅስቃሴዎችን ለማገድ በኢንዶኔዥያ ስትሞክር ፤ ፈረ
ንሳይ በቬየናትም ድል ሆነች ፤ የሞሮኮንና የቱኒዚያን እንቅ
ስቃሴዎች ለማገድ ፍሬ የሌለው ሙከራ አካሄደ ፤ በአልጀ
ሪያ ደግሞ ለረጅም ጊዜ በቆዬ ትግል ውስጥ ተነከረች ።

ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ምንም ጊዜ ቢሆን ወደጦር
ነት የሚዳፋና ጊዜው ያለፈበት እንደሆነ የሚገልጸውን
የማርክሳዊ ቴሲስ(አበክሮ ጽሑፍ) ( Thesis ) ለማሳየት
እነዚህን እውነቶች ደጋግሞ ማጤን አስፈላጊ ነው ። የማ
ርክሲዝም መደባዊ አቀራረብ ሠራተኛውን መደብ የጦር
ነት ውስጥ ፕሮፓጋንዳን ፤ ወደጦርነት የሚመሩትን ኃይ
ሎችና ለሰላም የሚዋጉትን ኃይሎች በግልጽ እንዲአይ
ያስችለዋል ። በአንድ በኩል የኢምፔሪያሊስት ቡድኖች
በተለይም ዩናይትድ ስቴትስ ለመስፋፋት የዓለምን የሶ
ሻሊስት ክበብ ለካፒታሊዝም አሸንፎ ለመውሰድ ይጣ
ጣራሉ ። በሌላ በኩል የሶሻሊስት መንግሥታት ነጻነታ
ቸውን ካገኙት የቅኝ ግዛት ሕዝቦችና ነጻነታቸውን ለማ
ግኘት በመታገልም ላይ ካሉት ፤ በተጨማሪም በካፒታ

ሊዝም ውስጥ ካለው ሰፊ ሕዝብ (ዩናይትድ ስቴትስን ጨ
ምሮ) በጦርነት ዝግጅት ምክንያት በጦርነት ፤ በምጣኔ—
ሀብትና በፖለቲካ የሚሰቃዩት — እርምጃቸው በሰላም
ላይ የተመሰረተ ነው ፤ ለሰላምም ይዋጋሉ ።

ኢምፔሪያሊዝም ወደጦርነት ነው የሚዳፋው ስንል ፡
ጦርነት የማይቀር ነው ማለት ነው ? ያለፈው ገጠመኝ
ይህን መደመደሚያ ይጠቁም ይመስለናል ። ግን ይህንን
ለወደፊቱ መሆን አለበት ብለን ካሰብን « ቀኖናዊ » ማር
ክሲዝም ይሆናል ፤ ማለትም በማርክሳዊ አቀራረብ ዋናው
ነጥብ ሆኖ የተወሰደውን የሁኔታዎችን መለዋወጥ አለመ
ገንዘብ ፡ አለማጤን ነው ። ዛሬ ነገሮች (ሁኔዎች) ተለው
ጠዋል ። የጦርነት ዝንባሌ አሁንም አለ ፤ እናም ለዚህ ማረ
ጋገጫው የኢምፔሪያሊስቶች ጥላቻ በሶሻሊስት አገሮች
ላይ መኖሩን በራሳቸው በካፒታሊስት አገሮች መካከል
የፍላጐት ግጭት መፈጠሩ ፡- እንዲሁም የቅኝ በነበሩ ግዛ
ቶች ጦርነቶች ሁሉ ናቸው ። ግን አዲሶች ምክንያቶች
ባጭሩ የታተቱት ናቸው ፤ የኒውክሌር መሣሪያዎች ያሏቸው
ኃያል የሶሻሊስት ክበቦች መኖር ዕውቅ ነው። ስለዚህም «ጦ
ርነት ይነሣ » ማለት እንድላይ መጥፋት ነው ፤ በዚህም ላይ
ዓለም አቀፋዊ የቅኝ ግዛቶች የነጻነት እንቅ ስቃሴ አለ ።
ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ በግብፅ እንደታየው ሁሉ ኢምፔሪ
ያሊዝም አንድን አገር ነጥሎ ለመምታት በጣም አደጋች
ይሆንበታል ፤ በተጨማሪም በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ
እንኳን ጦርነትን የመቃወም ሁኔታ በሠራተኛው መደብ
እንቅስቃሴና በአጠቃላይ በሕዝቡ መካከል ጥንካሬ እያገኘ
ነው ። እነዚህ ምክንያቶች በአሁኑ ወቅት ጦርነት ሊቀር
የማይችል ነው የሚለውን ፉርሽ ያደርጉታል ። ግን በሕ
ዝቦች ንቃታዊ ክንዋኔ ጦርነቱ ሊገታ ይችላል ። ይህም የሚ
ሆነው በሶሻሊስት አገሮች የሰላም ፖሊሲና ነጻ በወጡ



የቅኝ ግዛት አገሮች ነው ። ብሎም በሰላም አብሮ መኖር
ይቻላል ። ( Peaceful Co.-Exisanee ) እንዴት ? ሁሉም
የእያንዳንዱን ሃገር የማይገሰስ ክብር ( Sovereignty ) በማ
ክበር ፡ ከወረራና ከጣልቃ ገብነት በመወገድ ፡ በማንኛ
ውም ግንኙነት እኩልነትና እኩል ጥቅምን በመጠመብቅ፤
እና ምጣኔ — ሀብታዊ ሕብረት ላይ በመመሥረት ፤ነው።

በመላው ዓለም የመደብ ኃይሎች ዝምድና ውስጥ
ያሉት የጥልቀት ለውጦችም በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ
ያሉትን ወደሶሻሊዝም የመሸጋገሪያ ችግሮች ተፅዕኖ ያሳ
ድሩባቸዋል ።

ማርክስ በእርሱ ጊዜ በነበረው ሁኔታ ካፒታሊስት
ገዥ ዎችን ለማስወገድና ወደሶሻሊዝም የሚአስኬደውን
ውጣውረድ ለመሸከም የሠራተኛውን መደብ ኃይል ለማቋ
ቋም አማራጭ መንገድ ኃይል ባለው (በመሣሪያ) አብዮት
ብቻ መጠቀም ነው ብሎ ነበር ። ማርክስ በዚያ ጊዜም
እንኳን እንግሊዝና ዩናይትድ ስቴትስን እግሊሎ እን
ደነበረ እውነት ነው ፡ ግን በእነዚህ አገሮች የወታደራዊ
ቢሮክራሲያዊ መንግሥት መሽከርከሪት ያልዳበረ መሆ
ኑን መሠረት በማድረግ ነው ። በኋላም ፡ በአንደኛው የዓ
ለም ጦርነት ሉኒን እንደጠቆመው በተግባር እንደማይውል
ታይቷል ። ከገጠመኞች እንደ ምንረዳው ማርክስ ያሳሰብ
የነበረው «በኃይል የመጠቀም አብዮት» የተረጋገጠው በፍ
ጹም ዲሞክራሲያዊ ለውጥ የሚፈጠርበት መንገድ በሌ
ለው — ምክንያቱም ዲሞክራሲያዊ ተቋሞች አልነበ
ሩምና — በሩሲያ ነው ። በቻይናም ተመሳሳይ ሁኔታ ነበር ፡
ይሁንና አብዮቱ የአደገበት መንገድ ልዩ ነው ።

ዛሬ የሶሻሊስት ዓለም ክበብ እየጠነከረ መሄድና
በቅኝ ግዛት የነጻነት ንቅናቄ ምክንያት አሁንም በመኖር

ላይ ያለው የካፒታሊስት ሥርዓት መዳከም በአንድነት
እያደገ በሚሄደው የሠራተኛው መደብና የካፒታሊስት
አገሮች ውስጥ የተራማጅ እንቅስቃሴዎች ጥንካሬ አስተ
ዋፅዎ ያደርጋሉ ። በተለይም በዩናይትድ ስቴትስ — ሁል
ጊዜም ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የመገደብ ዝንባሌ ቢኖ
ርም — ሠራተኛው መደብና ተራማጅ ንቅናቄዎች የዲሞ
ክራሲን ማንኛውንም ገፅ ለመጠበቅ በየጊዜው ቆራጥ
ነታቸውን አሳይተዋል ። ከዚህም በላይ ፡ ሞኖፖሊ ካፒ
ታሊዝም ታይቶ የማይታወቅ ትርፍ ለማግኘት በሙያ
የሠለጠኑ ሰዎችና የአነስተኛ ድርጅቶችን ባለቤቶች
ኑሮ ቢረግጥና ቢይዙም ፡ አድሃሪ ፖሊሲን ለመቋቋም
ይበልጥ እየተስፋፉና ለተራማጅ ዓላማዎች ሠፊ ሕብረት
የሚአስገኘው በር እፉ እየሰፉ ይሄዳል ። ስለዚህም ፡ በተለ
ይም ረጅም ጊዜ የቆዩትና የዳበሩ ዲሞክራሲያዊ ተቋሞች
እንዲሁም ጠንካራ ዲሞክራሲያዊ ልምዶች ባሉበት ሀገር ፡
ሠራተኛው መደብ ከተባበረና ከሌሎች ተራማጅ
የሕዝብ ክፍሎች ድጋፍ ካለው — ካካፒታሊስቶች ሥል
ጣን ነጥቆ ሶሻሊዝምን መገንባት ይችላል ። ዋናው ባሕሪ
ሥልጣን መንጠቁነው ፡ ቅርጹ ወይም አውሳሰዱ በኃ
ይል ወይም በሰላም መሆኑ የሚንተራሰው በመደቦች የዘም
ድና ጥንካሬና ካፒታሊስቶቹ ራሳቸው የታሪክን ጉማ
ወደ ኋላ ለማሽከርከር በጥረቱ ላይ የሚአደርጉት የኃይል
መቋቋም ላይ ነው ።

ስለዚህ ማርክሳዊ ንድፈ — ሀሳብ ሁኔታዎች ሲለ
ወጡ በአዲስ መንገድ በተግባር ይውላል ፤ ሠራተኛው
ንም መደብ ባለው የዛሬው ዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ላይ
ሊፈጽም ወደሚአስችለው ክንዋኔ ይመራዋል ፤ ሶሻሊስት
ሕብረተሰብን በጣም በቀላሉና በአፋጣኝ ወደ ሕልውና
ለማምጣት ያስችለዋል ።



የሩሲያ ሠራተኞች ሥልጣን ያገኙበት ታሪካዊ ደረ
ጃና እነዚሁ ሠራተኞች መወጣት ያለባቸው በኢንዱስትሪ
በፖለቲካና በሶሻል በዘመኑ ዛር ወደ ኋላ መቅረት ተግባ
ራቸውን ሊታመን በማይችል ችግር ውስጥ ጥሎት ነበር ።
ይበልጥ ችግር እንዲፈጠር የተደረገው በውጭ ጣልቃ
ገብነት ነው ፤ ገና በጨቅላነት ደረጃ በአሥራ አራት አገ
ሮች መንግሥታዊ የመሣሪያ ጥቃት ፤ ከ፲፱፻፴፫—፲፱፻፴፯
በሂትለራዊ ወራሪ አደገኛ ጥፋት ማድረስ የመሳሰሉት በዚህ
ዓይነት ሁኔታ አዲሱን ሕብረተሰብ ለመገንባትና
ለመጠበቅ ሲባል ግዴታና ኃይል ዋና ሚና መጫወታ
ቸው የማይቀር ነገር ነው ፤ ስለዚህ ሕዝቡ የረጅም ጊዜ
ከባድ መሥዋዕትነት ኑሮ ማሳለፍ ነበረበት ፡ አሳልፏ
ልም ። ግን በነዚህ ችግሮች ምክንያት ፡ እና በስ
ታሊን የኋለኛው ዘመን የኑሮ መተረፍረፍ ፡ የሩ
ሲያ ሠራተኞች በሃገራቸው ሶሻሊዝምን ገን ብተዋል ፡
ድሎቻቸውም በዓለም ውስጥ የተካሄዱትን ሰፊ አብዮታዊ
ለውጦች አነሳስተዋል ፡ ገፋፍተዋል ።

ወደ ሶሻሊዝም ለመገስገስ እንደገና በዚያ ዓይነት
ገጠመኝ የሚጠቀም ምንም አገር አይኖርም ። የዓለም
ሶሻሊስት ክበብ ከፍተኛ ጥንካሬ ማግኘት ስለሌሎች አገ
ሮች የሠራተኛው ሕዝብ ሥልጣን በሚነጥቅበት ጊዜ ለሚ
ደረገው የውጭ ጣልቃ ገብነት ተከላካይ ነው ። የሶቪ
የት ሕብረት በሰፊው በኢንዱስትሪ መበልጸግ ሩሲያ እን
ዳደረገችው ብዙ መስዋዕትነት ሳይጠይቅ ፡ አዲሶች
ሶሻሊስት አገሮች ኢንዱስትሪአቸውን እንዲገነቡ የሚአ
ስችል መሠረት ነው ። የሶቪዬት የሽግግር ገጠመኝ —
(ጉጂና ጠቃሚ ጎን አለው) — ለሎች አገሮች ተግባራቸ
ውን ለማካሄድ ቀላል ያደርገላቸዋል ።

ወደሶሻሊዝም ለሚደረግ ሽግግር ዋናኛ |አስ
በየሃገሩ ወደሶሻሊዝም በተጨማሪ የሚወስደው የቻይናው
ፈላጊ ምሣሌ ሆና በተጨማሪ እንደተመለከትነው በሽግግር
ገጠመኝ ነው ፡፡ ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው በሽግግር
ዘመን የካፒታሊስቶች የመተባበር ሁኔታ ሊፈጠር እንደ
ሚችልና ይህ ሕብረት (በአብዮቱ ውስጥ) በአዲሱ የሶሻ
ሊስት ምርት አደረጃጀትና አከፋፈል ውስጥ በውዴታ
መዋጥ Voluntary Submergence ) እንደሚአልቅ ተገንዝ
በናል ፡፡ ይሁንና ይህ በማኦ ሴቱንግና በኮሚኒስት ጋር
ቲው መሪነት በጠቅላላ የመሸጋገሪያ ችግር ለመወጣት
ከተደረጉት አቀራረቦች አንድ ምሳሌ ነው ፡፡ በእርግጥ
የቻንግ ቻይ -- ሼክ አምባገነንነት በኃይል መወርወር
አስፈላጊ ነበር ፤ እናም በኃይል ለመቋቋም የሚፈልጉትን
የቻንግ ወኪሎችና ሌሎች ቡድኖች ላይም ኃይል መጠ
ቀም ዋናው ነበር ፡፡ ግን ዋናው መርሆ ፡ «ኃይል አይደለም ፡
ምሳሌ መሆንና ሕብረተሰባዊ ዕርዳታ መስጠት ነው »
የሚል ነበር ፡፡ ይህ ነው ለሕዝቦች ችግር የማርክሳዊ መሠ
ረታዊ አቀራረብ ፡፡ ትምህርት ፡ ማሳመን ፡ ትዕግሥት
ለሰው ክብር መስጠት — ለጥላቻቸውም ሆነ ላሉበት
ቦታ (ደረጃ) ማለት ነው ፡፡ ወደፊት ወደሶሻሊዝም የሚሻገሩ
አገሮች ከቻይና ከሚማሩአቸው ዘዴዎች አንዳንዶቹ እነ
ኝህ ናቸው ፡፡

ነጻነታቸውን ካገኙ ከቀድሞ ቅኝ ግዛት አገሮችም
ሌሎች አዲስ ገጠመኞች ይገኛሉ ፡፡ የእነዚህ አገሮች ችግር
ባሕሉ የሚንተራስበትና ማንኛውም አውሎ የማሳደሪያ
ምግብና የኑሮ ደረጃ ከፍ የሚልበትን ዘመናዊ ኢንዱስት
ሪን የመገንባቱ ሁኔታ ነው ፡፡ እርግጥ የኢንዱስትሪ መገ
ንባቱ አብዛኛውን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በማድረግ
መልክ ሊካሄድ ይችላል ፡፡ ስለዚህም ይህ ተግባር ወደ
ሶሻሊዝም የሚአሸጋግረውን ድልድይ መሠረት ለማዘጋ



ጀት ሩቅ ጊዜ አይወስድበትም ፡፡ በዚህ የኢንዱስትሪ
ዕድገት በሶሻሊስት አገሮች ይረዳሉ ፡፡ እነርሱም «ለሰላ
ምና » ለጠብ አጫሪው ኢምፔሪያሊዝም የጣላትነት
መቋቋም ባላቸው የጋራ ፍላጎት ከሶሻሊስት አገሮች
ጋር ይቀራረባሉ ፡፡

ሶሻሊስት አገሮች ያገኟቸው ውጤቶች ጥቅም ለቅኝ
ግዛት ሕዝቦችም የዚያኑ ያህል ይሆናል ፡፡ ከአገር አገር
የውጭ ገዥነትን ደርብተው ለራሳቸው ጥቅም አገራቸውን
ለማሳደግ እየሠሩ ናቸው ፡፡ እስከአሁን ድረስ እንኳን ነጻነ
ታቸውን ያላገኙት የቅኝ ግዛቶች የብሔራዊ ነጻነት መለ
ስተኛ ንፋስ ወደ አውሎ ነፋስነት እያደገ ነው ፡፡

ዓለም ወደሶሻሊዝም በመሸጋገር ላይ እየታየች ነው ፤
ካሁን ቀድም ሠፊ አካባቢ ከካፒታሊስትና ኢምፔሪያሊ
ሊስት በዝበዛ ተላቋል ፤ እናም ይህ አካባቢ እያደገ ነው ፤
በአንጻሩ የካፒታሊስት ክበብ እየተጨማተረ አለ ፡፡

* * * * *


« የሰው ልጅ » ይላል ማርክስ ፣ « ራሱ ሊሠራው
እንደሚችል አድርጎ ፕሮ ብሌሞች ያቀርባል ፣ ፕሮብሌ
ሙ ሊመጣ የሚችለውና መፍትሔ የሚአስገኘው ቁሳዊ
ሁኔታ ሲፈጠር ወይም ቢአንስ በመምጣት ላይ እንዳለ
ነው ። »

የሰው ልጅ ደረጃ በደረጃ ፣ በአካባቢው ከሚገኘው
የተፈጥሮ ኃይል ጋር ባደረገው የረጅም ዘመን ትግል ከአ
ውሬነትና ከዝቅተኛ ደረጃ በሰው ሥራና ልምድ ፣ በሳይን
ስና ቴክኒክ ምክንያት ለሁሉም ሰው የጥሩ ሕይወትና
የብልፅግና መግቢያ በር እስከተከፈተበት ድረስ ራሱን
ከፍ አድርጓል ። የሰው ልጅን ዕድገት ለአምስት ሺህ
ዘመን ያህል ያገለገለውንና ለከፍተኛ ዕድገት ግን እሽ
ክላ የሆነውን «የሕብረተሰብን በመደብ መከፋፈል» እን
ዲአከትም የማድረግ ችግር ታሪክ ፊት ለፊት ገጥሟል ።
ይህንን ችግር መፍትሔ የሚሠጡት ቁሳዊ ሁኔታዎች በዛ
ሬው ዘመን አሉ ። የአቶሚክ ኢነርጅ ዘመንና ሁሉንም
ነገር አቶማዊ ማድረግ የሶሻሊዝም ዘመን ነው ።

በማርክሲዝም ሳይንሳዊ ንድፈ — ሀሳብ በመመራት
ከሰው ልጅ በጣም ብዙው ወደሚቀጥለው ሰብዓዊ ታሪክ
ደረጃ እመርታ አካሂዷል ። በራሳቸው ገጠመኞች እና
ልምዶች በመመሥረት ሌላውም የሰው ዘር እውነተኛ
ሰብዓዊ ሕብረተሰብን በመላው ዓለም ለማምጣት በማር
ክሲዝም እየተመራ ይህንን እመርታ ይወስዳል ፣ ያካ
ሂዳል ።



Proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com



WWW.BINYAMHK.WORDPRESS.COM